# Building Bridges of Faith Against Domestic Violence

# [ትምህርተ ሕይወት]

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እምነትን፣ ጋብቻን እና በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጥቃትን በተመለከተ የሚያስተምሩት ትምህርት እና ተግባራቸው:-

## በትግራይ ክልል በአክሱም ያለው ሁኔታ (ከጦርነቱ በፊት)


ጸሐፊ፡ ዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲ (Dr Romina Istratii)

ተርጓሚ፡ ኤልያስ ገብረሥላሴ (Elias Gebrselassie)



የትግበራ ጽሑፍ 3 (አማርኛ)

ሰኔ 2013

## ተከታታይ የትግበራ ጽሑፍ

ይሄ ተከታታይ የጥናት ጽሑፍ የታተመው በኢትዮጵያ፣ ኤርትራ እና ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ሃይማኖታዊ-ባሕላዊ መነሾ ያላቸው የቤት ውስጥ ጥቃቶች ቅነሳን ለማሳደግ እና ለማጠናከር የተቋቋመው ‹ድልድል› የሚለው ፕሮጀክት አካል ሆኖ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የተሠራው በለንደን በሚገኘው የSOAS University of London ውስጥ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ በጀትም ለመጀመርያዎቹ አራት ዓመታት የተሸፈነው የዩናይትድ ኪንግደም UK Research and Innovation (Future Leaders Fellowship, Grant Ref: MR/T043350/1) የወደፊት መሪዎች ኅብረት ‹ለኢትዮጵያ፣ ኤርትራ እና ለዩናይትድ ኪንግደም ዓይነተኛ በሆነው አቀራረብ፡ የቤት ውስጥ ጥቃቶችን ለመከላከል ሃይማኖታዊ ጥናቶችን፣ ጾታና ብልጽግና እና የሕዝብ ጤንነትን ማሰናሰል› በሚል ("Bridging religious studies, gender & development and public health to address domestic violence: A novel approach for Ethiopia, Eritrea and the UK") ፕሮግራሙ ውስጥ ሲሆን የተደገፈው ደግሞ ‹ሃይማኖት፣ ንቃተ ሕሊና እና ጥቃት የመፈጸም ጠባይ፡ እምነትና መንፈሳዊነት በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ጥቃቶችን ለማስቆም ያላቸውን ሚና መረዳት› ለሚል የምርምር ፕሮጀክት ("Religion, conscience and abusive behaviour: Understanding the role of faith and spirituality in the deterrence of intimate partner violence in rural Ethiopia") ከHarry Frank Guggenheim ፋውንዴሽን በ2019 (እ.ኤ.አ) በተገኘ የጥናት በጀት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ የቤት ውስጥ ጥቃትን ለመከላከል ከየቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎች ወይም ተራፊዎች እና ጥቃት ፈጻሚዎች ሃይማኖታዊ-ባሕላዊ የእምነት መንገድ ጋር በከፍተኛ ሁኔታ በመቀራረብ እና ይሄም የቤት ውስጥ ጥቃትን ለማስቆም ወይም ለማሳለጥ ከጾታ፣ ከቁስ እና ሥነ ልቦናዊ መለኪያዎች ጋር እንዴት እንደሚቆራኝ በመረዳት ከቅኝ ከተገዛ አስተሳሰብ[1] ነጻ የማውጣት መንገድን (decolonial approach) ይከተላል፡፡ ፕሮጀክቱ ከኢትዮጵያ እና ኤርትራ ተባባሪዎች እና የገጠርና የከተማ ነዋሪዎች ጋር በመሥራት አዲስ የጥናት እና ተጽእኖ የማሳደር መንገድን ለማምጣት እና በዩናይትድ ኪንግደም የሚገኙና የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ የሆኑ አናሳ ማኅበረሰቦችንና ስደተኞችን ለማዋሐድና በተሻለ መንገድ ለመደገፍ ዕውቀትን ከሁለቱ ሀገራት ለመጠቀም የሚያልም ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ጥናትን፣ ማነቃቃትን፣ የዕውቀት ልውውጥን እና የማኅበረሰብ አሳታፊ እንቅስቃሴዎችን፣ ከአጋሮች፣ ባለ ድርሻ አካላት እና ማኅበረሰብ ጋር አብሮ መሥራትን በሦስቱ አገራት ከሚከተሉት ጉዳዮች አንጻር ይተገብራል፡

ሀ) በቀሳውስትና በነገረ መለኮት ደቀመዛሙርት ዘንድ የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችን/ተራፊዎችን እና ፈጻሚዎችን በተመለከተ ያለውን ዝግጁነት ማሻሻል፡

ለ) ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚደረግባቸው ሀገራት ውስጥ የሚገኙ የውስጥ ጥቃት ላይ የሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃይማኖታዊ-ባሕላዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረታቸው እንዲጨምር፡

ሐ) ለሃይማኖታዊ-ባሕላዊ ኅብረ ብሔራዊ ሕዝብ ትኩረት የሚለግስ እና ምላሽ የሚሰጥ የውስጥ ጥቃት መከላከልን እና ተጠቂዎችንና አጥቂዎችን[2] የሚደግፍ አሠራርን ማበልጸግ እና

መ) ለሁሉም የቡድን አባላት፣ የፕሮጀክት አጋሮች እና ተሳታፊዎች ዕድገትና ብልጽግና የጋራ ምርምር ቡድን መመሥረት እና ዕድሎችን ማመቻቸት፡፡

ፕሮጀክቱ ከዚህ ቀደም በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ማኅበረሰብ ዘንድ በጋብቻ ውስጥ ያለ ጥቃትን በተመለከተ በተሠራ የጥናት ምርምር ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ጥናቱ የምእመናንን ሕይወት፣ በጾታዊ መመዘኛዎች እና ልማዶች መካከል ያለውን ግንኙነት እና በዚህ ሃይማኖተኛ ማኅበረሰብ ውስጥ በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጥቃት በመቀጠሉ እና በመገታቱ መካከል ያለውን ውስብስብ ግንኙነት ከመረዳት አንጻር የእምነትን እና የሃይማኖት ልምምድ ያላቸውን ወሳኝነት አሳይቷል፡፡ እምነት የጥቃት ፈጻሚነትን ጠባይ እና በጋብቻ ውስጥ ከሚኖር ጥቃት ጋር በተያያዘ ያሉ ልማዶችን ለመከላከል ወይም ለማስቆም ውስብስብ በሆነ መንገድ ለንጽጽር በቀረበበት ሁኔታ ጥናቱ በነገረ መለኮት እና ባሕላዊ አረዳድ መካከል ያለውን ወሳኝ የሆነ ውጥረት ገልጧል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀሳውስትና የነገረ መለኮት ሊቃውንት፣ የመንግሥት አካላት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የቤት ውስጥ ጥቃት መከላከል አገልግሎት ሰጪዎች እምነትና የሃይማኖት ልምምድ በምእመናን የጋብቻ ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ውስብስብ ሚና፣ በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጥልን ለማስታረቅ ቀሳውስት የሚከተሉት

[1] ከአስተሳሰብ ቅኝ ግዛት፡፡

[2] የቤት ውስጥ ጥቃት ፈጻሚዎችን ችግራቸውን ተረድቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ፡፡

መንገድን በተመለከተ እና ችግሩን ለመቅረፍ ነገረ መለኮትና የኖላዊነት አገልግሎት እንዴት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችሉ ለማስገንዘብ በሚደረግ ጥረት ይሄ የጽሑፍ ሥራ የዚህን የተጠናቀቀ የጥናት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች ለብዙሀኑ ለማድረስ ያልማል፡፡

## የማጣቀሻ ጥቆማ

ሮሚና ኢስትራቲ (Romina Istratii) (ሰኔ 2013) ‹[ትምህርተ ሕይወት] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቀሳውስት እምነትን፣ ጋብቻን እና በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጥቃትን በተመለከተ የሚያስተምሩት ትምህርት እና ተግባራቸው፡፡ በትግራይ ክልል በአክሱም ያለው ሁኔታ (ከጦርነቱ በፊት)› ትርጉም በኤልያስ ገብረሥላሴ (Elias Gebrselassie)፡፡ የትግበራ ጽሑፍ 3 (አማርኛ). Project dldl/ድልድል: Bridging religious studies, gender & development and public health to address domestic violence in religious communities. SOAS University of London.

## የቅጂ መብት

ከዚህ ፕሮጀክት የሚወጡ ግኝቶች ሁሉ የታተሙት በ UKRI Open Access ሕግ መሠረት እና ዕውቀትን ለሁሉ ለማካፈል ፕሮጀክቱ ካለበት ግዴታ መነሾ ነው፡፡ ሁሉም ግኝቶች የታተሙት በ Creative Commons Attribution NonCommercial (CC BY-NC 4.0) International Licence, https://creativecommons.org/licenses/by-nc/4.0/ ነው፡፡

የጽሑፍ ሥራው ከጸሐፊዋ ያልታተመ የሦስተኛ ዲግሪ ጥናት፡ Istratii, R. "Gender and development through local epistemologies: Understanding conjugal violence among Orthodox *Täwahədo* Christians in northern Ethiopia and implications for changing attitudes and norms within local worldviews." PhD thesis, SOAS University of London, 2019. DOI: https://doi.org/10.25501/SOAS.00030986. ላይ አንዳንድ ይዘቶችን ያካፍላል፡፡

የዚህ ጽሑፍ ሥራ አስፈላጊ ክፍሎች (ሳጥን 3 ጨምሮ) መጀመርያ የታተሙት የጸሐፊዋ ሥራ ከሆነው፡ Istratii, R. *Adapting Gender and Development to Local Religious Contexts: A Decolonial Approach to Domestic Violence in Ethiopia*. London: Routledge, 2020. ላይ ነው፡፡ ይሄ ይዘትም በድጋሚ የታተመው በመጀመርያው አታሚ ፈቃድ ነው፡፡

## ምስጋና

የፊት ገጹን እና የተከታታይ ጽሑፍ ሥራውን የሄዲንግ ፔፐር ዓርማ ስለሠራልን በአዲስ አበባ ከሚገኘው ከDDN Advertising አቶ ዳንኤል ደስታን (Daniel Desta) እናመሰግናለን፡፡

የጽሑፍ ሥራውን በመገምገም የማሻሻያ ዐሳብ እና ግብረ መልስ ስለሰጠን በተጨማሪም ለጽሑፍ ሥራው የሚሆን ርእስ ስለመረጠልን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆነውን መምህር ግርማ ባቱን (Girma Batu) እናመሰግናለን፡፡

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የጾታዊ ግንኙነትና የቤት ውስጥ ጥቃቶች ጥናት እንደሚያመለክተው ሃይማኖታዊ ተቋማት እና ካህናት በምእመናን የጋብቻ ሕይወት ላይ ተጽእኖ አላቸው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ደግሞ አንዳንዴ የካህናት ምክር የከረሩ ጾታዊ ልማዶችን ስለሚያጸና ለሴቶች ጭቆና ብሎም በእጅ አዙር ለሴቶች ጥቃት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ካህናት ስለ ጾታዊ ግንኙነት፣ ጋብቻና በጋብቻ ላይ ስለሚኖር ጥቃት የሚያስተምሩትን፣ ስለራሳቸው መንፈሳዊ ሕይወት እና በማኅበረሰቡ ውስጥ ካለው ጾታዊ ልማድ ጋር ስላላቸው ቁርኝት ወይም ስለ ኖላዊነት ዘዴአቸው ጥልቅ ከሆነ ሳይንሳዊ የባሕል ምርምር አንጻር የተመለከቱ ጥቂት ጥናቶችም አሉ፡፡[3]

ይሄ ጽሑፍ በሰሜን ኢትዮጵያ በጋብቻ ውስጥ ያለ ባሕልና ሃይማኖትን ካስተሳሰረ መዋቅር እና ከነገረ መለኮት ጋር በተገናኘ ጾታዊ ጥቃትን አስመልክቶ ዝንባሌ ስለሚያሳይና ስለአለ እውነታ ዶ/ር ሮሚና ኢስትራቲ (Dr Romina Istratii) በሠሩት አንድ ዓመት በፈጀ የባሕልና ጾታ ተኮር ጥናት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የሀገርኛው ሃይማኖታዊ ትውፊትን መሠረታዊ አስተምህሮ ለማወቅና የሀገረኛው ቤተክርስቲያናዊ የማስተማርያ ዘዴ ታሪካዊ ዕድገትን ዐውዳዊ መልክ በአግባቡ መረዳት ይቻል ዘንድ በጥናቱ በአብነት ትምህርት ቤት፣ በገዳማት፣ በአክሱም ካሉ የአጥቢያና በአዲስ አበባና በመቀሌ ከሚገኙ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡ ጎን ለጎንም ጋብቻና መንፈሳዊ ሕይወትን በተመለከተ እና በተጨማሪም በጋብቻ ውስጥ ያለ ጥቃትን እና በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ጸብንና አስቸጋሪ ሁኔታን የማስታረቅያ ስልቶችን በተመለከተ የተሻለ መረዳት ይኖር ዘንድ በአክሱም ከተማና በዙሪያዋ በሚገኙ ገጠራማ አከባቢዎች ከሚገኙ ካህናትም ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡ በድምሩ በአክሱም የተደረገው ጥናት 244 ተሳታፊዎችን አሳትፏል፡፡

ይሄኛው ጽሑፍም በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የካህናትን አስተያየቶች በጥልቀት በመመልከት የዋናውን ጥናት ምርምር የሚያሰፋ ነው፡፡[4] የ‹ድልድል› ፕሮጀክት ግብ እንዳለ ሆኖ ይሄ የጥናት ጽሑፍ ሥራ የማንኛውንም የጥናት ሥራ ውሱንነት የሚረዳ ሲሆን እዚህ የተጠቆሙት ምልከታዎችም የመጨረሻ አማራጭ እና ሁሉን ያካተቱ ናቸው ብሎ አያምንም፡፡ ዓላማውም የጥናቱን ግኝት በኢትዮጵያ የበለጠ ተደራሽ በማድረግ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንዲመረምሩት እና እንዲጠቀሙበት ማድረግ እና የማኅበረሰቡን የሃይማኖት ሕይወት ባማከለ መልኩ የቤት ውስጥ ጥቃትና ሌሎች ጾታ ተኮር ጉዳዮችን ለመከላከል ለሀገረኛው በሚመጥንና አካታች በሆነ መንገድ አሁን ላይ እየተደረገ ያለውን ጥረት ማሳወቅ ነው፡፡

በምልልሳዊ መንገድ ስለተከናወነው የአማርኛ ትርጉም ሥራም የተወሰነ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ትርጉሙ መሠረት ያደረገው በእንግሊዘኛ የተጻፈውን የዶ/ር ኢስትራቲን ጽሑፍ ሲሆን የብዙ ሂደቶች ውጤትም ነው፡፡ በዝርዝርም፡ በመጀመርያ ደ/ር ኢስትራቲ የእንግሊዘኛውን ጽሑፍ ለአቶ ኤልያስ ገብረሥላሴ አቀረቡ እርሱም የመጀመርያውን ረቂቅ ትርጉም አዘጋጀ፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ አቶ ኤልያስ ጥያቄዎችን ያነሣ ሲሆን ተለዋዋጭ እና ከባድ የሆኑ ቃላትን ከመተርጎም አንጻር የቃላት መረጣ ላይ እና በአንዳንድ አገላለጦች ምን ማለት እንደተፈለገ ማብራሪያ ጠይቋል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደ/ር ኢስትራቲ የማብራሪያ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ሁለቱም በጋር (ጸሐፊና ተርጓሚ) አግባብነት ያላቸውን የአማርኛ ቃላት መርጠዋል፡፡ በአራተኛ ደረጃ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች ከተጠቀሟቸው ቃላት ላለመራቅ ዶ/ር ኢስትራቲ በአማርኛ የተዘጋጀውን ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸውን ሰዎች ዋና የቃለ መጠይቅ ቃል ለተርጓሚው አቅርበዋል፡፡ በአዲስ አበባ፣ መቀሌ እና አክሱም ከሚገኙ የነገረ መለኮት ሊቃውንት፣ ቀሳውስት እና ምእመናን ጋር የተደረጉ አብዛኞቹ ቃለ መጠይቆች በአማርኛ ሲሆኑ በገጠር ከሚገኙ ቀሳውስትና በአክሱም ከሚገኙ ምእመናት ጋር የተደረጉት ቃለ መጠይቆች በትግርኛ ቋንቋ የተደረጉ ናቸው፡፡ በደ/ር ኢስትራቲ ከቀረበው የእንግሊዘኛ ጽሑፍ

[3] ስለ ጉዳዩ ሰፊ ትንታኔ ለማግኘት የሚከተለውን የሮሚና ኢስትራቲ ጆርናል (Romina Istratii) ይመልከቱ "An ethnographic look into conjugal abuse in Ethiopia: A study from the Ethiopian Orthodox *Täwahədo* community of Aksum through the local religio-cultural framework", *Annales d'Éthiopie* 2020-2021, 33: 253-301.

[4] R. Istratii, *Gender and development through local epistemologies: understanding conjugal violence among orthodox Tawahedo Christians in northern Ethiopia and implications for changing attitudes and norms within local worldviews,* PhD thesis, SOAS University of London, 2019, DOI: https://doi.org/10.25501/SOAS.00030986.

(በዋናው ጥናት ላይ ከተጠቀሱት የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በመስክ ሥራ ጊዜ በነበረ መስተጋብር የተዘጋጀ) በመነሣት አቶ ኤልያስ የነዚህን የትግርኛ ቃለ መጠይቆች ቃል ወደ አማርኛ ተርጉሟል፡፡ በመቀጠልም ደ/ር ኢስትራቲ የትግርኛ ተናጋሪዎቹ ማለት የፈለጉትንና ዋነኛ ዐሳባቸውን በተሻለ እንዲገልጥ በማሰብ አንዳንድ ቃላት እንዲቀየሩ አንዳንዶቹ ደግሞ እንዲሻሻሉ ዐሳብ ሰጥተዋል፡፡ በአምስተኛ ደረጃ አቶ ኤልያስ የተሰጡትን ዐሳቦች አካቷል፡፡ በመጨረሻም ዶ/ር ኢስትራቲ የመጨረሻውን የአማርኛ ትርጉም ቃል በቃል ያረሙ ሲሆን ለአቶ ኤልያስ የመጨረሻ ማስተካከያ ዐሳቦችን ሰጥተዋል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ሥራ ሙሉ የትርጉም ሥራ ወደ ስምንት ወር ገደማ ፈጅቷል፡፡

## ባሕላዊው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ እና ፈተናዎቹ

ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ በመንግሥት የሚመራ ትምህርትን እስኪያስተዋውቁ ድረስ በኦርቶዶክሳዊቷ ኢትዮጵያ ትምህርት በቤተክርስቲያኗ እጅ ላይ ነበረ፡፡ ይሄን ሃይማኖታዊ ትምህርት ወንዶችም ሴቶችም መማር የሚችሉ ሲሆን ሴቶች ግን በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ኋላ ይቀራሉ፡፡ ለምሳሌ ጾታ ተኮር በሆኑ ልማዶቹ ማኅበረሰቡ ሴትን ልጅ ለቤት እመቤትነት ብቻ ሲያጭ በቤተክርስቲያን ደግሞ በክፍያ የሚሠሩ ሥራዎችን የማግኘት ዕድላቸው ጠባብ ነው፡፡[5] በሌላ በኩል ሴቶች ሊሳተፉበትና ግእዝን የማንበብና የመጻፍ ጥበብን ሊማሩ የሚችሉበት ንባብ ቤት የቋንቋ ጥናትና የትርጓሜ ሥልጠና አይሰጥበትም፡፡ በዚህም ምንም ስንኳ አንዳንድ ሴቶች በግእዝ የሚጸለዩ የቤተክርስቲያን ጸሎቶችን ቢያውቋቸውም ሙሉ በሙሉ ምን እንደሚሉ እና ነገረ መለኮታዊ ፍቺአቸውን መረዳት ላይ ግን ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ በመስክ ጥናት ወቅት እንዲት ሴት ‹‹ሃይማኖታዊ ትምህርት ለወንዶች ብቻ ነበረ›› ያለች ሲሆን ሴቶች ስለ ሃይማኖታቸው የሚማሩት በዋነኝነት ‹ከመዝሙራት እና ከሴቶች ገዳማት› ነው ብላለች፡፡[6]

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሴት የሃይማኖት መምህራን አሉ ንቁ ተሳትፎም አላቸው፡፡ ሴቶች ዲያቆን ወይም ቄስ መሆን ስለማይችሉ ወደ ትርጓሜ ትምህርት ቤት በመሄድ በቤተክርስቲያን የመምህርነት ድርሻን ይይዛሉ፡፡ በዚህ የዶ/ር ኢስትራቲ ጥናት ላይ በቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የሚገኙ የወንጌላት ትርጓሜ እውቀት ያላቸው ሁለት ሴት መምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል።

የአብነቱ ትምህርት አጠቃላይ ቅርጽ አክሱም በሚገኙ በአንድ መምህር በጥሩ ሁኔታ እንደሚከተለው ተገልጧል፡

> የአብነቱ ትምህርት የሚጀምረው ፊደል በመማር ነው፣ በመቀጠልም ወደ ንባብ ቤት ከዛም ወደ ዜማ ከዛ ወደ አቋቋም ይሄዳል፡፡ ዜማ በማዜም ብቻ ሲከናወን አቋቋም ግን ተቁሞ በከበሮና በጽናጽል በመታገዝ ነው የሚከናወነው፡፡ በመቀጠልም ወደ ትርጓሜ ቤት ይቀጥላል፡፡ በዚህ መጀመርያ ጥሬ ንባቡ (በግእዝ) ይጠናል፤ በመቀጠልም ፍቺው በተለያዩ ትርጓሜዎች ይጠናል፡፡ በዚህ ቤት ተማሪው እንደምርጫው ከብሉይና ከሐዲስ ይጀምራል፡፡ ዜና አበው በሚባለው ክፍል ደግሞ ስለ አባቶች ማለትም ስለ እነ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ እና ሌሎችም ትምህርት ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል እንደ ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እና የመሳሰሉት አባቶች የሚጠኑት በሊቃውንት-ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡[7]

አንድ የቤተክርስቲያን የታሪክ ምሁር የአብነቱን ትምህርት ጅማሮ ለቅዱስ ያሬድ[8] ሲሰጥ ምክንያት ያደረገው በአብነት ትምህርቱ ዋና ከሚባሉት ትምህርቶች አንዱ ድጓ ያለ ጥርጥር የቅዱስ ያሬድ ሥራ መሆኑን ነው፡፡ የውዳሴ ማርያም (በቅዱስ ኤፍሬም

---

[5] L. Melaku, *History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church: From the Reign of Emperor Caleb to the End of Zagwe Dynasty and from the Classical (Golden) Age of the Present. Part Two and Three* (Addis Ababa, Ethiopia, 2010), 73; ከቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ አዲስ አበባ፣ ጥር 9፣ 2009፡፡

[6] የጥናቱ ተሳታፊ ከሆነችና በለንደን ከምትኖር ሴት ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ጥቅምት 11፣ 2009፡፡

[7] በአክሱም ከሚገኙ የነገረ መለኮት መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዝያ 19፣ 2009፡፡

[8] በአዲስ አበባ ከሚገኙ የታሪክ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ታኅሣሥ 7፣ 2009፡፡

እንደተዘጋጀ ይታመናል) ዜማም የቅዱስ ያሬድ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች እነዚህን የሚማሩባቸው የዜማ ቤቶች መሠረታቸው የቅዱስ ያሬድ ጥበባዊ ሥራዎች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ ማስተማር የጀመረው በጎንደር ዙርአምባ እንደሆነ ይነገራል፡፡[9] የእርሱ ደቀመዛሙርት ደግሞ ወደ ዐድዋ አክሱምና ኤርትራ በመሄድ አስተምረዋል፡፡ ይሄው የታሪክ ምሁር በድጓ መጽሐፍ ውስጥ ቅኔአዊ ይዘት ያላቸው ግጥሞችን አካቷል በሚል አመክንዮ የቅኔ ትምህርት የሚሰጥበትን ቅኔ ቤትም ጭምር ጅማሮ ለቅዱስ ያሬድ ይሰጣል፡፡ ቀጥሎም እንዲህ ዓይነት ቅኔአዊ ግጥሞች የበለጠ እየጠነከሩ የመጡት በ14ተኛውና በ15ተኛው መ/ክ/ዘ (እ.ኤ.አ) ሲሆን ውስብስብ የሆኑ ቅኔዎች ቅኝት የተጀመረው በዚሁ በ15ተኛው መ/ክ/ዘ (እ.ኤ.አ) በጎጃም ወሎ ነው በማለት ያብራራል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሠረታዊ የአገልግሎት ደረጃዎች ዲያቆን፣ ቄስ፣ መርጌታ እና መምህር ናቸው፡፡ መነኮሳትና መነኮሳይትም ትልቅ ድርሻ ያላቸው ቢሆኑም የክህነት ደረጃዎች አይደሉም፡፡ መርጌታዎች በዜማ ቤት የሚሰጠው የቅዱስ ያሬድ መጽሐፍ የድጓ ትምህርት ሊቃውንት ተብለው ነው የሚታወቁት፡፡ መምህራን ነገረ መለኮታዊ ትርጓሜዎችን በየአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ የሚሰብኩና የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያን ካሉ ሚናዎች ሁሉ የደብተራ ሚና አሻሚ ሲሆን ለቤተክርስቲያኑ ትውፊትም ለየት ያለ ድርሻ ያለው ነው፡፡ ዐሳባቸውን የተጠየቁት የነገረ መለኮት ሊቃውንት እንዳብራሩት በአሁኑ ጊዜ ደብተራዎች በዋነኝነት የዜማ ባለሙያዎች ናቸው፡[10] በ2007 ዓ.ም የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምክትል ዲን የነበሩት መምህር እንዳብራሩት ደብተራ የሚለው ቃል የማስታወሻ ‹ደብተር› የሚል ትርጉም ካለው ‹ደፍተሪ› ከሚለው የግሪክ ቃል ሳይገኝ እንዳልቀረ እና ትርጉሙም ጸሐፊ ማለት እንደሆነ ያብራሩ ሲሆን፤ በአማርኛው ‹ደብተር› የሚለውም ቃል ከዛ የመጣ ነው ብለዋል፡፡[11] እርሳቸው እንደሚያረጋግጡት ሁሌ ላይሆን ቢችልም ደብተራዎች ምሥጢራዊ አንድምታዎችን የሚያውቁ ሊቃውንት ናቸው፡፡ አንዳንድ ደብተራዎች ግን በሥርዓተ አምልኮ ዜማዎች ላይ ብቻ የሠለጠኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በእርግጠኝነት የትምህርት ደረጃቸው እንዲህ ነው ብሎ መናገር ያስቸግራል፡፡

ዲያቆን ለመሆን ለተወሰኑ ዓመታት ማጥናት ይጠይቃል፣ ከዛ ከፍ ያለ ደረጃ ለማግኘት ረዘም ያሉ ዓመታት ትምህርት ይጠይቃል፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜን ለማወቅ ደግሞ ዐሥርት ዓመታትን ሊወስድ ይችላል፡፡ የሊቃውንት ጉባኤ አባል የሆኑ አንድ ሊቅ የአብነት ትምህርቱን ባሕል ሲያስረዱ፡

> በትውፊታዊው የቤተክርስቲያን ትምህርት ተማሪዎች መጀመሪያ በቃል ነው የሚማሩት፡፡ የተማሩትን ነገር ይዘት በደንብ በቃላቸው እስኪይዙ ድረስ ይለማመዳሉ፡፡ ከዛ ይሄን የተማሩትንና በደንብ የያዙትን በደብተራቸው ላይ መጻፍ ይችላሉ፡፡ ለመመረቅ ጽፈው መጨረስ አለባቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ከነርሱ ከፍ ካሉ ተማሪዎች ደብተር በመዋስ የጻፉትን ይመለከታሉ፡፡ በመመረቂያ ጊዜ ደብተሩ ተጽፎ ማለቅ አለበት፡፡ ተመራቂ ተማሪዎችም ይሄንን ደብተር አዲስ ተማሪዎችን ለማስተማር ይጠቀሙበታል፡፡ ብዙ ተማሪዎችም ወደ ሌሎች ትምህርት ቤቶች በመሄድ የራሳቸውን ደብተር ይዘት እዛ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር ያነጻጽራሉ፡፡ በዚህም የራሳቸውን ደብተር ይዘት ያበለጽጋሉ አንጻራዊ የሆኑ ነገሮችንም ያካትታሉ፡፡ በዚህ መንገድ የሚገኘው እስትግቡም[ዕ] ምእላድ (‹መእለአድ›) ሲባል የእያንዳንዱን ተመራቂ ተማሪ አቅም የሚለካ ነው፤ የማስተማሪያ ስንቅም ይሆናቸዋል፡፡[12]

የነገረ መለኮት ሊቃውንቱና ካህናቱ የሁሉም ካህናት የትምህርት ደረጃ እንደ ተማሪው ግላዊ ብቃትና ተሰጥኦ፣ ታታሪነትና የኢኮኖሚ ዐቅም የሚወሰን መሆኑ ላይ የሚስማሙ ይመስላሉ፡፡ አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም በአብዛኛው የገጠር ቀሳውስቱ በነገረ

---

[9] በመምህሩ በጌዴዎን እግር ተተክቶ ትርጓሜ መጻሕፍት ያስተማረው እዚያው አክሱም ውስጥ እንደኾነም ይነገራል።

[10] በትውፊታዊው የቤተክርስቲያን ትምህርት ዘዴ ላይ የተሠሩ አያሌ ጥናቶች አሉ፡፡ ነገር ግን ይሄ ክፍል ከታች እንደተመለከተው ቀሳውስት ያለባቸውን ፈተና አንባቢው ይረዳ ዘንድ በቂ የሆነ ዐውድ ለማቅረብ የታሰበበት ነው እንጂ የነዚህ ጥናቶች ግምገማ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ በዋነኝነት የተመሠረተውም ተሳታፊዎች የትምህርት ዘዴው በተመለከተ ያብራሩት ላይ ነው፡፡

[11] ከቅድስት ሥላሴ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ዲን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ኅዳር 29፣ 2009፡፡

[12] የሊቃውንት ጉባኤ አባል ከሆኑ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ጥር 13፣ 2019፡፡

መለኮት ሥልጠና የመውሰድ ዕድላቸው በተለያዩ መሰናክሎችና ታሪካዊ ምክንያቶች ይገደባል፡፡[13] በአክሱም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ካህናት ለተወሰኑ ዓመታት በዲቁና የሠለጠኑና ያገለገሉ ሲሆኑ በቅስና ማገልገል ከመጀመራቸው አስቀድሞ በቤተክርስቲያን የተክሊል ጋብቻ የፈጸሙ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ መጽሐፍ ቤት ያልገቡ ሲሆን የወንጌልና የመልእክታት ትርጓሜ መደበኛ ሥልጠናም የሌላቸው ናቸው፡፡ አብዛኞቹ የሚያውቁት ቅዳሴን ሰዓታትንና ውዳሴ ማርያምን ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በራሳቸው ተነሣሽነት የወንጌል አንድምታን ያጠኑ ሲሆን ስለ ጋብቻ ትምህርት ሲጠየቁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመጥቀስ ተገቢ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም ምንም ስንኳ በአብነት ትምህርት ከመጀመርያው ጀምሮ ግእዝን ሲማሩ ቢቆዩም እና የግእዝ ጸሎቶችን በቃላቸው ቢያውቁም ቋንቋውን ሁሉም በደንብ የተረዱት አይመስሉም፡፡ አብዛኞቹ ጥቂት ብቻ የትርጓሜ እውቀት እንዳላቸው አልሸሸጉም፡፡ ከዚህ የሚለዩት በየአጥቢያው ያሉት የሃይማኖት መምህራን ናቸው፡፡ እነርሱ ትርጓሜ የተማሩ ቢሆኑም በሁሉም አጥቢያ ቤተክርስቲያን ግን አይገኙም፡፡ ሥልጠናውም ከሁለት እስከ አራት ዓመታት ይፈጃል፡፡ (ከታች ያለውን ሰንጠረዥ 1 ተመልከት)

**ሰንጠረዥ 1፡ የተመረጡ ካህናትት የትምህርት ደረጃ**

| | |
|---|---|
| ቄስ በ ም. ጣቢያ፣, መጋቢት 5፣ 2009 | ዜማ፣ ቅኔ፣ አቋቋም እና መጽሐፍ ተምረዋል፡፡ ለነዚህም ወደ ስድስት ወር ገደማ ወስዶባቸዋል፡፡ ሃይማኖተ አበውና የሐዲስ ኪዳን አንድምታም ተምረዋል፡፡ ምሥጢረ ሥላሴም አጥንተዋል፡፡ |
| ቄስ/መምህር በ ል. ጣቢያ, መጋቢት 10፣ 2009 | አቋቋም በጎንደር፣ የብሉይና የሐዲስ አንድምታ በአክሱም ተምረዋል፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን አንዳንድ ትምህርቶች አጥንተዋል ለምሳሌ የግንቦት 12 ትምህርቱን፡፡ |
| ቄስ በ ል. ጣቢያ, መጋቢት 10፣ 2009 | 14ቱን ቅዳሴያት ተምረዋል፡፡ መጀመርያ ዲያቆን ለመሆን ለ5 ዓመት ተምረዋል፤ ከዛ ወደ ደብረ ዓባይ በመሄድ ከመምህር አሮን ገብረኪዳን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት በዋነኝነት የሚያስፈልጉትን የ14ቱን ቅዳሴያት፣ የሰዓታት፣ የኪዳን እና የሊጦን ዜማ ተምረዋል፡፡ ከቀሰሱ ሦስት ዓመት ሆኗቸዋል፡፡ |
| ቄስ በ ም. ጣቢያ, የካቲት 1፣ 2009 | ለአምስት ዓመት ያህል ተምረዋል፤ የጀመሩት በግእዝ ፊደል ሲሆን ከዛም ቅዳሴና ሰዓታት በመቀጠልም የተወሰነ አንድምታ ተምረዋል፡፡ የሐዲስ እና የብሉይ ትርጓሜ ይሁን የተማሩት፣ መጽሐፍ ቤት ይሁን የገቡት ግልጽ አይደለም፡፡ በቤተክርስቲያን አገልግሎት 57 ዓመት ሆኗቸዋል፡፡ |
| ዲአኮን በ ይ. ጣቢያ, መጋቢት 5፣ 2009 | ለ4 ዓመት ገደማ በዲቁና ያገለገለ ሲሆን በቅርቡ ቅስና ይቀበላል፡፡ |
| ቄስ በ ድ. ጣቢያ, የካቲት 5፣ 2009 | በደብረ ሊባኖስ ለ4 ዓመት ተምረዋል፡፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን አንድምታ ተምረዋል፡፡ |
| ቄስ በ ሕ. ጣቢያ, ጥር 29፣ 2009 | በትግራይ የአብነት ትምህርት ተምረዋል፡፡ ከግእዝ ፊደል ጀምረው ግብረ ዲቁናን አጥንተዋል፡፡ ድጓ ተምረዋል፡፡ በመቀጠልም አቋቋም ተምረዋል፡፡ መጽሐፍ ቤት ስላልገቡ ትርጓሜ አልተማሩም፡፡ ነገር ግን ብሉይ ኪዳንን፣ ሐዲስ ኪዳንን እና የአባቶች መጻሕፍትን በራሳቸው አንበዋል፡፡ ለ10 ዓመት ያህል የተማሩ ሲሆን ለ14 ዓመት ያህል በጎንደር አስተምረዋል፡፡ |

[13] ከታሪክ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ታኅሣሥ 7፣ 2009፡፡; ከቅድስት ሥላሴ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ዲን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ኅዳር 29፣ 2009፡፡

| | |
|---|---|
| መምህር በ ድ. ጣቢያ, ሚያዝያ 18፣ 2009 | በጎንደርና በጎጃም ተምረዋል፡፡ ለ15 ዓመታት ገደማ ነው የተማሩት፡፡ ትርጓሜ ብዙም አልተማሩም ግን በራሳቸው ተነሣሽነት አጥንተዋል፡፡ |

ካህናትንና የነገረ መለኮት ሊቃውንትን አብዛኞቹ ቀሳውስት ለምንድነው መጻሕፍትን መተርጎም የማይችሉት ብዬ ስጠይቃቸው ችግሩ መኖሩን አምነው ችግሩን ታሪካዊ ከሆነው ባሕላዊው የማስተማርያ ዘዴ ደካማ መሆን ጋር አያይዘውታል፡፡ ጥናቱ ረዥም ጊዜ የሚፈጅና ብዙ ሲሆን ተማሪዎች ግን ራሳቸውን እየደገፉ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት የሚጠበቅባቸውን ጊዜ ለመወጣት ይቸገራሉ ብለዋል፡፡[14] አብዛኞቹ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ቆይተው ለመማር ይቸገራሉ ምክንያቱም ከቤተክርስቲያኗ የወጪ ድጋፍ ስለማያገኙ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለማሟላት ከማኅበረሰቡ ለምነው በሚያገኙት ላይ ብቻ ስለሚደገፉ ነው፡፡ ስለዚህም አብዛኞቹ ተማሪዎች በመጻሕፍት ቤት እስከ ሚሰጠው ከፍተኛ ትምህርት ድረስ የሚማሩበት አጋጣሚ አይኖርም፡፡ የመሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ችግር በሚስተዋልባቸው አከባቢዎች አብዛኞቹ ተማሪዎች ወደ አገልግሎት ሊያሰማራና ደሞዝ ሊያስገኝላቸው የሚችለውን ያህል ብቻ ለመማር ይጣጣራሉ፡፡ ለቃለ መጠይቅ የተባበሩኝ ሁሉ እንደሚያምኑት ሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ አይደሉም፤ አንዳንዶች እጅግ ሲጥሩ አንዳንዶች ግን አነስተኛ ፍላጎት የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡[15]

እኚሁ የነገረ መለኮት ሊቅ እንደተናገሩት የቤተክርስቲያን አባቶች ትርጓሜዎች በጥቂት ካህናት ብቻ የሚታወቁበት ብዙ ምክንያቶች አሉ፡

> የአሌክሳንድርያ፣ የሶርያ፣ የአንጾኪያ፣ የሮምና የቀጰዶቅያ አባቶችን ትርጓሜ የያዘውን አንድምታን ለመማር ብዙ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ ትምህርቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎችም ጥቂቶች ሲሆኑ ተማሪው የግድ ትምህርት ቤቶቹ ድረስ መጓዝ ይጠበቅበታል፡፡ ይሄን ትምህርት የሚሰጡ ምምህራንም ጥቂቶች ናቸው፡፡ የተቀሩት ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚያስፈልጉትን ንባብ፣ ዜማና ቅዳሴ ነው የሚማሩት፡፡ ይሄም ክህነታቸውን በዘር ብቻ ከሚያገኙት ከአሮን ልጆች ሁኔታ ጋር በጣም የሚመሳሰል ነው፡፡[16]

የቤተክርስቲያን ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው ፕሮፌሰር ሉሌ መልአኩ ‹‹እንደ ባሕሉ አንድ ልጅ በአከባቢው የንባብ ቤት ትምህርትን ብቻ ነው መማር የሚችለው፤ በአብዛኞቹ የገጠር አከባቢዎች ከፍ ያሉ ትምህርቶችን የሚሰጥ ትምህርት ቤት የለም››[17] ማለታቸው ከላይ ከተነሡት መረጃዎች ውስጥ አንዳንዶቹን እንደሚደግፏቸው ያሳያል፡፡

በኢኦተቤ ውስጥ ቄስ መሆን የሚችሉት ያገቡ ብቻ ናቸው (አለዚያ መመንኮስ አለባቸው)፡፡ ይሄ ቅድመ ሁኔታ ደግሞ በቀሳውስቱ ትምህርት ላይ ተጨማሪ ፈተና ይሆናል፡፡ ያገቡ ካህናት በቤተክርስቲያን ከማገልገል በተጨማሪ ቤተሰባቸውን መደገፍ ስላለባቸው ትምህርት መቀጠል የሚችሉበት ጊዜ አይኖራቸውም፡፡[18] በቤት ውስጥ የሚኖርባቸው ሓላፊነት ለምሳሌ እርሻ ማረስ ቀሳውስቱ ምእመናንን ለማስተማር መስጠት ያለባቸውን ጊዜ ይቀንስባቸዋል፡፡[19] በመስክ ጉብኝት ወቅት ዶ/ር ኢስትራቲ አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን በተደጋጋሚ የጎበኙ ሲሆን ከእሑድ ማለዳ በስተቀር ብዙውን ጊዜ አጥቢያ ቤተክርስቲያናቱ ዝግ ይሆናሉ ወይም ካህናት አይገኙባቸውም፡፡ በአከባቢው የሚኖሩ ሰዎች ካህናቱ እርሻ ሊያርሱ ወይም በማኅበር ተገኝተው ቡራኬ ሊሰጡ አልያም ለስብሰባ ወደ ከተማ ሄደው ሊሆን እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡ ይህም በራሳቸው በካህናት የተረጋገጠ ሲሆን አንድ ካህን ‹‹እኔ ሰዎች

---

[14] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም ከተማ፣ ሐምሌ 12፣ 2009፡፡
[15] በጣቢያ አንድ ከሚገኙ ቄስ ጋር ተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2019፡፡
[16] በፍሬምናጦስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ከሚገኙ አስተማሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መቀሌ፣ ጥር 22፣ 2009፡፡
[17] Melaku, *History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church*, 74.
[18] በቅዱስ ፍሬምናጦስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ካሉ አስተማሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መቀሌ፣ ጥር 22፣ 2009፡፡
[19] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ፤ ግንቦት 12፣ 2009፡፡በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡

ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ መጥተውም እንዲማሩ እነግራቸዋለሁ፡፡ እንዲያ ብያቸው ግን እኔ ወደ ሥራዬ እሄዳለሁ፡፡ ሥራ ሳልሠራ መኖር አልችልም፤ መብላት አለብኝ፡፡ ከብቶቹንም እንዲበሉና እንዲጠጡ ማሠማራት አለብኝ›› ብለዋል፡፡[20]

የነገረ መለኮት እና የአብነት ሊቃውንቱ ከዚህ በተጨማሪም ቤተክርስቲያኗን አዳክመዋታል ብለው የሚያምኑባቸውን የታሪክ አጋጣሚዎች ያነሣሉ፡፡ የ10ኛው መ/ክ/ዘ የዮዲት ጉዲት ወረራ እና የመሐመድ ግራኝ የ16ኛው መ/ክ/ዘ ጥፋት በዋነኝነት የሚጠቅሷቸው ናቸው፡፡[21] አንዳንዶች እንደሚያምኑት ደግሞ ይሄ ደካማ የትርጓሜ ትምህርት አሰጣጥ የተባባሰው የክህነት አሰጣጥ ቀኖና አተገባበር ደካማ በመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡[22] ሉሌ መላኩም ይሄ የሆነው በኢትዮጵያ በተነሣው የሙስሊም ጦርነቶች ወቅት ላይ ሳይሆን እንደማይቀር በመጽሐፋቸው ጽፈዋል፡፡[23] A.H.M. Jones ና E. Monroe በዚህ ጊዜ የተከናወነ እና የተባሉት ችግሮች መኖራቸውን የሚያረጋግጥ የክህነት አሰጣጥን የሚያሳይ ሥርዓት በመጽሐፋቸው ላይ አስፍረዋል፡፡[24] እነዚህ ጸሐፍት በ1520 እ.ኤ.አ. በአቢሲኒያ የፖርቹጋል ልዑካን መሪ የነበረው Francisco Alvarez ዘገባ ጠቅሰዋል፡፡ Alvarez እንደገለጸው እርሱ በተመለከተው አንድ የክህነት አሰጣጥ ላይ በሙቶዎች የሚቆጠሩ ወንዶች በጳጳሱ ለመሾም ተገኝተው ነበር፡፡ ክህነት ከመቀበል የተከለከሉት ከሴት ጋር ጾታዊ ግንኙነት የነበራቸው ብቻ ናቸው፡፡ ቀኖናው ከሚያዘው ውጪ አካለ ስንኩላን ሳይቀር ክህነት መቀበል ይችሉ ነበር፡፡ ሕፃናት እንዲሁም ጨቅላዎች ሳይቀር ክህነት ተቀብለዋል ለዚህም ጳጳሱ ሰጡት የተባለው ምክንያት የቅብጥ ቤተክርስቲያን ሌላ ጳጳስ መቼ እንደምትልክ ስለማይታወቅ ነው የሚል ነው፡፡ ደካማ የሆነ የክህነት አሰጣጥም በአንዳንድ ካህናት ተጠቅሷል፡-

> እኔ የወረዳው አጥቢያ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ነኝ፡፡ ምእመናን በሕጉ መሠረት እየኖሩ መሆን አለመሆኑን እናጣራለን፡፡ ካልሆነ ቄሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ይጠየቃል፣ ከዛም ቅጣት ይተላለፍበታል፣ ከቅስናውም ይሻራል፡፡ እዚህ ነገሮችን የምናከናውነው በዚህ መንገድ ነው፡፡ አሁን ላይ ካህናትን በአግባቡ የመሾም ሥርዓት እየተሰፋፋ ነው ነገር ግን አንቺም እንዳልሽው ከዚህ ቀደም ችግሮች ነበሩ፡፡ ካህናት አይሾሙም ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ካህናትን መሾም የተለመደ ሆኗል፡፡[25]

ካህናት ሕዝቡን በአግባቡ ማስተማር ላለመቻላቸው በነገረ መለኮት ሊቃውንቱ በዋነኝነት የሚነሡት እነዚህ ችግሮችና ታሪካዊ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ በአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ያሉ አንድ መምህር ሌሎች ስለዚህ ጉዳይ የሚያስቡትን ዶ/ር ኢስትራቲ ካብራሩ በኋላ እርሳቸውም ይሄ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል፡

> ልክ ነሽ፡፡ ብዙዎቹ መምህራንና የቤተክርስቲያን አገልጋዮች መጻሕፍት ቤት በመግባት ትርጓሜ ስለማይማሩ ሕዝቡን ማስተማርና መቀየር አልቻሉም፡፡ አብዛኞቹ ቀሳውስት ለቤተክርስቲያን አገልግሎት በዋናነት የሚያስፈልገውን ዜማን ብቻ በመማር ያገለግላሉ፡፡ ነገር ግን ይሄን በዜማ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበትን በመተርጎም ለሕዝቡ ማስተማር ላይ ብዙም አልተሠራም ስለዚህም ሰዎች ጋር የእውቀት ክፍተት አለ፡፡[26]

በአንዳንዶች አመክንዮ ደግሞ አንዳንድ ካህናት በነገረ መለኮታዊ አስተምህሮ የተረጋገጡ አረዳዶችን ከመያዝ ይልቅ ከባሕል ጋር በተቀየጠ እና አፈታሪክንና የማኅበረሰቡን ልማዳዊ እምነት በሚያጎላ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ይሳባሉ፡፡ እኚሁ መምህር ባሕልን ከሃይማኖት ከለዩ በኋላ በአግባቡ ያልተማሩ ካህናት ይሄንን ላይለዩ እንደሚችሉ መከራከርያ አቅርበዋል፡

---

[20] በ ጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡
[21] Melaku, *History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Churc,* 107; የሊቃውንት ጉባኤ አባል ከሆኑት መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ጥር 13፣ 2019፡፡
[22] በቅዱስ ያሬድ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ከሚገኙ አስተማሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ አክሱም፣ ግንቦት 18፣ 2009፡፡
[23] Melaku, *History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church*, 99.
[24] A.H.M. Jones and E. Monroe, *The History of Ethiopia* (London: Oxford University Press, 1935), 75-76.
[25] በጣቢያ አንድ ከሚገኙ ቄስ እና መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡
[26] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም፣ መጋቢት 23፣ 2009፡፡

ሃይማኖት እና ባሕል የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ የሃይማኖት ትምህርት በልማድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከሚተላለፈው ከባሕል ይለያል፡፡ ሃይማኖት በልምድ የሚሄድ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በአንድ አከባቢ ያለ የአለባበስ ባሕል ከሌላው አከባቢ ይለያል፡፡ ሃይማኖት ግን አንድ ነው፡፡ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ክርስቲያን ነው፡፡ አንዲት ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት እና አንዲት ቤተክርስቲያን ነው ያለን፡፡ የሃይማኖታችን አስተምህሮ ይሄ ነው፡፡ ባሕል ግን በአንድ ማኅበረሰብ ስንኳ እጅግ ብዙ ዓይነት ሲሆን ከቦታ ቦታም ይለያያል፡፡ ባሕልን ከሃይማኖት የመለየት ችግር ግን አለ፡፡[27]

ዐሳባቸውን እዲያጋሩ የተጠየቁት አብዛኞቹ የነገረ መለኮት ሊቃውንትና ካህናት ባሕል ሃይማኖት እንዳልሆነ ካረጋገጡ በኋላ ሃይማኖታዊ ግንዛቤ ሳይኖራቸው በባህላዊው መንገድ የሚጓዙ ካህናት ‹‹ቤተክርስቲያንን እጅግ ይጎዷታል›› ብለዋል፡፡ በማብራሪያው እንደተገለጸው ከሆነ እነዚህን ታሪካዊ ጉድለቶች ለማስተካከል ይቻል ዘንድ በቤተክርስቲያኗ የተቀናጀ ጥረት እየተደረገ ነው፡

አሁን ላይ ግን ቤተክርቲያን ይሄንን ችግር ለመቅረፍ ጠንክራ እየሠራች ትገኛለች፡፡ የካህናት የሥልጠና ማእከላት በመክፈት፣ መንፈሳዊ ትህርት ቤቶችን በመክፈት እና የተማሩ መምህራንን በመቅጠር ላይ ትገኛለች፡፡ የሚማሩትና ሥልጠናውን የሚከታተሉት ደግሞ ወደ ቀዬአቸው በመመለስ የአጥቢያቸውን ምእመናን በማስተማር ባሕልን ከሃይማኖት እንዲለዩ ያስተምራሉ፡፡ የነገረ መለኮት ምሩቃንን እና ሰባኪያነ ወንጌልንም አጫጭር ሥልጠናዎችን እንዲሰጡ እናደርጋለን ምክንያቱም እነርሱ በባሕልና በሃይማኖት መካከል ያለውን ልዩነት ስለሚያውቁ ስለ ጋብቻ፣ እምነት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወዘተ... ቤተክርስቲያን የምታስተምረውን ትክክለኛ ትምህርት ያስተምራሉ፡፡ በዚህ መንገድ ቤተክርስቲያን መጥፎ የሆኑ ባሕላዊ ልማዶችን ለምሳሌ ከቤተክርስቲያን ትምህርት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን የሴት ልጅ ግርዛትን እና የመሳሰሉት ለማሻሻልና ለማስወገድ ትጥራለች።[28]

ሌላም የነገረ መለኮት ምሩቅ ጥረቱ ከባሕላዊው የአብነት መንገድ በተለየ የትርጓሜ ትምህርቶች በዘመናዊ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ከመጀመርያ ጀምሮ እንዲሰጡ ማድረግን እንደሚያካትት በመጥቀስ እነዚህ ጥረቶች መኖራቸውን አረጋግጧል፡፡ [29] ካህናትም በስብከትና በኖላዊነት ምክር አሰጣጥ እየሰለጠኑ ነው፡፡ አንድ የአጥቢያ መምህር በነገረ መለኮት ምሩቃን ማኅበር እየተደረገ ስላለው ጥረት ሲናገሩ፡

ይሄንን ግን ካህናት የተማሩትንና በአገልግሎት ጊዜ የሚዘምሩትን መስበክ ይችሉ ዘንድ የስብከት ዘዴ በማሠልጠን ለማሻሻል እየሞከርን ነው፡፡ የትርጓሜ መምህራንንም በአጥቢያ ላይ እየመደብን ነው፡፡ እነርሱ ብዙ ጊዜ የሚያስተምሩት በከተማ ቢሆንም በገጠርም እንዲያስተምሩ እያበረታታናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ አሁን ከሁለት ከተሞች የተውጣጡ 80 ቀሳውስትን በነገረ መለኮት ምሩቃን ለማሠልጠን እያቀድን ነው፡፡ የነገረ መለኮት ምሩቃን ማኅበር የሚባል በውጭም በሀገር ውስጥም ያሉ አባላት ያሉት ማኅበር አለ፡፡ ማኅበሩ ለመጽሐፍ እና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚሆን ገንዘብ ይረዳናል፡፡ ሁሉም የማኅበሩ አባለት ለማኅበሩ ከደሞዛቸው ላይ ያዋጣሉ፡፡ ያዋጡት ገንዘብ ካህናቱን ለማሠልጠን ለሚያስፈልጉት ለመጻሕፍት፣ ለመጽሐፍ ቅዱስና ለተለያዩ ነገሮች መግዣ ይውላል፡፡ ዋና መሥሪያ ቤታቸው ያለው አዲስ አበባ ሲሆን መቀሌም ግን ቅርንጫፍ አላቸው፡፡ እነርሱ እዚህ ብዙ ሥራ ይሠራሉ፡፡ ለምሳሌ ቀሳውስቱን ከ8 እስከ 15 ለሚሆኑ ቀናት በስምንት ዙር ያሠለጠኑ ሲሆን ሥልጠናውም ዶግማን፣ የስብከት ዘዴን፣ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን እና ቀኖናን ያካተተ ነበር፡፡[30]

[27] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም፣ መጋቢት 23፣ 2009፡፡
[28] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም፣ መጋቢት 23፣ 2009፡፡
[29] በቅዱስ ፍሬምናጦስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ካሉ አስተማሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ጥር 22፣ 2009፡፡
[30] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም፣ መጋቢት 23፣ 2009፡፡

እንደተጠቆመው በነዚህ ሥልጠናዎች ምንም ስንኳ ቀኖናዊ ትምህርቱን በሚያጎሉና እነዚህም በዚህ ጊዜ ጋብቻ ላይ ከሚኖሩ ጉዳዮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት እምብዛም በማይዳስስ መልኩ ቢሆንም የጋብቻ ጉዳዮችም ይዳስሳሉ፡

> አዎ በቤተክርስቲያኗ የምሥጢራት ትምህርት ውስጥ ተካቷል፤ ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያ ውስጥ አንዱ ቅዱስ ጋብቻ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ትምህርት ውስጥ ስለ ጋብቻ ምንነት፣ እንዴት መሆን እንዳለበት፣ መረዳዳት እንደሚገባ፣ አንዱ አንዱን መጠበቅ እንደሚገባ እና በጋብቻ ውስጥ ስላለ ዕኩልነት ይማራሉ፡፡ ከዛ ሥልጠናውን የወሰዱት ቀሳውስት ወደ አጥቢያቸው በመሄድ ሌሎች ቀሳውስትን ያሠለጥናሉ፡፡ በዚህ መንገድ ቀስ በቀስ ለውጥ እየመጣ ነው፡፡[31]

አብዛኞቹ ካህናት የነገረ መለኮት ምሩቃን በሆኑባቸውና መደበኛ የሆኑ ሥልጠናዎችን በወሰዱባቸው በከተማ አከባቢ አንዳንድ የሥልጠናው ውጤቶች በግልጽ ይታያሉ፡፡ ነገር ግን ሥልጠና በገጠር አከባቢ ተጽእኖው አነስተኛ ይመስላል፡፡ አንድ በአክሱም ያሉ ቄስ እንደተናገሩት ቀሳውስቱ ሥልጠናውን ታድመው የሚባለውንም ይሰማሉ ነገር ግን የትርጓሜ ትምህርት መሠረት ስለሌላቸው መልእክቱ ሙሉ በሙሉ ላይገባቸው ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ አዲሱን መረጃ ከራሳቸው ጋር ለማዋሐድ በቂ ጊዜ ከማጣት ጥቂት ብቻ ገብቷቸው ወይም በትክክል ሳይረዱት ወደ አጥቢአቸው ይመለሳሉ፡፡[32]

በተጨማሪም ታማሪዎች እና ካህናትት ከፍ ያለ ትምህርት ቢማሩም ወደ ገጠር በመመለስ በቅስና ከማገልገል ይልቅ ወደ ከተማ ሄደው መምህር መሆንን ይመርጣሉ፡፡ ተማሪዎችም የተሻለ የሚሉትን አማራጭ ሲከተሉ ለምሳሌ የአስኳላና የዘመናዊ የነገረ መለኮት ትምህርት ከተማሩ በኋላ ከባሕላዊው የአብነት ትምህርት ፈጽመው ሊርቁ ይችላሉ፡፡ እዚህ ጋር በቀደሙት ጊዜአት የመንግሥት ትምህርት ኃጢአት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ካህናት እንዲማሩ የማይፈቀድ እንደነበር ማስታወስ ይገባል፡፡[33] ቃለ መጠይቅ በተደረገላቸው በተለያዩ ሰዎች እንደተባለው በዚህ ጉዳይ ላይ ቅዱስ ሲኖዶስ ምንም ዓይነት ውሳኔ አሳልፎ የማያውቅ ሲሆን ክልከላው ቀሳውስቱ በጉዳዩ ዙሪያ ከነበራቸው ግላዊ ግንዛቤ የመነጨ ነበር፡፡[34] ቃለ መጠይቅ ካደረግኩላቸው ሰዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ይሄ ካህናት የመንግሥት ትምህርት እንዳይማሩ የነበረ ክልከላ የቤተክርስቲያን ሰዎች የትምህርት ደረጃ የወረደ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል፡፡[35]

አሁን ላይ ምንም ስንኳ ቀሳውስቱ የመንግሥት ትምህርት ከእግዚአብሔር እና ከእምነት ሊያርቅ ስለሚችል አደገኛ እንደሆነ ማስተማራቸውን ቢቀጥሉም በአግባቡ ከተጠቀሙበት ትምህርት ጠቃሚ እንደሆነ ይስማማሉ፤ ስለዚህም ካህናትንም ሆነ ምእመናንን ትምህርት ከመማር አያደናቅፏቸውም፡፡ ነገር ግን ይሄ ማለት በአብነቱ ትምህርት የሚሳተፉ ተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ ጥቂት ካህናትን ብቻም እያፈራ ነው ማለት ነው፡፡[36] አንድ የነገረ መለኮት ተማሪም በዚህ ጉዳይ ስጋቱን እንዲህ ገልጧል፡

> አሁን ላይ ያለው ችግር ወደ ዓለማዊው ዘመናዊ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሰዎች ከምርቃት በኋላ በአንጻሩ ጥሩ ገቢ ያገኛሉ የተሻለ ሕይወትም ይመራሉ፡፡ ወደ አብነት ትምህርት ለሚሄዱት ግን ቤተክርስቲያን በቂ ክፍያ አትከፍልም፡፡ ከዚህም የተነሣ ሰዎች ወደ ዓለማዊው ዘመናዊ ትምህርት መሄድን ይመርጣሉ በዚህም በመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር በጣም እየቀነሰ ነው፡፡[37]

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናቶቿን ለማሠልጠንና በአንዳንድ ካህናት ላይ ሚስተዋለውን ሃይማኖትን ከባሕል ያለ መለየት ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረት እያደረገች ቢሆንም የዘመናዊነት ተጽእኖ፣ የመንግሥት ትምህርት መስፋፋት እና የገጠር ካህናት የቀደመ ደካማ የትምህርት መሠረት ይሄ እንቅስቃሴ ብዙም ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት እየሆኑ

[31] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም፣ መጋቢት 23፣ 2009፡፡
[32] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ አክሱም፣ ሐምሌ 21፣ 2009፡፡
[33] በጣቢያ 2 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[34] አባቱ በአክሱም ከተማ ቄስ ከነበሩ አንድ ምእመን ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሚያዝያ 16፣ 2009፡፡
[35] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ አክሱም፣ ሐምሌ 21፣ 2009፡፡
[36] በጣቢያ 2 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ አ-መደበኛ ውይይት፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[37] በቅዱስ ያሬድ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ካሉ አስተማሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ግንቦት 18፣ 2009፡፡

ይመስላል፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው የዚህ ችግር ተብሎ የሚወሰደው እናም ሥልጠናው የሚቀረጸው በቤተክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች የካህናቱ ችግር ነው ብለው በሚረዱት እጅግ ጠቅላይ በሆነ አረዳድ ላይ ተመሥርቶ ይመስላል፡፡

ለዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የነገረ መለኮት እና ሌሎች የቤተክርስቲያኗ ምሁራን ከሚያቀርቡት አመክንዮ በተቃራኒ በጉዳዩ ላይ የሚሳተፉ ካህናት ጉዳዩን ከመፍታት አንጻር የሚስተዋልባቸው ድክመት ከትውፊታዊው የቤተክርስቲያን ትምህርት ጠባይ መነሾ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ውስብስብ ጉዳዮችም መነሾ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሪፖርት ግልጽ እንደሚሆነው ቀሳውስት በጋብቻ እና በቤተሰብ ጉዳዮች ላይ እና ጾታዊ መስተጋብሮች እና የባለትዳሮች ሕይወት ላይ መጥፎ መልክ ያላቸው ተግባራትን በመቃወም ለማስተማር በተገቢው ደረጃ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ከመማር አንጻር ዝግጁነት የጎደላቸው የመሆናቸው ነገር ከምእመናን ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ላይ እና በራሳቸው ሕይወት ላይ በሚታየው እውነታም ላይ የሚስተዋል ነው፡፡

## ካህናት ስለ ሃይማኖት (እምነት) የሚያስተምሩት

ካህናት እምነታቸውን ሲገልጹ ሕግ ከመጠበቅ እና ከሌሎች ጋር ተስማምቶ ከመኖር አንጻር ነው፡፡ ለብዙዎቹ ትክክለኛው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የሚበየነው ከታሪካዊ ቀዳሚነቱ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ አንድ የቤተክርስቲያን መምህር እንደገለጸው ዋናው ክርስትና ኦርቶዶክስ ነው ምክንያቱም ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ4ኛው መ/ክ/ዘ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ስለሆነ ነው፡፡ በመቀጠል እንዳብራራውም ፍሬምናጦስ ያስተዋወቀው ሃይማኖት ሲሆን ከዛ ጊዜ ጀምሮ ተጠብቆ የቆየ ነው፡፡ ከተሐድሶና በኢትዮጵያ እያደገ ከመጣው ከፕሮቴስታንት ጋር በማነጻጸርም እነኛ ከሐዋርያትና ከቅዱሳን አባቶች ትምህርት የተለዩ በመሆናቸው ትክክል አለመሆናቸውን ገልጧል፡፡[38]

ምእመናንን ስለ እምነት ምን እንደሚያስተምሯቸው ሲጠየቁ አብዛኞቹ ካህናት እንደመለሱት ከሆነ ምእመናን ከዘመዶቻቸውና ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሰላም እንዲኖሩ፣ እንዳይሰርቁ ወይም ሌሎችን በገንዘብ ጉዳይ እንዳያታልሉ፣ ለመጀመርያ የትዳር አጋራቸው ታማኝ እንዲሆኑ እና ከኃጢአት ርቀውና ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በመካፈል በቤተክርስቲያን እንዲኖሩ ይታዘዛሉ፡፡ ብዙዎቹ ካህናት አጽንኦት እንደሰጡት ጾምና ሥጋ ወደሙን መቀበል ለጠንካራ እምነት መሠረታዊ ናቸው፡፡ ብዙ ልምድ ያላቸውና ጥሩ ሥልጠና የወሰዱት ካህናት እነርሱም በግል ሕይወታቸው እነዚህን ማድረግ እንዳለባቸውና ለምእመናን ጥሩ ምሳሌ መሆን እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፡፡ ለ40 ዓመት በክህነት ልምድ ያላቸው አንድ አባት የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ምእመናን ከእንግዶች፣ ከጎረቤትና ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር በሰላም እንዲኖሩ፣ ሌሎችን እንዳይበድሉ እና የራሳቸው ያልሆነውን እንዳይመኙ መምህራን ቀንም ማታም ያስተምራሉ፡፡ እምነት ያለ ፍቅርና ንስሐ ባዶ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ አንገቴ ላይ ይሄንን መስቀል አድርጌ ልዘርፍ፣ በሀሰት ልመሰክር፣ ባለቤቴ ሚስቴ ላይ ሌላ ላገባ፣ ሌሎችን ላማ እና ክፉ ላስብባቸው አልችልም፡፡ ፍርዱን እንዴት አመልጠዋለሁ?[39]

ሌሎች ደግሞ እምነት ከድኅነት ጋር ያለውን ቁርኝት ያጎሉ ሲሆን የግለሰቡ ምርጫና ድርጊት ወሳኝ እንደሆነ አንሥተዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ቄስ እንዳሉት፡

> እግዚአብሔር አያዳላም ወይም ሰዎችን በ[ሀ]ብታቸው፣ በቁመታቸው፣ በክብደታቸው ወይም በቆዳ ቀለማቸው ምክንያት አይገፋቸውም፡፡ እግዚአብሔር ሰውን የሚገፋው ከሰውየው ሥራ የተነሣ ብቻ ነው፡፡ የሰው መጥፎ ሥራው ነው ወደ ሲኦል እንዲወርድ የሚያደርገው፡፡ እግዚአብሔር ‹‹ደሀ ስለሆንክ ወደ እኔ ና›› አይልም፡፡ ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው ሥራው ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን የሚገፋውም የሚቀበለውም በሥራው ምክንያት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚነግረን ሁለት አማራጮች ተቀምጠውልናል፡ እሳት ወይም ውኃ፤ ወደ ወደድነው መስደድ እንችላለን ወይ ወደ ውኃው አልያም ወደ እሳቱ፡፡ እሳቱ የሲኦል ውኃው ደግሞ የገነት ማሳያዎች ሲሆኑ ከሁለቱ የፈለግነውን የመምረጡ ሓላፊነት በእኛ እጅ ላይ ነው፡[40]

---

[38] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[39] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡
[40] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡

ሁሉም ራሱን ኃጢአተኛ አድርጎ የመመልከት ዝንባሌ አለ ይሄም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸውን አብዛኞቹን ሰዎች ራስን የመመርመርንና የንስሓ አስፈላጊነት አጽንኦት እንዲሰጡት አድርጓል፡፡ አንድ ሰው በሕይወት ጉዞው ብዙ መልካም ሥራ ቢኖረውም ያለ ፍጹም ንስሓ መንግሥተ ሰማያትን መውረስ አይችልም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ቄስ እንዳብራሩት፡

> እግዚአብሔር ያዘዘን ስለ ፍቅርና ስለ ሰላም መልካም ሥራዎችን እንድንሠራ ነው፡፡ እርስ በእርሳችን እንድንጨቃጨቅ፣ እንድንተማማ፣ የኛ ያልሆነውን እንድንፈልግ፣ በሀሰት እንድንመሰክር፣ የባልንጀራችንን ሚስት እንድንመኝ አልፈቀደልንም፡ ፡ እነዚህ እግዚአብሔር እንድንሠራ ያዘዘን ሥራዎች አይደሉም፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱን ወይም ተጨማሪ የሠራ ማንኛውም ሰው ካልተናዘዘ ትክክል አይደለም፡፡ አንድ ቤት ሙሉ ወርቅ ለቤተክርስቲያ ቢሰጥ ወይም ለድሆች ቢያበላ ስንኳ ስለ ኃጢአቱ መጸጸት እና ማዘን አለበት፡፡[41]

ሁሉም ቀሳውስት ለንስሓ ዕኩል አጽንኦት አልሰጡም፤ ከነዚህም ውስጥ ነገረ መለኮት የተማሩ መምህራንና ምንም አንዳንዴ የተወሰነ ሥልጠና ብቻ ቢያገኙም በመንፈሳዊ ሕይወት የጎለበቱ ቀሳውስት ዋነኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ተጠያቂዎች በቤተክርስቲያን ሕግ መኖር እንደሚገባ በአጽንኦት ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ሕግጋት ኦርቶዶክሳዊ የድኅነት ትምህርትን በሚገነዘብ መልኩ አስማምተው አላቀረቡአቸውም፡፡ ደ/ር ኢስትራቲ እንዳስተዋሉት ከሆነ አብዛኞቹ ካህናት የእምነት ዓላማው አማኞችን ለመንግሥተ ሰማያት ማብቃት እንደሆነ ይስማማሉ ነገር ግን አንዳቸውም እግዚአብሔርን ከመምሰል ጋር አያይዘው አላቀረቡትም፡፡ ጥቂት የሚባሉ መምህራንና መነኮሳት ብቻ የቅድስና ሕይወት መኖር ለሚለው አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ ጥናት ከሚደረጉባቸው መንደሮች ውስጥ በአንዱ የሚኖር አንድ መምህር መንፈስ ቅዱስ በሰውዬው ላይ መሥራት ይችል ዘንድና በዓለም ካለ ፈተና ይጠብቀው ዘንድ በንስሓ ጸጸት መኖር አስፈላጊ መሆኑን አብራርቷል፡፡[42]

## በጾታዊ ግንኙነት፣ ጋብቻ እና በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጥቃትን አስመልክቶ የካህናት ትምህርት

### ጾታዊ ግንኙነት

በአክሱም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ካህናት ከሞላ ጎደል የቤተክርስቲያኗን የአዋጅ ትምህርት ቢያንጸባርቁም የገለጢቸው ግን እንደ መረዳት መጠናቸው፣ እንደ ሥልጠና ደረጃቸውና ግላዊ ዝንባሌአቸው በተለያየ መንገድ ነው፡፡ አንድ መምህር ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ ወንድና ሴት እኩል ናቸው ይላል ከዚህ የሚቃረነው ባሕል ነው፡፡ ሲጋቡ ሁለቱ አንድ አካል ይሆናሉ፤ በእግዚአብሔር አምሳል አንድ ይሆናሉ፡፡ ገንዘባቸውም የሁለቱም የጋራ ነው፡፡ አንድ አስተሳሰብ ይኖራቸዋል ሥራም በክፍፍል ይሠራሉ፡፡››[43] ብሏል፡፡ እጅግ በጣም የተማሩ አንድ ያናገርኳቸው ቄስም የዘፍጥረት መጽሐፍን በማንሣት በሃይማኖት ትምህርት ወንድና ሴት ዕኩል መሆናቸውን እንደሚስማሙበት ተናገረዋል።

የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል በቀጥታ የሚጠቅሱ ሌሎች ካህናትም አሉ፡፡ ለምሳሌ ‹መጽሐፍ ቅዱስ ብትወድም ባትወድም ሚስት ባሏ የሚለውን ታድርግ ትገዛለትም ይላል፡፡ አሁን ላይ ግን እየተቀየረ ነው (ሚስቶች አይገዙም)›[44] ያሉ አሉ፡፡ ይሄንን ያሉት በዕድሜ የገፉ ግን የነገረ መለኮት መሠረታቸው ደካማ የሆነ ቄስ ናቸው፡፡ በሚያስገርምና ትኩረት በሚስብ መልኩ በቃለ መጠይቁ ጊዜ የነበረ የቤተክርስቲያን ትምህርት በአግባቡ የተማረ መምህርም ይሄንን ዐሳብ በሚደግፍ መልኩ ጭንቅላቱን ሲነቀንቅ ነበር፤ ይሄም መገዛት አለባት የሚለው ዐሳብ ብዙም ባልተማሩት ካህናት ብቻ የሚቀነቀን አለመሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይሄ አገላለጽ ነባር የሆነውና በአንዳንድ ምእመናን ዘንድ አሁንም ድረስ ቅቡል የሆነውን የሴት የበታችነት ባሕላዊ አስተሳሰብ የሚያጸና ነው፡፡

በተጨማሪም አንዳንድ ካህናት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ሴቶችን በመከልከል ላይ የሚያተኩረው ባሕላዊ ልማድን የሚያጸኑ ይመስላሉ፡፡ እነዚህ ልማዶች በራሳቸው በሴት ምእመናን ላይ የሚስተዋሉ ሲሆኑ ቀሳውስቱ ትክክለኛውን ትምህርት በማስተማር ስሕተት መሆናቸውን አያሳዩም፡፡ ለምሳሌ ጥናቱ በተደረገበት መንደር ያሉ ሴቶች በወር አበባቸው ወቅት ወደ ቤተመቅደስ

---

[41] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡
[42] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ግንቦት 12፣ 2009፡፡
[43] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስና መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡
[44] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስና መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡

አይገቡም፤ እሑድ በቅዳሴ ጊዜ ከቤተ መቅደሱ ውጪ ሆነው ነው የሚያስቀድሱት፡፡ አብዛኞቹ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ይሄ ልማድ ጾታዊ አድሎን አያሳይም ብለው ያስባሉ፤ ይልቅስ ይሄ በቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ደም በሚፈሳቸው ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት እንደማይፈቀድላቸው የሚያሳይ ሲሆን የዚህም ምክንያቱ በቤተመቅደስ መፍሰስ ያለበት የክርስቶስ ደም ብቻ ነው የሚለው ቤተክርስቲያናዊ አረዳድ ነው ይላሉ፡፡ ምንም ስንኳ ይሄ ጾታ ተኮር ሕግ አይደለም ቢባልም የቤተክርስቲያኗ የቀኖና መጽሐፍ የሆነው ፍትሐ ነገሥት ግን ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ሴቶች በወር አበባቸው ጊዜ ከቤተክርስቲያን መራቅ እንዳለባቸው ሲሆን አንዲገቡ የሚፈቅድላቸው ካህንም ከክህነቱ እንደሚሻር ያስጠነቅቃል፡፡[45] ጾታ ተኮር ጉዳዮች ላይ የምትሠራው የነገረ መለኮት ምሩቋ ሐረገወይን ቸርነት ቀደም ብላ እንደጠቆመችው ይሄ ክልከላ የባሕላዊ ልማድ ዝንባሌዎች ውጤት እንጂ ነገረ መለኮታዊ አመክንዮ ያለው አይደለም ትላለች፡፡[46] የዚህ ልማድ ምንጩ የብሉይ ኪዳን ትውፊት መሆኑን በማንሣት በአዲስ ኪዳን ክልከላው እንደተነሣ ታብራራለች፡፡ ‹‹ቤተክርስቲያን እንደምታስተምረው ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በወር አበባዋ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያ የገባችን ሴት በድንጋይ ለመውገር የተዘጋጁ ሰዎችን አጅግ አድርጎ ተቃውሟቸዋል፡፡››[47]

የኢኦተቤ በነገረ መለኮታዊ ትምህርቷ ልክ እንደ ወንጌሉ ትምህርት ወንድ እና ሴት ዕኩል መሆናቸውን ብታስተምርም በምእመናን ዘንድ ያሉ አንዳንድ ከብሉይ ኪዳን የተወረሱ ትውፊቶች ግን አሉ፡፡ ምንም ስንኳ አንዳንድ ጾታ ነክ እና ጋብቻ ነክ የሆኑ ጉዳዮች ከሐዋርያት ትምህርት አንጻር ቢበየኑም በአክሱም ባሉ ማኅበረሰብ ውስጥ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው በምእመናን ባሕል ውስጥ የማይጠፋ ቦታ የተሰጣቸው ልምዶች አሉ፡፡

## ጾታዊ ድርሻ

ጾታን መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል በማኅበረሰቡ ውስጥ እጅግ የጎላ ሲሆን ከመጠን በላይ በሚያደክም ሥራ እና በጋብቻ ውስጥ በሚኖር አለመግባባት ከአንዳንድ የሴቶች ጥቃት ዓይነቶች ጋር ይገናኛል፡፡ ምእመናኑ አለ ልዩነት ይሄንን ክፍፍል ለባሕል የሰጡ ሲሆን ካህናቱ እንዲህ ብለው እንደማያስተምሩ አረጋግጠዋል፡፡ ለምሳሌ ሁለት የተለያየ የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ የገጠር ወጣቶች እንዳረጋገጡት ጾታ ተኮር በሆነ መንገድ ሥራን መከፋፈል ባሕል ነው ያሉ ሲሆን ሃይማኖታቸው እንዲህ ዓይነት ክፍፍልን እንደማታስተምር እርግጠኞች ናቸው፡፡[48] አንድ ወንድ እንዳለውም፡ ‹‹በሃይማኖት አይደለም፡፡ ልማዳችን ነው፡፡ በቆየ ባሕል መሠረት ሴት የራሷን ሥራ ትሠራለች ወንድም እንዲሁ የራሱን ሥራ ይሠራል፡፡ ሁለቱም የሚገባቸውን ሥራ ይሠራሉ፡፡ እስካሁን ድረስ ይሄ የቆየ ልማድ አልተለወጠም፡፡››[49] በዛው አከባቢ የሚኖር የአንደኛ ደረጃ መምህር እንዳስተዋለው፡ ‹‹ቤተክርስቲያን ሁሌም ቢሆን ዕኩልነትን ነው የምትሰብከው፡፡ በቤተሰብ ውስጥ አሁን የሚስተዋለው ጾታ ተኮር የሕይወት ዘዬ ልዩነት እና የሥልጣን ክፍፍል የባሕላዊ ሥርዓት ውጤት ነው፡፡››[50] በመንደሩ የሚኖር አንድ ወንድ እንዳረጋገጠውም፡ ‹‹ሃይማኖት ወንድን ለውጪ ሥራ ሴትን ደግሞ ለቤት ሥራ ይመድባል››[51]

---

[45] የመጀመርያው ሁኔታ እንዲህ ይላል፡ ‹ከቀሳውስትና ከዲያቆናት ወገን አንዱስ እንኳ ተደፋፍሮ ከግዳጅዋ (ከደሟ) ያልነጻችውን ሴት ወደ ቤተክርስቲያን ያስገባ በደሟም ወራት ሥጋውንና ደሙን ያቀበላት ቢኖር ከሹሙቱ ይሻር፡፡ ምንም ከነገሥታት ሴቶች ወገን ብትሆን፡፡› ሁለተኛውም በድጋሚ ‹በወር አበባዋ ላይ ያለች ሴት ከወር አበባዋ እስከምትነጻ ድረስ ወደ ቤተክርስቲያን ትገባ ዘንድ እና ከሥጋ ወደሙ ትቀበል ዘንድ አይገባትም፡፡ የንጉሥ ሚስትም ብትሆን፡፡› በትርጉሙ ላይ ቀጥተኛ ትእዛዙ ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ለተጻፈው የመለካውያን ቅጂ ለሆነው ሁለተኛው የቀኖና መጽሐፍ ተሰጥቷል፡፡ Tzadua and Strauss (1968, 46) ን ተመልከት፡፡

[46] H. Cherinet, *Women and Donkeys in Ethiopia: Gender and Christian Perspective* (Addis Ababa: Graphic Printers, 2015, 272-273.

[47] Cherinet, *Women and Donkeys in Ethiopia*, 273.

[48] ከምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዝያ 5፣ 2009፣ ; ከማኅበረ ቅዱሳን አባል ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 28፣2009፡፡

[49] ከምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዝያ 5፣ 2009፡፡

[50] ከማኅበረ ቅዱሳን አባል ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 28፣2009፡፡

[51] ከምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣2009፡፡

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ካህናትም እንዳረጋገጡት ይሄ ጾታ ተኮር የሕይወት-ዘዴ ልዩነት እና ትውፊታዊው የሥራ ክፍፍል ከሃይማኖታዊው ትምህርት የሚቃረን ባሕላዊ ልማድ ነው፡፡ አንድ መምህር ሰዎች ይሄንን ተዋረድ መጠበቅ ለምን እንደሚፈልጉ ሲናገሩ፡ ‹‹ሴቷ በአካላዊ ጥንካሬ ከወንዱ ስለምታንስና ወንዱ በችሎታ ከሴቷ ስለሚያንስ ይሄ ያንተ ሥራ ነው ይሄ ያንቺ ሥራ ነው ይባባላሉ፡፡ ቀሳውስቱ ግን እንደዚህ አያስተምሩም፡፡›› ብለዋል፡፡[52] ሌላ ቄስ ደግሞ በጋብቻ ውስጥ ያለ ጾታ ተኮር ክፍፍልን በሚከተለው ማሳያ አውግዘዋል፡

> ለምሳሌ ሚስትየው ገንዘብ ብትጠይቀው አይሰጣትም፡፡ ‹‹ደክሞኛልና ውኃ ቅዳልኝ›› ብትለው ወይም ሌላ ሥራ ይዞ ከብቶቹን እንዲያይላት ብትጠይቀው ‹‹ይሄ ያንቺ ሥራ ነው›› ይላታል፤ ለራሱም ‹‹ምን ዓይነት ሚስት ነው ያገባሁት? እኔ ሴት ነኝ እንዴ ውኃ ቅዳ፣ ከብቶች ጠብቅ የምትለኝ?›› ይላል፡፡ ይሄ ግን መንፈሳዊ ወይም ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ሰው ሊያውም ለገዛ ሚስቱ ሊሰጣት የሚገባ ምላሽ አይደለም፡፡ አይደለም የገዛ ሚስቱ ሌላ ሴት ተጨንቃና እርዳታ ፈልጋ ቢያገኛት ሊረዳት ይገባል፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚያስተምረን ይሄንን ነው፡፡ ባሏ ሞቶባት ልጆቿን ብቻዋን የምታሳድግን ሴት ዐቅም ያለው ሰው ሁሉ የመርዳት ሓላፊነት አለበት፡፡[53]

ካህናት ስለ ጾታዊ ድርሻ የተናገሩትን በጥልቀት ስንመለከተው እንደ ሥልጣና ደረጃቸውና እንደ ነገረ መለኮት ግንዛቤአቸው ልዩነቶች ይስተዋልበታል፡፡ በአንዳንድ ንግግሮቻቸው ሐዋርያዊው ትምህርት ከብሉይ ኪዳን ልማዶች ያም የማኅበራዊ-ባሕላዊ ልማድ በአደገኛ ሁኔታ በተቀላቀለበት መልኩ ትኩረት በማግኘት በሁለተኛነት ይቀመጣል፡

> ባልየው ዘሩ ከአባቱ ከአዳም ነው፡፡ ሚስት ደግሞ ዘሯ ከእናቷ ከሔዋን ነው፡፡ እግዚአብሔር ባልና ሚስት አብረው እዲኖሩ ስላዘዘ ያንን ትእዛዝ እያከበርን ነው የምንኖረው፡፡ ባል ብቻውን መኖር ስለማይችል ማግባት ቢፈልግ ከሔዋን ዘር የሆነች ሴት አምጥቶ ማግባት አለበት፡፡ ይህች ሴት የቤት ሥራዎችን ስትሠራ ባልየው ደግሞ የውጪ ሥራ ይሠራል፡፡ ይጋባሉ ከዛም ልጆችን ይወልዳሉ፤ ራሳቸውን የሚመስሉ ልጆችን በመውለድም ይራባሉ፡፡[54]

የቄሱ ገለጻ ከቤተክርስቲያኗ መደበኛ ትምህርት የተለየ ባይሆንም ጾታ ተኮር የሥራ ክፍፍልን በውስጡ ስለያዘ ጾታዊ ድርሻን ያስተጋባል፡፡ ስለ እምነታቸው ለማወቅ የቀሳውስቱ ትምህርት ላይ የሚመሠረቱት የገጠር ምእመናን ከላይ ቄሱ እንደተናገሩት በተፈጥሮ አምላክ ባኖረው የጾታ ልዩነት እና ጋብቻ መካከል እና በባሕላዊው ትውፊት ተጽእኖ በተጠበቀው ጾታ ተኮር በሆነው የሥራ ክፍፍል መካከል ያለውን ብዙም ግልጽ ያልሆነ ልዩነት ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ ጾታ ተኮር የሆነው የሕይወት መዋቅር ሚስትነት ላይ ባሳደራቸው ሓላፊነቶች ሴቷ ቤቷን እንድታስተዳድር፣ ልጆች እንድትወልድና እንድታሳድግ እና ሌሎችንም ሓላፊነቶች እንድትሸከም ቀድሞውኑ የሚጠብቅ ስለሆነ እንዲህ ዓይነት ስብከቶች በእጅ አዙር ስለ ሚስትነት የተወሰደውን ይሄንን የማኅበረሰቡን ግንዛቤ በአንዳንድ በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ጥቃቶችን ሊያስቀጥሉ በሚችሉ ማሳያዎች ሊያጸኑ የሚችሉበት ዕድል ይኖራል፡፡

## *ጋብቻ*

በቤተክርስቲያኗ የነገረ መለኮት ትምህርት ሴትና ወንድ ዕኩል ሲሆኑ እግዚአብሔርን የመምሰል እና ወደ ቅድስና የማደግ ዕኩል ክህሎትም አላቸው፡፡ ምንም ስንኳ በወንድና በሴት መካከል ከእግዚአብሔር መጋቢነት የተነሣ በቤተሰቡ ውስጥ ስምምነት ይኖር

---

[52] በጣቢያ 1 ካሉ ቄስና የቤተክርስቲያን መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡

[53] በጣቢያ 1 ካሉ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡

[54] ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2009፡፡

ዘንድ የሥልጣን ልዩነት እንዳለ በቤተክርስቲያን ቢታመንም ይሄ መሠረታዊ ዕኩልነት በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የሚተገበር ሲሆን በዘርፉ ላይ ተጠያቂ በሆኑ መምህራንም የሚታመንበት ነው፡፡

አብዛኞቹ ያናገርኳቸው ካህናት እንዳብራሩት ጋብቻ የተጠነሰሰው በገነት በመጀመርያዎቹ ጥንዶች በአዳምና በሔዋን ነው፡፡ እንዳሉትም ትክክለኛ ኢጋር የሚባሉት የወንድ የመጀመርያ ሚስቱና የሴትም የመጀመርያ ባሏ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድም እንዲሁ ነው ብለዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ቄስ እንዳረጋገጡት ‹‹አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ቢያገባት እና ቢፋቱ ከዛም እንዲሁ ሁለተኛና ሦስተኛ ሚስት ቢያገባ ትክክለኛ ሚስቱ ተደርጋ የምትወሰደው የመጀመርያ ሚስቱ ናት፡፡››[55] በቤተክርስቲያን አስተምህሮ ከአንዷ በኋላ ሌላኛዋን እያከታተሉ ብዙ ማግባትም የሚፈቀድ አይደለም ምክንያቱም የአዳምና ሔዋንን ወይም የአብርሃምና የሳራን አብነት አይከተልምና ነው፡፡ በርካታ ቀሳውስት የአብርሃምና የሳራን ጋብቻ አብነት የሆነ ጋብቻ ይሉታል ይሄም በመከባበር እና በመግባባት ስለኖሩ እንዲሁም እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ እንደተጋቡ ስለቆዩ ነው፡፡

የጋብቻ ዓላማ አሁንም ድረስ የሚያያዘው ልጅ ከመተካት ጋር ሲሆን ይሄም በዋናው የጥናት ሥራ ላይ በጥልቀት እንደተዳሰሰው ቤተክርስቲያኗ የብሉይ ኪዳኑ አረዳድ ላይ እንደምትገኝ እና ከሐዲስ ኪዳኑ እና ከቅዱስ ጳውሎስ ትምህርቶች ጋር ያላት ውሕደት ውስን መሆኑን ያንጸባረቀ ነው፡፡ ይሄም በተከታዩ ካህን አስተያየት ውስጥ በደንብ ተገልጧል፡

> በገነት ሁለቱ አንድ ነበሩ ስለዚህ ባልና ሚስት በመሆን በመራባት ይሄንን ምድር መሙላት አለባቸው፡፡ይሄን እንዲያደርጉ በእግዚአብሔር ታዘዋል፡፡ በዚህም መሠረት እኛም የአዳም ልጆች ስለሆንን ጥምረት እንድንፈጥርና እንድንራባ ከዛ በፊት ግን እንድንጋባ ታዘናል፡፡ በዚህም የአምላካችን የክርስቶስን ትእዛዝ በመከተል እንጋባለን።[56]

አንዳንዶች ከነገረ ድኅነት ጋር የተገናኘው የጋብቻ ነገረ መለኮታዊ ትርጉም የገባቸው ይመስላሉ፡፡ በገዳም ያሉ አንድ መነኩሴ እንዳብራሩት ለሰው ወደ ቀደመ ገነታዊ ክብሩ ለመመለስ ሁለት አማራጮች አሉት ፡፡ ጋብቻ አንዱ መንገድ ሲሆን ሌላኛው ምንኩስና ነው፡፡ በጋብቻ ሕይወት ጥንዶቹ እርስ በእርስ መዋደድን ይማራሉ ርጋታንም ይለማመዳሉ፡፡ በመቀጠል እንዳብራሩት ክርስቲያኖች በቅዱስ ጋብቻ ሲጣመሩ የቀደመ ኃጢአታቸው ይቀርላቸዋል በምሥጢራቱም ይነጻሉ፡፡ በአዲሱ ሕይወት ቅዱስ ጳውሎስ በሰጣቸው የእግዚአብሔር ሕጎች አንድ አካል ሆነው መኖር አለባቸው፡፡ እኚሁ መነኩሴ በአጽንኦት እንደተናገሩት እግዚአብሔር የሚፈቅደው አንድ ወንድን ለአንድ ሴት ብቻ ነው ስለዚህ ከአንድ በላይ ማግባት ወይም ውሽማ መያዝ የተከለከለ ነው፡፡ ይሄም እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበትን ሁኔታም ያም አዳምና ሔዋንን ጥንድ አድርጎ መፍጠሩን ያንጸባርቃል፡፡ በሌላ አገላለጽ ምንም ስንኳ አዳምና ሔዋን ከገነት እስኪባረሩ ድረስ በዘ አግባብ ባይተዋወቁም ጋብቻ የተመሠረተው በገነት ነው፡፡ በጋብቻ ሕይወት ባል ሚስቱን እንዲወድ ሚስትም ለባሏ እንድትገዛ ይጠበቃል፡፡ ሁለቱም በሰላም መኖር አለባቸው፡፡[57]

ሌሎች ቀሳውስትም ምንም ስንኳ በጣም ጥርት ባለ ቋንቋ መግለጹ ቢያጥራቸውም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አረዳድ አንጸባርቀዋል፡፡ ለ40 ዓመት ያህል ጥንዶችን በማገዝ ልምድ ያላቸው አንድ ቄስ እንዳሉት፡

> ጋብቻን በተመለከተ የትምህርቱ ትኩረት ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው እንደ እኅትና ወንድም እንዲተያዩ፣ እርሷ ባሏን ወንድሜ እያለች እንድትጠራው እርሱ ደግሞ ሚስቱን እኅቴ እያለ እንዲጠራት ነው እና እርሱ እርሷን እንዲንከባከባት እና የሚረዳት ነገር እንዳለ እንዲጠይቃት ነው፡፡ ሲደክማትና ሲያማት እንዲረዳት እርሷም በተመሳሳይ እርሱ ሲደክመውና ሲያመው እንድትረዳው ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚወደው ይሄንን ነው፡፡ የጋብቻ ዓላማ አብሮ በአንድ አልጋ መተኛት ወይም ልጆች መውለድ አይደለም፡፡ ዓላማው እርስ በእርስ መዋደድ ነው፡፡

[55] ወደ ጣቢያ 1 በተደረገ ጉዞ ላይ ከአንድ ቄስ ጋር መኪና ውስጥ የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ መጋቢት 21፣2009፡፡
[56] በጣቢያ 1 ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2009፡፡
[57] በጣቢያ 1 ከመነኩሴ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ የካቲት 2፣ 2009፡፡

ለምሳሌ እኔ ሚስት አለችኝ፡፡ ከሷ ውጪ ማንንም አላውቅም፡፡ ይሄን ብቻ ግን በቂ አይደለም፤ ልወዳትና ላከብራት ይገባል፡፡[58]

በዚህ ንግግራቸው ቄሱ ‹ዓለማዊ› ለሆነውና ጋብቻን በሁለት ሰዎች መካከል አብሮ ለመኖር፣ ዘር ለመተካትና የዕለት ተዕለት ሥራን ለመጋራት ብቻ የሚፈለግ አድርጎ በመውሰድ በምእመናን ዘንድ ለተያዘው የጋብቻ አረዳድ መልስ እየሰጡ ነው፡፡ ይሄም በአንድ ቄስ በጥሩ ሁኔታ በተከታዩ አስተያየት ተገልጧል፡

በጋብቻ ወንድና ሴት አብረው ይኖራሉ፣ ልጆችም ይወልዳሉ፤ ሥራቸው እርሻ ከሆነ በእርሻ ቦታቸው፣ ሥራቸው ንግድ ከሆነ በንግዳቸው፣ ሥራቸው ማኅበራዊ አገልግሎት ከሆነ በማኅበራዊ አገልግሎቱ አብረው ናቸው፡፡ ጋብቻ የሚባለው አብሮ መኖር ነው፡፡[59]

ለጋብቻ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በተመለከተ ቀሳውስቱ በፍትሐ ነገሥት ላይ የተቀመጡትን ቀኖናዊ ቅድመ ሁኔታዎች ነው የደገሙት፡፡ እንዳብራሩትም ጋብቻ በሙሽራውም በሙሽራዋም ፈቃድ ሲሆን መከናወን ያለበት የወላጆቻቸውን ይሁንታም ማግኘት አለበት፡፡[60]

ሁሉም ቀሳውስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ በፊት በቤተክርስቲያን የመጋባትን አስፈላጊነት ተናግረዋል፡፡ ያለጥርጥር ከፍተኛው አጽንኦት የተሰጠው ለሥጋዊ ድንግልና ነው፡፡ የነፍስ ድንግልና በትምህርታቸው ውስጥ እንዴት እንደሚዳሰስ እንዲያስረዱ በተጠየቁበት ጊዜ ቀሳውስቱ ለማስረዳት የቻሉ አይመስሉም፡፡ ቀሳውስቱ በጠቅላላው የሚያበረታቱት ሁሉም ምእመን በድንግልና እንዲቆይና በቤተክርስቲያን እንዲያገባ ነው፡፡ ነገር ግን  ድንግልናቸውን ያፈረሱ ሰዎች በመንደር ውስጥ በሚፈጸም ባሕላዊ ቃል ኪዳን ማግባት እንጂ ሌላ አማራጭ የላቸውምና ባሕላዊ ጋብቻን ብዙም ሲቃወሙ አይስተዋልም፡፡ ምንም ስንኳ ቀኖናው ቢፈቅደውም  በታሪክ እንደሚታውቀው ድንግል ያልሆኑ ሰዎች ጋብቻ  በቤተክርስቲያን አይፈጸምም ነበረ፡፡ አንዳንድ ቀሳውስት በግልጽ እንደተናገሩት ድንግል ያልሆኑ ጥንዶችን በባሕላዊ መንገድ እንዲጋቡ ያሰናብቷቸዋል፡፡

በትውፊቷ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ጋብቻን የምትፈጽመው በተክሊል ሥርዓት ሲሆን እርሱም ለድንግል ሙሽራና ሙሽሪት ነው፡፡ ቅዱስ ጋብቻ በካህናትም በምእመናንም እንደተረጋገጠው ለዲያቆናትና ለድንግል ሚስቶቻቸው ብቻ ነበር የሚፈጸመው[61]፡፡ ያለጥርጥር ለቅዱስ ጋብቻ ያለው አረዳድ ደናግላን ጥንዶች ብቻ ለዕድሜ ልክ የሚጣመሩበት ‹ሽልማት› የሚል ነው፡፡ አንድ ቄስ እንዲህ አብራርተውታል፡

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጋብቻ ማለት መጋባት የሚፈልጉ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመምጣት ቃል ኪዳን የሚግባቡበት ነው፡፡ እንደዚህም ይላሉ፡ ‹‹ከዚህ ቀደም ሁለት ነበርን ከዚህ በኋላ ግን አንድ ነን፣ ተመሳሳይ ነን፣ መደጋገፋችን አንድ ነው፣ ሥራችን አንድ ነው፣ ልባችን አንድ ነው፣ ሕሊናችን አንድ ነው፡፡›› ንስሓ አባታቸው ፊት ቃል ይገባሉ፡፡ እንዲህም ይላሉ ‹‹ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እኔ ካንቺ (ካንተ) ጋር ነኝ፣ እስከ ሕይወቴ መጨረሻ ድረስ ካንቺ (ካንተ) ጋር ነኝ፡፡ መራመድ ቢያቅትሽ(ህ)፣ ማየት ቢያቅትሽ(ህ)፣ ቢያምሽ(ህ) ላልጠላሽ(ህ)፡፡›› የተክሊል ሥርዓት አለ፡፡ ከመጽሐፈ ተክሊልም ይነበባል፡፡ ጥንዶቹም አንዳቸው ለሌላቸው በድጋሚ ያነባሉ፡፡ ተክሊል ድንግል ለሆኑ ሰዎች ብቻ ነው፡፡[62]

[58] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡

[59] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2009፡፡

[60] ከሽሬ ወደ አክሱም በነበረ ጉዞ ላይ ከአንድ ቄስ ጋር በመኪና ውስጥ የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ግንቦት 26፣ 2009፡፡

[61] ለምሳሌ በጣቢያ 3 ከአንድ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 1፣ 2009፡፡

[62] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2009፡፡

በአብዛኞቹ ካህናት እንደተገለጠው ቅዱስ ሲኖዶስ በጊዜ ሂደት የተክሊል ሥርዓትን ከምእመናንም ወገን ድንግል ለሆኑት ፈቅዷል። አንድ የነገረ መለኮት ምሩቅ ይሄንን ሲያብራራ፡

> በቀደመው ጊዜ ተክሊል ለዲያቆናት ብቻ ነበር ይፈጸም የነበረው፡፡ ከቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በኋላ በተለይም ደግሞ ከአምስተኛው ፓትርያርክ ከአቡነ ጳውሎስ በኋላ ግን ድንግል ለሆነ ሁሉ ይፈጸማል፡፡ በቀደመው ጊዜ የምእመናን ጋብቻ በባሕላዊ መንገድ የተጋቢ ጥንዶች ቃልኪዳን በሽማግሌዎች ይፈጸም ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ከቤተክርስቲያን ውጪ ይፈጸም የነበረው የቀለበት ሥነ ሥርዓት ሳይቀር በቤተክርስቲያን በቡራኬ ነው የሚከናወነው፡፡ በዛም ቀን እነዚህ ሦስቱ ምሥጢራ ማለትም ተክሊል፣ ቀለበት፣ ቅዱስ ቁርባን እና ቅዱስ ሜሮን ይፈጸማሉ፡፡ ከቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ በኋላ ከቤተክርስቲያን ውጪ ሲያጋባ የተገኘ ቄስ ይቀጣል፡፡ አሁን ግን ነገሮች እየተሻሻሉ ሲሆን የጋብቻ ሕጉም በገጠርና በከተማ ተመሳሳይ ነው፡፡[63]

አሁን ላይ ምሥጢረ ተክሊሉን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ አንዳንድ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው፡፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ዲያቆን እንዳረጋገጠው ቤተክርስቲያን ሁሉም ሰው በቤተክርስቲያን በቀለበት ሥነ ሥርዓት እንዲያገባ የፈቀደች ሲሆን ጥንዶቹ ደናግላን ካልሆኑ ትክክለኛውን የንስሓ መንገድ ካለፉ በኋላ መጠናቀቅ ያለበት በጋራ ሥጋና ደሙን እንዲቀበሉ በማድረግ ነው፡፡[64] ሌላ ቄስ ደግሞ እንዳሉት ድንግልናቸውን ያልጠበቁ ጥንዶች ‹‹ፍትሐት ዘወልድ ብቻ ተጸልዮላቸው ጸበል ይረጫሉ››፡፡[65] ጥቂት ቄሶች ድንግል ላልሆኑ ጥንዶች በቁርባን ሥርዐት ያገቡ ዘንድ ከ15 ወይም 20 ዓመት (እንደ አስተያየት ሰጪው የሚለያይ) በፊት የወጣ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መኖሩን ወደ ኋላ በመሄድ ያነሣሉ፡፡ ይሄም ቀሳውስት የቤተክርስቲያን ጋብቻን ከጥንዶቹ አንዱ ወይ ሁለቱም ድንግል ካልሆኑ በተለያየ መንገድ ሊያከናውኑት እንደሚችሉ የሚጠቁማቸው ነው፡፡ አንድ ቄስ እንዳብራሩት ወደ ቤተክርስቲያን ሊያገቡ የሚመጡ ሰዎች ሁሉ አንድ ዓይነት አልነበሩምም፤ አንዳንዶቹ ‹ንጹሕ› ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ‹ኃጢአተኞች› ነበሩ[66] ስለዚህ እነዚህን የተለያዩ ዓይነት ሰዎች የምንቀርብበት መንገድ የተለያየ መሆን ነበረበት፡፡ ቄሱ የሥጋ ድንግልና ቅድመ ሁኔታን ያላሟሉትን በቤተክርስቲያን እንዳያገቡ የመከላከል ሓላፊነትን በያንዳንዱ ቄስ ላይ ያስቀመጡ ሲሆን እኒህ ወደ ባሕላዊ ጋብቻ መሄድ እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡

> በሁለት መንገድ ሁኔታዎች አሁን ላይ መልካም ናቸው፡፡ በቀደመው ጊዜ ምእመናን በቤተክርስቲያን ማግባትን ይፈሩ ነበር፡፡ ካህናቱ በቤተክርስቲያን ሊያጋቧቸው ፈቃደኛ ስለማይሆኑ ወደ ቤተክርስቲያን አይመጡም፡፡ ስለዚህ ምእመናን በባሕላዊው መንገድ ጋብቻቸውን ይፈጽሙ ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ምእመናን የቀሳውስቱን ቡራኬ ለማግኘት ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ፡፡ ጥንዶቹ ለመጋባት እንደሚፈልጉ ሲያሳውቁ የንስሓ አባታቸው ወደ ቤተክርስቲያን ይዘዋቸው ይመጣሉ፡፡ በቤተክርስቲያን ቡራኬ ካገኙ በኋላ ወደ ቤታቸው በመመለስ ባሕላዊ ጋብቻ በቀለበት ይፈጽማሉ፡፡ ከአምሳ ዓመት በፊት ሰዎች ትዳር የሚፈጽሙት በቤታቸው ነበረ፡፡ እርስ በእርስ ቀለበት በመሰጣጣት ቃል ይግባባሉ፡፡ ቀሳውስትም ወደ ተጋቢዎቹ ቤት በመሄድ ትዳሩን ይባርካሉ፡፡[67]

በትውፊቱ መሠረት ከጋብቻቸው በፊት ሁሉም ጥንዶች ለንስሓ የንስሓ አባታቸውን ያገኛሉ፡፡ ድንግልናቸውን እንዳጡ ካመኑ በባሕላዊው መንገድ በቃል ኪዳን በሽማግሌዎች ፊት ይጋባሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ሲፈጠር ካህናት የንስሓ ልጆቻቸውን በባሕላዊው መንገድ እንዲያገቡ ያበረታቱዋቸዋል፡፡ በአንድ ቄስ ቃላት መሠረት፡

[63] ከአባ ሴራፒም ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም፣ ሚያዝያ 11፣ 2009፡፡
[64] የመስከ ማስታወሻ፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[65] ከቤተክርስቲን አስተዳዳሪ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አክሱም ከተማ፣ መጋቢት 1፣ 2009፡፡
[66] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 1፣ 2009፡፡
[67] በጣቢያ 3 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 1፣ 2009፡፡

ተጋቢዎቹ ደናግላን ካልሆኑ ተክሊል እንዲፈጸምላቸው መጽሐፍ እንደማይፈቅድላቸው ይነግራቸዋል፡፡ በባሕላዊው መንገድ እንዲጋቡም ይነግራቸዋል፡፡ የተክሊል ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምላቸው ግን አይፈቅድላቸውም፡፡[68]

ከሁለት አንዱ ድንግል ቢሆኑና አንደኛቸው ድንግል ባይሆኑ ድንግል የሆነው ተክሊል ይፈጸምለታል ሌላኛው ግን አይፈጸምለትም። አንድ ቄስ እንደገለጹት ጥንዶቹ የተለያየ ቦታ ላይ ቆመው የተለያየ ጸሎት እንዲደርስላቸው ይደረጋል፡፡[69]

እነዚህ ልማዶች ያለጥርጥር እንደሚያሳዩት በታሪክ የገጠር ካህናት ለሥጋዊ ድንግልና ልዩ ትኩረት እንደሰጡ እና ይሄንንም በቤተክርስቲያን ለሚፈጸም ጋብቻ ዋና መሥፈርት እንዳደረጉት ነው፡፡ አንዳንድ ካህናት ይሄንን ጥብቅ የሆነ የቀሳውስቱን አቋም ለመከላከል ያቀረቡት ምክንያት አብዛኞቹ ኃጢአተኞችና ድንግል ያልሆኑ ሰዎች አግብተው የፈቱ ናቸው በተጨማሪም ሁለተኛ ጋብቻ በቤተክርስቲያን በጠቅላላው ስለማይበረታታ እነዚህ ጥንዶች ተገፍተዋል የሚል ነው፡፡ ያላገቡም ወይም ፍቺ ያልፈጸሙም ሆነው ግን ድንግል ያልሆኑ ሰዎች ጉዳይ ለዚህ ወግ አጥባቂ ማኅበረሰብ እምብዛም አሳሳቢ አይመስልም፡፡ በዚህ ዘመን ግን ብዙ ሰዎች ከጋብቻ በፊት ግንኙነት ስለሚፈጽሙ (በዚህም በጋብቻ ጊዜ የሥጋ ድንግልናን መሥፈርት አሟልተው ስለማይገኙ) ንስሓ ለሚገቡ ድንግል ያልሆኑ ጥንዶች ተገቢ የሆነውን ጋብቻ ማከናወን አግባብሆኗል፡፡

ምንም ስንኳ ቀኖናው ላይ ቅዱስ ጋብቻን በተመለከተ እንዲህ ዓይነት ማስተካከያ መደረጉ ቢታወቅም በገጠር አከባቢ ድንግል ያልሆኑ ጥንዶች ጋብቻ በቤተክርስቲያን እምብዛም እንደማይፈጸም ቀሳውስቱ አረጋግጠዋል፡፡[70] አንዳንድ ዲያቆናትና ቀሳውስትም ድንግል ላልሆኑ ጥንዶች ቅዱስ ጋብቻን እንደማይፈጽሙላቸው ገልጸዋል፡፡[71] አንድ ዲያቆን የቅብጥ ቤተክርስቲያንን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት በቤተክርስቲያን ተገኝቶ ድንግል ላልሆኑ ጥንዶች ጋብቻ ሲፈጽሙ የመመልከት ዕድሉ ነበረው፡፡ ይሄንንም በማድረጓ የቅብጥ ቤተክርስቲያን ድርጊት የወረደ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ለዚህም ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ድንግል ያልሆኑ ጥንዶች በቤተክርስቲያን በቅዱስ ቁርባን ማግባት የማይችሉ መሆናቸውን ነው፡፡[72]

ምእመናንና ካህናት እንደመሰከሩት አሁንም ድረስ አንዳንድ ቀሳውስት ድንግል ላልሆኑት ቅዱስ ቁርባንን ትተው አክሊል በሚመስል ነገር ሥነ ሥርዓቱ ይፈጽማሉ፡፡[73] ለሁለተኛ ጊዜ የሚፈጸም ጋብቻ በገጠር ካህናት የመፈጸም ዕድሉ ጠባብ ነው፡፡[74] ጥቂት ቀሳውስት እንዳረጋገጡት ድንግል ላልሆኑ ጥንዶች ጋብቻ በአክሊል ሲፈጸምላቸው ቁርባን ግን መቀበል አይፈቀድላቸውም። ጥንዶቹ መቁረብ የሚችሉት ንስሓ ከገቡ በኋላ ብቻ ሲሆን ይሄም መሆን የሚችለው በሌላ ቀን ነው፡፡ ይሄ በሌላ ሦስተኛ ቄስም እንዲህ በማለታቸው ተረጋግጧል፡

ቄሱ ‹‹ድንግል ናችሁ ወይ›› ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ አንዳንዴ ሴቷ ድንግል ሆና ወንዱ ድንግል ላይሆን ይችላል። ይሄ ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ መጋባት አይችሉም፡፡ ነገር ግን ከጾሙ ከጸለዩና ምጽዋት ከሰጡ በኋላ አብረው መሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ተክሊል መፈጸም ይችላሉ፡፡ ቁርባን መቀበል ግን አይችሉም፡፡ ምክንያቱም እርሷ ድንግል ስትሆን እርሱ ግን አይደለም፡፡ ሁለቱም ድንግል ሆነው ቢሆን ኖሮ የንስሓ አባታቸው ለሁለቱም ቁርባን በፈቀደላቸው ነበር፡፡ ድንግል ካልሆኑ ግን መፈጸም አይችሉም፡፡ ከጾሙ ከጸለዩ እና ምጽዋት ከሰጡ በኋላ ግን ለምሥጢረ ቁርባን ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ይችላሉ፡፡[75]

[68] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2009፡፡
[69] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 5፣ 2009፡፡
[70] ለምሳሌ በጣቢያ 2 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሐምሌ 2፣ 2009፡፡
[71] ለምሳሌ በጣቢያ 2 ከሚገኝ ዲያቆን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[72] በጣቢያ 2 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[73] ከምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ግንቦት 8፣ 2009፡፡
[74] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 10፣ 2009፡፡
[75] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡.

ይሄ አገላለጽ የነገረ መለኮት ሊቃውንቱና የተማሩ የሚባሉ ካህናት ካብራሩት ጋር የሚቃረን ነው፡፡ እንደ እነርሱ ከሆነ አክሊል የሚለበሰው ድግልናቸውን የጠበቁት ጥንዶች በቅዱስ ቁርባን ሲጋቡ ድንግልናቸውን እስከ ጋብቻ ድረስ ጠብቀው ስለቆዩ እንደ ሽልማት ነው፡፡ በዚህ አረዳድ ድንግል ያልሆኑት በፍጹም በአክሊል መጋባት የለባቸውም፡፡ በተጨማሪም ሊቃውንቱ እንዳብራሩልኝ ጥንዶቹን አንድ አካል አድርጎ የሚያዋሕዳቸው ቁርባኑ ከመሆኑ አንጻር ያለ ቁርባን የሚፈጸም ጋብቻ ሙሉ ጋብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ይሄ የተሳሳተ አረዳድ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት በቤተክርስቲያን የመነጨው ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ ግንኙነትን ለመከላከል እና ‹ንጹሕ ያልሆኑ› ሰዎች ቅዱስ ቁርባንን እንዳይቀበሉ ለመጠበቅ ሊሆን ይችላል፡፡ በቀደመው ጊዜ ምእመናን የሥጋ ድንግልናቸውን እንዳጡ ከተጠረጠሩ ቀሳውስት ሥጋ ወደሙን ከመቀበል ያሳንፏቸው እንደ ነበር ተወስቷል፡ ፡ ይሄ ሥጋና ደሙን የተመለከተ አስተሳሰብ መልሶ ሳያንሰራራ አይቀርም፡፡ ደናግላን ላልሆኑት ንስሓን ከመስጠት፣ ጾምን ከማዘዝና በመጨረሻም ሥጋ ወደሙን እንዲቀበሉ ከማድረግ ይልቅ ወግ አጥባቂ የሆኑ ቀሳውስት ድንግል ላልሆኑ ቁርባን መቀበል የሚገባ አይደለም ከሚል መነሻ ምናልባት ቅዱስ ቁርባኑን በአክሊል ቀይረውት ሊሆን ይችላል፡፡

በከተማ አከባቢ ግን እንዲህ ያለው ነገር አይስተዋልም፤ እጅግ ብዙ የሆኑ ሰዎች ጥንዶች ሆነው የተራከቦ ሕይወት የጀመሩና ድንግል ያልሆኑትም ጭምር በቤተክርስቲያን ያገባሉ፡፡ ይሄ ሁኔታ በገጠር ከጋብቻ በፊት የሚደረጉ ግንኙነቶች ልክ እንደከተማው በነጻነት እንደማይነገሩ እና ግልጽ እንደማይወጡ ከኖሩም ከሐሜት ለመዳን ሲባልና ከባሕል ያፈነገጡ ላለመሆን በምሥጢር እንደሚጠበቁ ሊያሳይ ይችላል፡፡ ስለዚህ ድንግል ያልሆኑ ቁጥር እንደከተማው የጎላ ላይሆን ይችላል፡፡

ቀደም ብሎ በተጠቀሰው መሠረት በታሪክ እንደሚታወቀው የገጠር ካህናት አሁን ድረስ በቀጠለው ባሕላዊ ጋብቻ ላይ ይታደሙ ነበረ፡፡[76] አንድ የነገረ መለኮት መምህር እንዳሉት ይሄ ከላይ የተነሣውን ቀኖናዊ ክልከላ አይጻረርም ምክንያቱም ቀሳውስቱ የሚገኙት በጓደኝነት ነውና፡

> ቀሳውስት እነዚህ ጋብቻዎች ላይ ለምን ይሄዳሉ ብለሽ ለጠየቅሽው ምክንያቱ ቀሳውስቱ ከሰዎች ጋር በቤተሰባዊ ሕይወት ስለሚቀራረቡ ነው፡፡ እዚህ ያለው ባሕል በጥሩም በመጥፎም ጊዜ አብሮ መሆን ነው፡፡ ስለዚህ ቀሳውስት ከቤተክርስቲያን ውጪ የሚደረጉ ጋብቻዎች ላይ የሚገኙት በማኅበራዊ ሕይወት ምክንያት እንጂ በክህነታቸው ሊባርኩ አይደለም፡፡ ይሄንን ከቤተክርስቲያን ውጪ የሚያደርግ ቄስ ካለ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡[77]

ነገር ግን በተወሰኑ የገጠርና የከተማ ባሕላዊ ሰርጎች ላይ መታደም በነዚህ ጋብቻዎች ላይ ቀሳውስቱ ምንም ስንኳ ምሳሌአዊ ቢሆንም ዋና ድርሻ እንደሚጫወቱ ማስተዋል ያስችላል፡፡ ጥንዶቹና የጥንዶቹ ቤተሰቦች በቀሳውስቱ መገኘት የቤተክርስቲያንና የእግዚአብሔር ቡራኬ አብሮአቸው እንዳለ የሚቆጥሩ ይመስላሉ፡፡

## *ያለ ዕድሜ ጋብቻና ሥጋዊ ድንግልና*

ካህናትና ምእመናን በተለምዶ ለሴት ልጅ የጋብቻ ዕድሜ የሚደረገውን 15 ዓመትን መንግሥት ሕገ ወጥ እንደሚለው ቢያውቁም በሚተገበርበት ጊዜ ግን በግልጽ የሚቃወም አንድም ቄስ የለም፡፡ እንደውም በገጠር በሚከናወኑ ያለ እቻ ጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ላይ ቀሳውስት መገኘታቸው የተለመደ ሆኗል፡፡ የቤተክርስቲያን ሥርዓት በታሪክ አጋጣሚ ባሕላዊውን ያለ እቻ ጋብቻን አስከትሏል ብሎ መከራከር ባይቻልም የቀሳውስቱ ስብከት ግን ይሄ ልማድ በተለይ በቅርብ ዓመታት እንዲቀጥል መንገዱን እንዳመቻቸ ማሳየት ይቻላል፡፡

ካህናት ጋብቻ ላይ የሚያሳዩት ይሄ ክልከላ በትውፊት ሥጋዊ ድንግልናን ለቅዱስ ጋብቻ ዋና ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ አጽንኦት የተሰጠው ከመሆኑ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ አንድ ቄስ እንዳሉት፡ ‹‹ሰዎች ድሮ በቤተክርስቲያን ማግባት ይፈሩ ነበር፡፡

[76] በጣቢያ 1 ከሚገኝ የቤተክርስቲያን መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[77] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፤ አክሱም፣ መጋቢት 23፣ 2009፡፡

የማይመጡት የነበረው ቀሳውስቱ በቤተክርስቲያን ሊያጋቧቸው ስለማይፈልጉ ነው፡፡ ስለዚህ በባሕላዊው መንገድ ያገባሉ፡፡››[78] አንድ ዲያቆን በግልጽ እንደተናገረው ድንግል ያልሆኑ ሰዎች በቤተክርስቲያን በቁርባን ማግባት አይችሉም፡፡[79] በመቀጠል እንዳረጋገጠውም እንዲህ ዓይነት ጥንዶች በቤታቸው ሽማግሌዎችና የንስሓ አባታቸው በተገኙበት በባሕላዊ መንገድ ይጋባሉ፡፡ በተመሳሳይም አንድ መምህር የሆኑ ቄስ እንዳሉት፡ ‹‹ሕጉ ድንግልናቸውን ያፈረሱ ሰዎች በቤተክርስቲያን እንዳይጋቡ ይከለክላል፤ ንስሓ ገብተው ከቤተክርስቲያን ውጪ በቃል ኪዳን ሊጋቡና መልካም ትዳር ሊኖራቸው ይችላል፡፡››[80]

ይሄ ከጋብቻ ጋር በተገናኘ ለሥጋ ድንግልና የተሰጠው ልዩ ቦታ ከአንድ ጎንደር ከተማሩ የገጠር መምህር ጋር በነበረ ውይይት በጥሩ ሁኔታ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡ ምእመናን ላይ የሚያዳክም ተጽእኖ እንዳለው እየታወቀ እና ሃይማኖት ሰዎች ሁሉ መንፈሳዊ ፈውስን ያገኙ ዘንድ የሚረዳ መንገድ መሆኑ እየታወቀ ለምንድነው ትውፊቱ ጋብቻን በተመለከተ የሥጋ ድንግልና ቅድመ ሁኔታን አጥብቆ የሚጠይቀው የሚል ጥያቄ ዶ/ር ኢስትራቲ ለመምህሩ አንሥተውላቸው ነበር፡፡ መምህሩ ሲያብራሩም በትውፊቱ የሥጋም የነፍስም ድንግልና ሁለቱም አስፈላጊዎች ነበሩ ብለዋል፡፡[81] ቅዱስ ጋብቻን በተመለከተ ግን የመጀመርያው ከሁለተኛው ይልቅ የበለጠ ይገናል፡፡ ይሄንንም በጥያቄአዊ መንገድ እንደሚከተለው አመልክተዋል፡ ‹‹ለምሳሌ የሥጋ ድንግልናውን የጠበቀ ሰው የነፍስ ድንግልናም አለው ማለት ይቻላል፤ ነገር ግን የሥጋ ድንግልናቸውን ካጡ የነፍስ ድንግልና አላቸው እንዴት ሊባል ይችላል?››[82] መምህሩ በሥጋ ድንግልና መሥፈርትነት ማን መቀረብ እንዳለበትና እንደሌለበት መወሰን ለነፍስ የሚሰጠውን ትኩረት በሰፊው እንደቀነሰው ቢስማሙም ሥጋዊ ንጽሕና የነፍስ ንጽሕና መኖር አመልካች ስለሆነ በአክሊል መሸለም እንዳለበት ግን ያምናሉ፡፡

ሌሎች ቀሳውስት ደግሞ ሥጋዊ ድንግልና ላይ በጣም ማተኮር አንዳንድ ሰዎች ድንግልናቸውን ‹ዓለማዊ› ለሆነ ምክንያት ሲሉ እንዲጠብቁ ወይም ድንግልናቸውን በተመለከተ እንዲዋሹ ሊያደርጋቸው ስለሚችል ችግር እንዳለው ያነሣሉ፡፡ ጥንዶቹ ለቀሳውስቱ ድንግል እንደሆኑ ነግረዋቸው በቤተክርስቲያን ለመጋባት ከጠየቁ ቀሳውስቱ የጥንዶቹን ቃል አምነው መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡[83] አንዳንዶች ይሄ ጉዳይ ከሚያሳድርባቸው ተጽእኖ አንጻር ክብራቸውን ጠብቀው ለመታየትና ማኅበረሰቡ ያስቀመጣቸውን ንጹሕና ድንግል ሆኖ የመገኘት መስፈርቶች ለሚሟላት ካላቸው ፍላጎት የተነሣ በትክክል ያሉበትን ሁኔታ ላይናገሩ ይችላሉ፡፡ አንድ ቄስም በሚከተለው ዐሳብ ይሄ ዕድል መኖሩን አመልክተዋል፡ ‹‹አንዳንዶች ከቤተክርስቲያን ሕግና አስተምህሮ በተቃራኒ ድንግል አለመሆናቸውን ደብቀው በተክሊል ይጋባሉ፡››[84] ይሄ ዐሳብ አስተያየቱን በሰጠ በአንድ ወንድምም እንዲህ ተገልጧል፡ ‹‹ራሳቸውን የማይጠብቁት ሌሎቹ ደግሞ እዚህም እዚያም እያሉ እግዚአብሔር የማይወደውን ነገር ሲሠሩ ቆይተው ድንግል ነን ይላሉ፡፡ ከቤተክርስቲያ ጋር ድብብቆሽ እየተጫወቱ ግራ ያጋባሉ፡፡››[85]

ለቅዱስ ጋብቻ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሥጋ ድንግልና ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ከቤተክርስቲያኗ ቀኖናዊ ትውፊት የተነሣ ቢሆንም ትውፊቱ ግን ስለ መንፈሳዊ ድንግልናም በተመሳሳይ ነው የሚያስተምረው፡፡ ለምሳሌ ድንግል ማርያም በሥጋዋ፣ በነፍሷና በዐሳቧ ድንግል መሆኗ መነገሩን ማንሣት ይቻላል፡፡[86] ስለዚህ ቅዱስ ጋብቻን በተመለከተ በቀሳውስቱ ሥጋዊ ድንግልና በዋናነት ወይም በብቸኝነት በሚያስብል መልኩ ልዩ አጽንኦት የተሰጠው ቤተክርስቲያኗ (በቀሳውስቱ በኩል) ማኅበረሰቡ ለሥጋ ድንግልና ቅድሚያ መስጠትን እንዲለማመድ ወይም ወደ ውስጡ እንዲያሠርጽ በማድረጓ ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡ ፡በገጠር በሚገኙ ምእመናን እንዳሉት የተለመደው ማኅበረሰባዊ ባሕል አዛውንት እናቶች በጋብቻ ጊዜ ሴቶቹ ድንግል መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ነበር፡፡[87] ሥጋዊ ድንግልናን የማስቀደም ዝንባሌ ቅዱስ ጋብቻ ድንግል ላልሆኑት ክፍት መሆኑን በሚቃወሙ

[78] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 1፣ 2009፡፡
[79] የመስክ ማስታወሻ፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[80] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 10፣ 2009፡፡
[81] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 10፣ 2009፡፡
[82] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 10፣ 2009፡፡
[83] ከምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[84] ከመርጌታ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 5፣ 2009፡፡
[85] ከምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[86] ልክ በድርሳነ ጽዮን እንዳለው፡፡
[87] በዕድሜ ከገፉ ሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ግቦት 15፣ 2009፡፡

አንዳንድ ምእመናን ላይም ይስተዋላል፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ቤተክርስቲያን ድንግል ላልሆኑት ቅዱስ ጋብቻን መፍቀዷን በተመለከተ አንድ በለንደን የ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያናት በአንዱ የሚገኙ ምእመን ያቀረቡት ትችት ነው።[88]

ሥጋዊ ድንግልና ላይ ቀሳውስቱ ያላቸውን አቋም የፈጠረው ምንም ይሁን ምን በዋነኝነት የሴቷን ድንግልና ለማግኘት ሲባል በምእመናን ዘንድ የቀጠለው ያለ ዕድሜ ጋብቻ ከዚህ የቤተክርስቲያን ስብከት ጋር ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት እውቅና መስጠት መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ቀሳውስቱ የሥጋ ድንግልናን በተመለከተ በትምህርታቸው ጾታዊ ልዩነት ሳያደርጉ ወንዶችም ሴቶችም ቅድመ ሁኔታውን ማሟላት እንዳለባቸው ማስተማራቸው እውነት ሊሆን ቢችልም እንደዚህ ዓይነት መልእክቶች እንዲሁም ለሴት ድንግልና ቅድሚያ በሚሰጥ ማኅበረሰብ ውስጥ በተዛባ መንገድ ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ ምንም ስንኳ የቀሳውስቱ ስብከት ጾታ የሚለይ ባይሆንም ያልታሰበ ጾታ የሚለይ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ጥብቅ የሆነው የሥጋ ድንግልና ቅድመ ሁኔታ፣ ቀሳውስት የጋብቻ ዕድሜን በተመለከተ ለዘብተኛ መሆናቸው እና በተያያዥም በኢትዮጵያ የተደረጉ የቀደሙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ዲያቆናት ድንግልናን በተመለከተ እርግጠኛ ለመሆን ሲባል በዕድሜ ሕፃናት የሆኑ ሴቶችን ማግባት መፈለጋቸው[89] የተወሰኑ ካህናት ራሳቸው የባሕላዊ መስፈርቶችን ተጽእኖ ማስወገድ አልቻሉም ብሎ ለማሰብ ዕድል ይከፍታል፡፡

## በጋብቻ ውስጥ ያለ ግንኙነት

ሁሉም ካህናት አብርሃምና ሳራን እንደ ዋና ማሳያ በመጥቀስ ጋብቻ የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን መሆኑን አጽንኦት ይሰጣሉ፡፡[90] አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ካገባ እስከ ዕድሜአቸው መጨረሻ ድረስ እንደተጋቡ መቆየት እንደላባቸውና ፍቺ ኃጢአት እንደሆነ ነው የሚያስተምሩት፡፡ ለምሳሌ አንድ ቄስ እንዳረጋገጡት አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ቢያገባት እና ቢፋቱ ከዛም እንዲሁ ሁለተኛና ሦስተኛ ሚስት ቢያገባ ትክክለኛ ሚስቱ ተደርጋ የምትወሰደው የመጀመርያ ሚስቱ ናት፡፡[91] ፍቺ ነገረ መለኮታዊ አመክንዮ ሊቀርብለትና ሊፈቀድ የሚችልበት አንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ተጠቅሰዋል፡ እነርሱም ዝሙት ከአንዳቸው ወይም ከሁለቱም ከተገኘ፣ የአንደኛውን ጥንድ ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል አካላዊ ጥቃት ወይም አንደኛው አካል ትዳሩን አልፈልግም ቢል (ለምሳሌ ባልየው ሚስቱን ትቷት ቢሄድ) ናቸው፡፡ እኒህን ልዩ ሁኔታዎች ለማብራራት አንድ ቄስ ክርስቶስ በተመሳሳይ ጉዳይ በአንድ ፈሪሳዊ ፍቺን በተመለከተ ሲጠየቅ ያስተማረውን በመጥቀስ እንዲህ ብለዋል፡

> ባል ሚስቱን መፍታት ቢፈልግ የፍቺ ወረቀቷን ይስጣትና ይፍታት ብሎ ሙሴ ማዘዙን በማንሣት ዕብራውያን ክርስቶስን ጠይቀውት ነበረ፡፡ አንተስ ምን ትላለህ ብለው ለጠየቁት ሲመልስ፡ ‹‹እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም አይለይ፡፡ ሙሴ ይሄንን ሕግ የሰጣችሁ ስለልባችሁ ደንዳናነት ነው›› ነበር ያላቸው፡፡ ስለዚህ ጋብቻን መፍታት የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ነገር ግን በሥጋ ወደሙ ተወስነው እየኖሩ እሱ ከዚህ በኋላ አልቆርብም ቢልና ከምሥጢር ቢለይ በዚህም አንድነታቸውን ቢንድ ሚስትየው ልትፈታው ትችላለች፡፡ ለሕይወቷ ከፈራችም ልትፈታው ትችላለች ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚፈልገው በሕይወት እንድንቆይና ተጸጽተን በንስሓ ወደ እርሱ እንድንመለስ ነው፡፡ ባሏ የገደላት ሴት ከሞተች በኋላ እንዴት አድርጋ ንስሓ ትገባለች? ሚስቴ በኔ ላይ ሌላ ባል ብታገባ ይሄንንም በወሬና በሐሜት ሳይሆን በማስረጃ ካረጋገጥኩ ልፈታት እችላለሁ፡፡ እኔም በሚስቴ ላይ ሌላ ባገባ እና[...] ሌላ አግብቷል የሚለው በመረጃ ከተረጋገጠ ሚስቴ ልትፈታኝ ትችላለች፡፡ ከነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ውጪ ግን መፋታት የተከለከለ ነው፡፡ አንድ አጥንት አንድ አካል ነን፣ ስንሞትም እንደዛው እንደሆንን እንሞታለን፡፡[92]

የጥንዶቹ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መኖርም በደንብ አጽንኦት የተሰጠው ነው፡፡ አንድ ቄስ እንዳረጋገጡት ካህናት ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠየቀው በአጠቃላይ ሰዉ ሁሉ በሰላም እንዲኖርና ወንዶች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ያስተምራሉ፡፡[93] በአንድ ቄስ

---

[88] የመስክ ማስታወሻ፤ ጥቅምት 12፣ 2009፡፡

[89] N. Jones, T. Bekele, J. Stephenson, T. Gupta and P. Pereznieto with G. Emire, B. Gebre and K. Gezhegne, Early Marriage and Education: The Complex Role of Social Norms in Shaping Ethiopian Adolescent Girls' Lives, Country Report, Overseas Development Institute, 2014, 37 ; የመስክ ማስታወሻ፤ ጥቅምት 12፣ 2009፡፡

[90] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡

[91] መኪና ውስጥ ከቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ መጋቢት 21፣ 2009፡፡

[92] ከቄስና በአከባቢው ከነበረ ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 29፣ 2009፡፡

[93] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ጥር 29፣ 2009፡፡

አስተያየት እንደተወሳው ከሰላም ጋር በተያያዘ ምእመናን በጋብቻ ሕይወታቸው ውስጥ መጣላትን እንዲያስወግዱ ካህናት ይጠይቃሉ፡ ‹‹ሌላ የሚያስተምረው ነገር በጋብቻ ውስጥ መጣላት እንዳይኖር ነው፡፡ በመጣላት ምን ቅድስና አለ? በመጣላት ውስጥ ምንም መልካም ነገር የለም፡፡ ከተጣላህ ኃጢአት ነው፤ አስቸጋሪም ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር አይመራህም፡፡››[94] ሌላም ቄስ እንዳረጋገጡት ቀሳውስት መእመናንን ከተጣሉ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንዳልሆነ ሁሌ ያስጠነቅቃሉ፡፡ በተጨማሪም ጾብ ለባልና ሚስት መጥፎ ስም ከማትረፉም ባለፈ በጥንዶቹ ቤተሰቦች መካከል ቂምን ሊያስከትል ይችላል፡፡[95]

እነዚህ አስተምህሮዎች በአጠቃላይ የሚያስተጋቡት የነገረ መለኮት ሊቃውንትና ቀሳውስት ጋብቻ የማኅበረሰብ ዋነኛ መሠረት መሆኑን እና አንድነቱ መጠበቅ እንዳለበት የሚረዱ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች ጋር በሰላም አብሮ መኖር የሃይማኖቱ ዓላማ የሆነውን ድኅነትን ከማሳካት አንጻር ስላለው አስተዋጽኦ ቤተክርስቲያን የምታስተምረውንም ያንጸባርቃል፡፡ አብዛኛው በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለው የአጥቂነት ጠባይ በጋብቻ ውስጥ ከሚኖር ጭቅጭቅና ጾብ ጋር የተገናኘ ሆኖ ከተወሰደ እነዚህ አስተምህሮዎች በእጅ አዙር በጋብቻ ውስጥ የሚኖር  ጥቃት እንዳይስፋፋ በማገዝ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በደንብ ባልተብራራ መልኩ የጋብቻን መሠረታዊነት የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ከመሆኑ ጋር ማያያዝና ይሄም ካህናት በጋብቻ ውስጥ በምንም ሁኔታ ሰላም መኖር እንዳለበት አጽንኦት ከመስጠታቸው ጋር ተደምሮ ሴቶች ከባላቸው ጋር መጨቃጨቅ እንደሌለባቸው እና እንደ ‹መልካም› ሴት ትዳራቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው በሚያምን የማኅበረሰባዊ ባሕል ቅርጽ ውስጥ ያልተፈለገ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## በጥንዶች መካከል የሚኖር ጥቃት

ካህናት ሁሉ በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጾብን ያወገዙ ሲሆን በተጨማሪም ጋብቻ ጾታ ሳይለዩ ሁለቱም ጥንዶች በሰላም የሚኖሩበት ካልሆነ ጋብቻ አይባልም ብለዋል፡፡ ነገር ግን ካህናቱ በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ጥቃትን በሚያወግዝ ሁኔታ በግልጽ ሲያስተምሩ አይደመጡም፡፡ በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ለተራክቦ ማስገደድን በተመለከተ ግን አንዳንድ ካህናት በማኅበረሰቡ ውስጥ ልማዳዊ የሆነውንና ሴት ልጅ የባሏን የተራክቦ ፍላጎት ሚሚላት አለባት የሚለውን ዝንባሌ ይደግፋሉ፡፡ ይሄ ልክ አንዱ ቄስ ሴት ከባሏ ጋር ተራክቦ መፈጸምን እንቢ ማለት ትችላለች ብለው እንደማያምኑ እንደተናገሩት ማለት ነው፡፡[96] ቄሱ እንደሚሉት አንድ አካል መሆን ማለት ባልና ሚስት ሰውነታቸውን ጨምሮ ምንም ነገራቸውን መለየት የለባቸውም ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ይሄ አመለካከት ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጋር አይቃረንም ነገር ግን በአግባቡ አያብራራውም፡፡  በጋብቻ ውስጥ ባሎች ራሳቸውን የሚስቶች አገልጋይ አድርገው እንዲመለከቱ የሚያዘው የሐዋርያት ትምህርትም ከፍ ብሎ ይደመጣል፡፡ ይሄም ባል ራስ ነው የሚለውን ትምህርት በሚዛን በማስቀመጥ አስገዳጅ የሆነ ተራክቦ ክርስቲያናዊ የጥንዶች ጠባይ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ ካህናት ጋብቻ በጋርዮሽ መፈቃቀድ የሚኖር መሰጣጣት (እንጂ በጉልበት መውሰድ አለመሆኑን) መሆኑን ባላስተማሩና ነገር ግን ባልና ሚስት አንድ መሆናቸውን አጽንኦት በሰጡት ቁጥር በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ተራክቦን በተመለከተ ማኅበረሰቡ የያዘውን ዝንባሌ ከማስጣል ይልቅ ሳይታወቃቸው ሊኮተኩቱት ይችላሉ፡፡

[94] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡
[95] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ጥር 29፣ 2009፡፡
[96] የመስክ ማስታወሻ፤ ግንቦት 6፣ 2009፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡ ቀሳውስቱ የሚያስተምሩት ትምህርት በካህናትና በምእመናን አገላለጽ**

| |
|---|
| ጋብቻ በገነት በመጀመርያዎቹ ጥንዶች በአዳምና በሔዋን አብነትነት እንደተጀመረ<br>የቅርብ ዘመድን ማግባት እንደማይገባ<br>ጋብቻ መፈጸም ያለበት በጋራ ፈቃድ መሆን እንዳለበት<br>ሰዎች ከመጋባታቸው በፊት የአባታቸውን (የቤተሰብ) ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸው<br>ሰዎች ድንግልናቸውን መጠበቅና በቤተክርስቲያን መጋባት እንዳለባቸው<br>ጋብቻ ቃል ኪዳን እንደሆነ እና ሊጠበቅ እንደሚገባ<br>ባልና ሚስት አንድ አካል እንደሆኑ እና በሰላምና በስምምነት መኖር እንዳለባቸው<br>መጣላት ሰዎችን ከእግዚአብሔር እንደሚያርቅ<br>ጾም በጋብቻ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ እንደሆነ<br>ከአንድ በላይ ማግባት፣ ውሽማ መያዝና ፍቺ ክልክል እንደሆኑ |

## የቀሳውስት አስታራቂነት ኖላዊነት በጋብቻ ሕይወት ውስጥ

በጋብቻ ውስጥ በሚኖር ጥቃት ሴቶች ርዳታ በሚፈልጉ ጊዜ ጉዳዮቻቸውን የሚያቀርቡባቸው በገጠር የሚገኙ ዋና ዋና ተቋማት ማለትም ፖሊስ ጣቢያ፣ ፍርድ ቤቶች እና የሴቶች ማኅበራት ሚና ውጤታማነቱ አከራካሪ ቢሆንም ቀሳውስት ግን በጋብቻ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ችግሮችን ለመፍታት ያላቸው አስፈላጊነት ያለ ልዩነት የተወሳ ሲሆን አብዛኞቹም የጋብቻ ሕይወት ችግሮችን ከመፍታት አንጻር ቀሳውስት ስላላቸው ጠቀሜታ ተናግረዋል፡፡ ይሄ የተስተዋለው አሳታፊ በነበረው የመስክ ሥራ ወቅት ላይ በነበረው እንቅስቃሴና ውይይት ነው፡፡ በአንዱ የመስክ እንቅስቃሴ ላይ ተሳታፊዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ በጣም ተመራጭ የሆነውን ተቋም እንዲጠቁሙ እና በጋብቻ ውስጥ ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ወደ የትኛው ተቋም እንደሚሄዱ እንዲለዩ ተጋብዘው ነበረ፡፡ ሰንጠረዥ 2 በገጠር ነዋሪዎች ከሆኑ ወንድና ሴት ነዋሪዎች ጋር የተከናወኑ አራት የተለያዩ የቤተ ሙከራ ሥራዎችን ውጤት ይገልጻል፡፡ በቤተ ሙከራ ሥራው ላይ የተሳተፉት አብዛኞቹ ወጣቶችና የጉልምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ሲሆኑ አማካይ ዕድሜአቸውም 38.45 ዓመት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡ ምእመናን በጋብቻ ውስጥ ጥቃት በሚገጥማቸው ጊዜ የሚሄዱባቸው ተጽእኖ ፈጣሪ ተቋማት**

| | |
|---|---|
| **በ ዲ. ጣቢያ የሚገኙ ወንድ የመስክ ሥራ ተሳታፊዎች፤ ሚያዝያ 22፣ 2009፡፡** | 1. ሃይማኖት/ቀሳውስት<br>2. ፍርድ ቤት<br>3. ሀኪሞች<br>4. ሽማግሌዎች<br>5. መምህራን (ሳኢኑስ ትምህርት) |
| **በ ዲ. ጣቢያ የሚገኙ ሴት የመስክ ሥራ ተሳታፊዎች፤ የካቲት 19፣ 2009፡፡** | 1 ችግር ካለ መፍትሔው ፍርድ ቤት ነው<br>2 የመንፈሳዊ አባት ምክር<br>3 ችግሩን በዕድር መሀል በመናገር |
| **በ ኤል. ጣቢያ የሚገኙ ወንድ የመስክ ሥራ ተሳታፊዎች፤ ሚያዝያ 15፣ 2009፡፡** | 1 ሃይማኖት/ቀሳውስት<br>2 ሽማግሌዎች |

| | |
|---|---|
| | 3 ዓለማዊ ትምህርት ቤት<br><br>4 ጤና ተቋማት<br><br>5 ፖሊስ<br><br>6 ፍርድ ቤት |
| **በ ኤል. ጣቢያ የሚገኙ ሴት የመስክ ሥራ ተሳታፊዎች፤ የካቲት 14፣ 2009፡፡** | 1 ሃይማኖት/ቀሳውስት<br><br>2 ትምህርት ቤት （‘ሳኢኑስ’ ትምህርት）<br><br>3 የእምነት ተቋም<br><br>4 ፍርድ ቤት<br><br>5 ዕድር<br><br>6 ሽማግሌዎች |

ሰንጠረዡ እንደሚያሳየው የቤተ ሙከራው ተሳታፊዎች በጠቅላላው በጋብቻ ውስጥ ችግር በሚከሰትበት ጊዜ መጀመርያ የሚሄዱት ወደ ቄሶች እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ ዓይነታዊ ቃለ መጠይቆቹ (qualitative interviews) በጋብቻ ውስጥ ቀሳውሰት አስፈላጊ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ አንድ ሰውም እንዳለው፡ ‹‹በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አንድ ሰው ያለ ካህን ሊሠራ አይችልም፡፡ ያለ ነፍስ አባት ማግባት የማይቻል ነው››[97] ሌላ ሰውም እንደገና እንዳብራራው ‹‹በአደጋ ጊዜ የምትጠራው የንስሓ አባት ይኖርሃል፡፡ የንስሓ አባት እንደ እግዚአብሔር ነው፡፡ አንድ ሰው ጥፋት እንዲያጠፋ አይፈቀድለትም፡፡ ለንስሓ አባቱ መናዘዝም አለበት፡፡››[98] በቀጣዩ አስተያየት እንደተጠቆመው ቃለ መጠይቅ ያደረግኩላቸው በአጠቃላይ እንደሚያስቡት ከንስሓ አባቶቻቸው ያገኟቸው ምክሮች ጠቃሚ ናቸው፡ ‹‹አዎ ጠቃሚ ነው ብለን እናስባለን፡፡ እነዚህ ቀሳውስት አባቶቻችን ይመጡና እንዲህ ይላሉ፡ ‹‹ይሄ መልካም ነው፡፡ እንደዚህ ነው መሆን ያለባችሁ፡፡›› እነርሱ ከነገሩን ጠቃሚ ነው ብለን እንቀበላለን፡፡››[99] ቃለ መጠይቅ የተደረገለት ሌላ አንድ ወንድ እንዳለው፡ ‹‹ለቀሳውስቱ ሕዝቡን በቤተክርስቲያን ማስተማር ጥሩ ነው፤ ሰዎች ራሳቸውን ለማሻሻል የቀሳውስቱን ምክር ይጠይቃሉ፡፡››[100] የቤተ ሙከራው ውጤት እና እነዚህን መሰል ምስክርነቶች ቀሳውስቱ እንደሚከበሩና በምእመናን እንደሚፈለጉ ያለ ጥርጥር ያሳያሉ፡፡

እነዚህ አገላለጾች ብዙዎችን ያስማሙ ይሆናል ነገር ግን በጥልቀት ሊታዩ ይገባል ምክንያቱም የገጠር ነዋሪዎች በቀሳውስቱ በራሳቸው ሕይወት እና ጋብቻ ውስጥ ድክመቶችን ይመለከታሉና ነው፡፡ በጠቅላላው ለመናገር ቀሳውስቱ የሚያስተምሩት ‹የእግዚአብሔርን ቃል› እንደሆነ ምእመናን እና ካህናት ያስባሉ ነገር ግን የተወሰኑ ቀሳውስት እነዚህን ትምህርቶች በራሳቸው ሕይወት ውስጥ እንደማይተገብሩ እና ለምእመናን መጥፎ ምሳሌ እንደሚተዉም ያስተውላሉ፡፡[101] ይሄ ምእመናንና ቀሳውስቱ በገለጹት መሠረት የቀሳውስቱ ኖላዊ ምክርና ድጋፍ ምን እንደሚመስል ከታየ በኋላ በመጨረሻው ክፍል ላይ ይዳሰሳል፡፡

---

[97] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዝያ 9፣ 2009፡፡
[98] ከወንድ ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[99] ከወንድ ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዝያ 5፣ 2009፡፡
[100] ከወንድ ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዝያ 28፣ 2009፡፡
[101] ለምሳሌ ከሽሬ ወደ አክሱም በነበረ ጉዞ ላይ ከአንድ ቄስ ጋር በመኪና ውስጥ የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ግንቦት 26፣ 2009፡፡

## የቀሳውስት ምክር ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ

ቀሳውስት ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚመልሱት እና የሚመክሩት ሀገርኛ የጋብቻ ችግሮችን በሚረዱበት፣ በሚያስተውሉበት እና በኖላዊነት ድርሻቸው በማማከሩ ላይ ባላቸው ልምድ ላይ ይመሠረታል፡፡ አብዛኞቹ ቀሳውስት በአከባቢአቸው ሰፊ የጋብቻ ችግር እና ፍቺ እንዳለ ይስማማሉ፡፡ የተወሰኑ ቀሳውስት በጥንዶች መካከል የሚኖር አካላዊ ጥቃት ከአከባቢአቸው እንደጠፋ ቢጎተጉቱም በቁጥር ብዙ የሚሆኑ ቀሳውስት ግን አካላዊ ጥቃቱ በተወሰነ ደረጃ ሊኖር እንደሚችል ነገር ግን ሴቶቹ (ብዙ ጊዜ የሚጠቁት እነርሱ ናቸው) ዝም እንደሚሉና ለፖሊስ ወይም ለፍርድ ቤት ስለ ጥቃቱ አቤቱታ እንደማያቀርቡ ያምናሉ፡፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱት ማኅበረሰቡን በማገልገል የ40 ዓመት ልምድ ያላቸው አንድ ቄስ ይሄንን ጉዳይ በተከታዩ ምሳሌ አብራርተዋል፡ ‹‹አብዛኞቹ ሴቶች በቤት ውስጥ ያለን ጥቃት እና ችግር ልክ በእርግዝናቸው ወቅት ልጃቸውን በውስጣቸው እንደሚይዙት ይይዙታል፡፡ በውስጣቸው ይይዙታል እንጂ ለማንም አይናገሩም፡፡››[102]

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ቀሳውስት በማኅበረሰቡ ውስጥ ላላው የጋብቻ ችግር የተለያዩ ምክንያቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ድህነት እና የገንዘብ እጥረት የሚያስከትለው ጭንቀት፣ በመጠጥ ወይም በሌላ ምክንያት የሚመጣ የአንዳንድ ባሎች መጥፎ ጠባይ እና በጥንዶቹ መካከል የሚኖር አለመስማማት ወይም ፍቅር መጥፋት በተደጋጋሚ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ ይገኙባቸዋል። አንዳንዶች እንደሚያስቡት ጋብቻ በኃብት ላይ የተመሠረተ መሆኑ እየጨመረ መጥቷል ይሄም በጋብቻ ውስጥ ያለ ጥልን እና ፍቺን እያባባሰ ነው፡፡[103] ብዙ ቀሳውስት በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ችግሮችን ከ ‹ዘመናዊነት›፣ ቁስ ተኮር ከመሆን ጋርና አጋርን በመምረጥ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ነዋይ ተኮርነት ከመኖሩ ጋር አያይዘዋል፡፡ በስፋት ከሚስተዋለው ፍቺ ምክንያት ጋር በተያያዘ ቀሳውስቱ ምክንያት ብለው የሚያቀርቡትን ነገር ለማጣራት የተደረገው ጥረት እንደሚጠቁመው ከሆነ ምክንያቱን በተመለከተ በቀሳውስቱ መካከል ስምምነት የለም፡፡ በመስክ ሥራው ወቅት ለዶ/ር ኢስትራቲ የቅርብ አማካሪ የሆኑ አንድ መነኮስ እንደተናገሩት ዶ/ር ኢስትራቲ የነዚህን ችግሮች ምንጭ በአክሱም ከቀሳውስቱ ጋር ማጣራት እንደጀሩ ወዲያው ቀሳውስቱ ይሄ ጉዳይ የተነሣበት ስብሰባ በአክሱም አድርገው ነበር፡፡ ሰውየው ለዶክተሯ እንደነገሯቸው ከሆነ ተሳታፊዎቹ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ለሚስተዋለው ፍቺ በቂ መልስ ማግኘት ሳይችሉ ስብሰባው ያለ ስምምነት ተጠናቋል፡፡[104]

ቀሳውስት በጠቅላላው ጥል፣ ፍቺና መለያየትን እንደማይመክሩ ነው የተገለጸው፡፡ እንደ አንድ ቄስ ከሆነ የገጠር ቀሳውስት ሰዎች ባላቸው ነገር እንዲረኩ እና ደስተኛ ሆነው እንዲኖሩ ነገር ግን የሌላቸው ከሆኑ እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ እንዲጸልዩ ለመምከር ይጥራሉ፡፡[105] ሰዎች እርስ በእርስ በሰላም እንዲኖሩ እና ባሎችም ሚስቶቻቸውን እንዲወዱም ይመክራሉ፡፡ ከተጣሉ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደሌለ ያስጠነቅቋቸዋል፡፡ ስለዚህ መጣላት የለባቸውም፡፡ እንደ አስተምህሮአቸው ከሆነ ጥል ለባልና ለሚስት መጥፎ ስም የሚያተርፍላቸው ሲሆን በሁለቱ ጥንዶች ቤተሰቦችም መካከል የሚኖር ቀጣይ ጸብና ቂም ያተርፋል። በአንድ አጥቢያ ያለ መምህር እንዳለው ቤተክርስቲያን ፍቅር ለሰላማዊ የጋብቻ ሕይወት አስፈላጊ እንደሆነ እና በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ራስ ወዳድነት እንደሌለ ያም ማለት ባልና ሚስት የጋብቻ ሕይወትን ድካም በጋራ መሸከም እንደሚገባቸው ለሁሉም ታስተምራለች፡፡[106] ሁሉም ቀሳውስት እንደጠቀሱት በሰላማዊ መንገድ መኖርን ገንዘብ ለማድረግ እና በጋብቻቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት ጥንዶቹ ወጥ የሆነ የጸሎት ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እኒህ ትምህርቶች በቀጣዩ አስተያየት ተጠቃለዋል፡

> በቤተክርስቲያን የምናስተምረው ለሁሉ የሚሆን ትምህርት ነው፡፡ ካህኑ ስለ ጋብቻ የሚያስተምረው ቤት ለቤት ነው፡፡ መንግሥተ ሰማያት መግባት ከፈለጋችሁ ባልና ሚስት ስትሆኑ የአብርሃምን እና የሳራን መንገድ ተከተሉ፣ አንድ ለአንድ ተወሰኑ፣ ጹሙ በዓላትን አክብሩ ብሎ ያስተምራል፡፡ ካህኑ የሚናገረው የእግዚአብሔርን ሕግ

[102] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡
[103] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[104] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መነኩሴ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ የካቲት 28፣ 2009፡፡.
[105] በጣቢያ 4 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ጥር 29፣ 2009፡፡
[106] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡

ነው። ይሄ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፤ የአብርሃምን መንገድ መከተል ያስፈልጋል፡፡ የአብርሃምን መንገድ መከተል የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል ነው፡፡ ካህኑ የሚያስተምረው ሌላው ጉዳይ ደግሞ በጋብቻ ውስጥ መጣላት እንደማይገባ ነው፡፡ በመጣላት ውስጥ ምን ቅድስና አለ? መጣላት ምንም መልካም ነገር የለውም፡፡ ከተጣላችሁ ኃጢአት ነው ወደ እግዚአብሔር አያቀርባችሁም ይላቸዋል፡፡[107]

በእሑድ ቅዳሴ ጊዜ ቀሳውስት ስለ ጋብቻ እንደሚያስተምሩ ቢነገርም ለስድስት ወር ያህል በገጠር በነበረ ግምገማ የእሑድ ቅዳሴዎች ላይ ቀሳውስት በቀጥታ በአደባባይ ስለ ትዳር እና ስለ ጋብቻ ሕይወት ያነሡት ጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ አብዛኞቹ ቄሶች እንደ ንስሓ አባትነታቸው በዐቅማቸው የሚያስተምሩት የግለሰቦችን ቤቶች በሚጎበኙበት ጊዜ ሲሆን በየአጥቢያው ያሉ ሁሉም ቀሳውስት ግን አይደሉም፡፡[108] በተጨማሪም አብዛኞቹ ቤተክርስቲያናት የሚገኙት በተራራ ጫፍ ላይ ወይም በተራራ በተከበበ ቦታ እና ምቹ ባልሆነ ቦታ ስለሆነ በእግር ማዳረሱ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ ይሄም ምእመናን በቋሚነት የሚጎበኙበትን ወይም ቀሳውስት በአከባቢው ተራርቀው የሚገኙ ቤቶችን በቀላሉ የሚጎበኙበትን ዕድል አነስተኛ አድርጎታል፡፡ የገጠር ቀሳውስት እርሻቸውን ማረስ እንዳለባቸው እና አክሱም ከተማን ጨምሮ በሌሎች ክንውኖች ላይም በዐቅማቸው መገኘት እንዳለባቸው ይሄም የክርስትና ልጆቻቸውን የሚጎበኙበትን እና የኖላዊነት ሥራቸውን የሚሠሩበትን ጊዜ እንደሚቀንሰው መታወስም አለበት፡፡

## አስቸጋሪ የሆነና ጥቃት ያለበትን ጋብቻ ማስታረቅ

በጋብቻ ውስጥ በጥብዶቹ መካከል ችግሮች ሲፈጠሩ የጥንዶቹ ንስሓ አባቶች በቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ለመምከር የሚቻላቸውን ያደርጋሉ፡፡ ሁኔታዎችን በቶሎ የሚረዱ አባቶች ሴቶች በጋብቻ ውስጥ የሚገጥሟቸውን ችግሮች በተመለከተ ዝም እንዲሉ የሚያደርገውን ልማድም ከግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡ የተለመደው የማስታረቅ አካሄድ በአንድ ልምድ ባላቸው ቄስ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡

> አዎ መጀመርያ የምትሄደው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወይም ወደ ፍርድ ቤት ሳይሆን ወደ ቄሱ ነው፡፡ ለምሳሌ ባለፉት ዓመታት እንዲህ ዓይነት ችግር ተከስቷል ነገር ግን ሴቶቹ እስከ አሁን ድረስ ምንም ነገር አላደረጉም፡፡ አሁን ወደ ንስሓ አባቷ ስትሄድ የደረሰባትን ትነግረዋለች፡፡ የንስሓ አባቷም ወደ ቤታቸውም በመሄድ ባልየውን ያናግረዋል፤ ያጠፉችው ምን እንደሆነ እና ለምን ትቼሽ ሄዳለሁ እንዳላት ይጠይቁታል፡፡ ባሏ ይመታት እንደሆነ እና የደበቀችው ነገር ካለም ይጠይቃል፡፡ ከዛ ሁኔታውን ይመረምራል፡፡ ያጠፋችው ሚስትየው ከሆነች የሷ ጥፋት መሆኑን በመንገር ድጋሚ እንዲህ እንዳታደርግ ይነግራታል፡፡ ያጠፋው ባልየው ከሆነ ደግሞ ጥፋተኛ እርሱ እንጂ እርሷ አለመሆኗን ይነግረዋል፡፡ የጋብቻ ችግርን ካህኑ የሚፈታው በዚህ መልኩ ነው፡፡ ጸባቸው የሚቀጥል ከሆነ ግን ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲፈቱት ይመክራቸዋል፡፡[109]

ይሄ አስተያየት በጋብቻ ውስጥ የሚኖር ግጭትን በተመለከተ ቀሳውስት ይከተሉታል ስለሚባለው የማስታረቅ መንገድ የሚገልጽ ብቻ ሳይሆን የተወሰኑ ቀሳውስት ሴቶች በባሎቻቸው ጥቃት ደርሶባቸው እንደሆነ አስቀድመው መጠየቅ እስኪያደርሳቸው ድረስ ሚስትን መምታት ሊከሰት የሚችል እንደሆነ የጠቆመ ነው፡፡

እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች ጊዜ ቄሱ ችግር ያለበትንና ጥቃት ፈጻሚውን አካል ጥቃት መፈጸም አግባብ እንዳልሆነ ከጋብቻ የሚጠበቀው ምን እንደደሆነ በማስተማር ይመክራል፤ ያም ባልና ሚስት አብረው በሰላም መኖር እንዳለባቸው፣ አንድ አካል እንደሆኑና ሊጎዳት እንደማይገባ እና ፍቺ እንደማይፈቀድ ነው፡፡ ባል ሚስቱ ላይ ጥቃት በሚፈጽምበት ጊዜ ቄሱ ጥቃት ፈጻሚውን ፊት ለፊት ለማናገር ይሞክራል፤ ይሄ ድርጊት ክርስቲያናው እንዳልሆነም ይመክረዋል፡፡ ምንም ስንኳ የትኛውም ቄስ ጥንዶች እንዲፋቱ ባይመክርም እርቅ መምጣት የማይችል በሚመስልበት ሁኔታ እና ተደጋጋሚ ጭቅጭቅ ሰላም እንዳይኖር ካደረገ ቀሳውስቱ ጥንዶቹን ወደ ሽማግሌዎች ወይም ወደ ፍርድ ቤት መላክ ግድ ይሆንባቸዋል እነዚህም ብዙውን ጊዜ ጥንዶቹን ወደ ማፋታት ይሄዳሉ፡፡ ሽማግሌዎች ሁል ጊዜ የማኅበረሰቡ ማእካለውያን ሲሆኑ ጥንዶቹን ለማስታረቅ ይሞክራሉ፡፡ ሁለቱ

[107] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡

[108] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡

[109] ከቄስ እና ከቤተክርስቲያ መምህር ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፤ መጋት 24፣ 2009፡፡

የማይታረቁ ከሆነ ፍቺው በአግባቡ የሚከናወንበትና ንብረት በጥንዶቹ መካከል የሚከፋፈልበት ሂደቶች ላይ ይስማማሉ፡፡ ይሄም በቀጣዩ አስተያየት ተብራርቷል፡

> እንዲፋቱ አልነግራቸውም፡፡ ጋብቻቸውን ላድን እየሞከርኩ መሆኑን ነው የምነግራቸው እንጂ እንዲፋቱ አልመክራቸውም፡፡ ሕጉ አይፈቅድም፡፡ ለቃል ኪዳናችሁ ታማኝ መሆን አለባችሁ፡፡ መጽሐፉ የሚለው ‹‹አንዳችሁ በሌላችሁ ላይ ትዕግሥትን አድርጉ፣ አትስከሩ፣ ወደ ቤተክርስቲያን ሂዱ›› ነው ብዬ ነግራቸዋለሁ፡፡ ባልየው ግን አይሰማም፡፡ ሚስትየው ይፈታኛል ወይም ይገለኛል ትላለች፡፡ ከዛም ወደ ሽማግሌዎች እንዲሄዱና የሚሏቸውን እንዲሰሙ እመክራቸዋለሁ፡፡ ሽማግሌዎቹም ‹‹ሳይገድላት በፊት መፋታት አለባቸው›› በማለት ያለያዩአቸዋል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ግን ይሄ ትክክለኛ ሥራ አይደለም፡፡ የትኛውም መንፈሳዊ አባት ተፋቱ ብሎ አይመክርም፡፡ እንደዚህ የሚያዝ ሥርዓት በመጽሐፋችን የለም፡፡ መጽሐፉን በማምጣት ምን እንደሚል ይነግራቸዋል፣ ሥርዓቱን ይነግራቸዋል፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ያስተምራል፡፡ ቃል ኪዳን እንደተግባቡ እና ሊያከብሩት እንደሚገባ ይነግራቸዋል፡፡ ነገር ግን ሊያስራቸውና ሊያስገድዳቸው አይችልም፡፡[110]

የማስታረቁ ሂደት ግልጽ የሆኑ ሂደቶች በተዘረዘሩበት ሁኔታ፣ በጣም በተብራራ መልኩ ለተጠቂዎቹ ከደኅንነት ጋር  የተያያዙ አደጋዎች የሚያስነሣ ቢሆንም በአንድ ቄስ እንደሚከተለው ተገልጧል፡

> ቄሱ የንስሓ ልጆቹን የሚያስተምር፣ ንስሓቸውን የሚቀበል እና በደንብ የሚመክራቸው ጥሩና እውነተኛ ቄስ ከሆነ ወደ ጥንዶቹ ቤት ይሄዳል ወይም እንዲጠብቁት የሚፈልግበትን ቀንና ሰዓቱን በመንገር ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። ከዛም በሰጣቸው ቀጠሮ መሠረት ወደ ቤታቸው ይሄዳል፡፡ ባልየውንም ሚስትየው ላይ የሚፈጽመውን ድርጊት ለምን እንደሚፈጽም ይጠይቀዋል፡፡ ምክንያቱም እርሱ ያስተማራቸው ንስሓ እንዲገቡና ሥጋና ደሙን እንዲቀበሉ ነው፡፡ ይሄን በእውነት ካደረጉ ደግሞ ባልየው እንደ ውሻ ወደ ተፋው ወይም ተጸጽቶ ወደ ተወው ነገር መመለስ የለበትም፡፡ ነገር ግን ሥጋና ደሙን አንዴም ስንኳ ያልተቀበሉ እንደሆነ እና ባልየው ጥፋቱን አምኖ ‹‹አባቴ ይፍቱኝ እነዚህን ጥፋቶች አጥፍቻለሁ›› ካለ ቄሱ ንስሓው ይቀበለዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ጥፋቱን ቢክድና አስቸጋሪ ጸባይ ቢያሳይ ቄሱ ‹‹ጥፋትህን እንድታምን እና እንድትጸጸት የተወሰነ ጊዜ እሰጥሃለሁ›› ይለዋል፡፡ የሚሰጠው የሳምንታት ያህል ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዛ በድጋሚ ያናግረዋል፡፡ ጥፋቱን ካመነ ይቀጥላሉ፡፡ ጥፋቱን የማያምንና የማይጸጸት ከሆነ ግን ቄሱ ሦስት ሰዎችን ምስክር አድርጎ በማምጣት ጥፋቱን አምኖ ንስሓ እንዲገባ እና ሥጋና ደሙን እንዲቀበል ‹‹ብመክረው አልሰማ አለኝ›› ብሎ ይነግራቸዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ሰውዬው ጥፋቱን አምኖ አካሄዱን ለመቀየር ከተስማማ መልካም ይሆናል ካልሆነ ግን በቀጣዩ እሑድ ከቅዳሴ በኋላ በቀሳውስቱና በምእመናን ፊት ቄሱ ‹‹እገሌ የሚባለው ሰው እንዲህ ያለ ጥፋት አጥፍቷል፡፡ እኔም ከጥፋቱ እንዲመለስና ንስሓ እንዲገባ ስመክረው ነበረ ነገር ግን አልሰማኝም፡፡ ከዚህ በኋላ ለመንግሥተ ሰማይና ለቤተክርስቲያን ሰጥቼ ትቼዋለሁ ይሄ የመጨረሻ ቃሌ ነው፡፡›› ይላል፡፡[111]

ጥቃት ፈጻሚው መጥፎ ጸባዩን ለመቀየር ፈቃደኛ ካልሆነ ቄሱ ቤተሰቦቹ ሰውዬውን እንዲያናግሩት እና እንዲለወጥ ተጽእኖ እንዲያደርጉበት ሊመክርም ይችላል፡፡[112] ሌሎች ምስክርነቶች እንደጠቆሙት ከሆነ ደግሞ ቀሳውስት የጥቃት ፈጻሚውን ጸባይ ለመቀየር ጠንከር ያሉ አካሄዶችን ሊከተሉም ይችላሉ፡፡ አንድ ቄስ እንዳረጋገጡት የንስሓ አባቱን ምክር አልሰማ ያለና በመጥፎ ጸባዩ የሚቀጥል ሰው መጸጸቱን በአደባባይ እስኪገልጽ ድረስ ከቤተክርስቲያን ሕይወት ይገለላል፡፡[113] ጥፋተኛው ሰው አሁንም ከመንገዱ አልመለስም ካለ ቄሱ ንስሓ አባትነቱን ሊተው እንደሚችል ይነግረዋል፡፡ ቃለ መጠይቅ የተደረገለት አንድ ወንድ እንደሚያስበው ይሄ መንገድ አዋጪ ነው ምክንያቱም በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ ንስሓ አባት የሌለው ሰው መሆን የማይታሰብ ነው፡

> ሰውየው የማይስተካከል ከሆነ ቄሱ አብዝቶ ይጥራል፡፡ ሰውየው ግን በጥፋቱ የሚቀጥል ከሆነ ቄሱ የአከባቢው ሰዎች ሁሉ የሚሰበሰቡበትን የበዓል ጊዜ ወይም ሌላ አጋጣሚ በመጠቀም በሕዝብ ፊት በግልጽ ለዚህ ሰው የነበረውን የክህነት አገልገልቱን ማንሣቱን ይናገራል፡፡ በኛ ሃይማኖት እንደምታውቂው አንድ ሰው የንስሓ አባት

---

[110] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡

[111] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡

[112] ከቄስ እና ከቤተክርስቲያን መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡

[113] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009፡፡

> ሳይኖረው ለአንድ ሌሊት ስንኳ መቆየት አይችልም፤ ያልተለመደ ነው፡፡ ይሄኛው ቄስ ካባረረው በኋላ ሰውየው ሌላ ቄስ ጋር በመሄድ ‹‹ዛሬን አሳድረኝ›› (**አሕድሩኒ**) ብሎ ይለምነዋል፡፡ ለመለወጥ ፈቃደኛ ካልሆነ ሌላ ንስሓ አባት ማግኘት ከባድ ነው፡፡[114]

ነገር ግን ቀሳውስት ምክራቸውን ለማይቀበሉ አማኞች የንስሓ አባትነታቸውን ቢተዉም በርካታ ምስክርነቶች በቃለ መጠይቁ ወቅት እንደጠቆሙት ሰዎች ወይ ወደሌላ ቦታ ይሄዳሉ ወይም ድጋሚ ካገቡ በኋላ ወዲያው ሌላ የንስሓ አባት ይይዛሉ፡፡ በተጨማሪም ቀሳውስቱ ራሳቸው አንድ ሰው ከቤተክርስቲያን ሕግ ውጪ የራሱን ፈቃድ ቢከተል ብዙም አያስጨንቁትም፡፡ አንድ ቄስ የሚከተለውን ታዝበዋል፡ ‹‹ቤተክርስቲያን ለካህኑ የምትነግረው ሰዎች ካልሰሙት እንዲተዋቸው ነው፡፡››[115] ከራሷ ጋብቻ ተሞክሮ አንድ ቄስ በጋብቻዋ ውስጥ የነበረ ችግርን ያዩበትን ሁኔታ በተመለከተ አንዲት ሴት የተናገረችው ይሄንን በደንብ ያብራራል፡

> የንስሓ አባቱ ያሉት ‹‹አትፋቱ፣ እርስ በእርስ ታረቁ እና ጋብቻቹ እንዲሰምር አድርጉ›› ነው፤ ነገር ግን ባልየው ለቄሱ ‹‹አንተ የምትለውን አላደርገውም›› አላቸው፡፡ የንስሓ አባቱም መልሰው ‹‹እኔ ከነገርኩህ ሌላ ማድረግ ከፈለግክ መልካም ነው የምትፈልገውን ማድረግ ትችላለህ›› አሉት፡፡ ከዛም ፈቃዳቸውን ሰጡ፡፡[116]

እኒህ ዐረፍተ ነገሮች መሠረታዊ የሆነውን የዚህን ትውፊት የነገረ መለኮት አድማስ ያም አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ መከተል ያለበት በቀሳውስት አስገዳጅነት ሳይሆን በነጻነት በሕሊናው እየተመራ መሆን እንዳለበት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አንድ የገጠር ቄስም እንዲህ አብራርተውታል፡

> እምነታችን የሚያስተምረው ግን እግዚአብሔርን መስማት ካልፈለግክ የራስህ ምርጫ እንደሆነ ነው (**ንርእስኻ አይትብል**)፡፡ ስለዚህ ቀሳውስቱ ሰዎች የሚሏቸውን ይቀበላሉ በዚህም አይፈርዱባቸውም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው እንደዛ ነውና (‹‹ላንተ የተባለውን ውሰድ››) ፡፡ ለምሳሌ ራሴን የምወቅስበት ሕሊና ከሌለኝ ቀሳውስቱን ላታላቸው እችላለሁ፡፡ ሕሊና ከሌለኝ ላታልላቸው እችላለሁ፡፡[117]

ይሄ አስተያየት ቀደም ብሎ ቅዱስ ጋብቻን በተመለከተ ቀሳውስት ጥንዶቹ ደናግላን መሆናቸውን ከተናገሩ እንደሚያምኗቸው ለተነሣው ጉዳይም ጠቃሚ ነው፡፡ እነዚህ ገለጻዎች እንደሚያሳዩት ምንም ስንኳ ቀሳውስት የንስሓ ልጆቻቸው መሻሻል ያሳዩ ዘንድ በግል ወይም በሕዝብ ፊት ቅጣት ሊያስተላልፉ ቢችሉም እምነት ግን ግለሰቦች በራሳቸው መርጠው የእግዚአብሔርን መንገድ የሚከተሉበት ስለሆነና ለድርጊቶቻቸው ራሳቸው ግለሰቦቹ የሚጠየቁበት ስለሆነ ቀሳውስቱ በዚህ ጉዳይ ግፊት ሊያሳድሩ የሚችሉበት ነገረ መለኮታዊ መሠረት የላቸውም፡፡

በጋብቻ ውስጥ ጥቃት ወይም ጉዳት የደረሰበትን አካል በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ መጀመርያ ላይ የቀረበው የአንድ ጉዳይ ጥናት እንዳመለከተው ቀሳውስት በአስቸጋሪ ጋብቻ ውስጥ ያሉ ሴቶች ትእግሥት እዲኖራቸው ይመክራሉ፡፡ ይሄም በስፋት ከሚነገረው ሴቶች ጥቃትን መቋቋም አለባቸው ከሚለው ልማድ ጋር ሊያያዝ የሚችል ነው፡፡ ሌሎች ምስክርነቶች እንዳመለከቱት ደግሞ ቀሳውስት ሴቶችን ብቻ ለይተው አይደለም በጋብቻቸው ላይ ትእግሥት እንዲያደርጉ የሚገፋፉት፡፡ ለምሳሌ አንድ ቄስ እንዳብራሩት በባልየው የተፈጠረ ችግር በትዳሩ ውስጥ ሲያጋጥም ሴቷ በትዳሯ መቆየት ባትፈልግ አትወቀስም ወይም ጥፋተኝነት እንዲሰማት አትደረግም፡፡ የቄሱ አስተያየት የሚከተለው ነው፡

> አዎ ፍቺ አይፈቀድም፡፡ ጥፋተኛው ባልየው ከሆነ ሚስትየው ምንም ማድረግ አትችልም፡፡ ችግሩን ያመጣችው እርሷ አይደለችም፡፡ ባሕሉ ግን ገና አልተቀየረም፡፡ ባልየው የወደደውን ማድረግና እንደወደደው መኖር ይችላል ሚስትየው ግን አትችልም፡፡ ይሄንን ሁኔታ ለመቀየር ጥረት ይጠይቃል፡፡ ፍቺው ደግሞ ራሷ ላይ ሌላ ኃጢአት መጨመር ነውና ልክ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለባልየው ጥፋተኛው እርሱ እንደሆነ፣ መጥፎ ጸባይ እያሳየ ያለው እርሱ

[114] ከወንድ ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[115] ከቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡
[116] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤መጋቢት 3፣ 2009፡፡
[117] ከወንድ ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡

> እንደሆነ እና ችግሮቹ ሁሉ እየተከሰቱ ያሉት በእርሱ ምክንያት እንደሆነ እንነግረዋለን፡፡ ከዚህ መንገዱ እንዲመለስም እንመክረዋለን፡፡[118]

ይሄ አስተያየት የተሰጠው አንድ ባልየው ሕጋዊ ሚስቱን ትቶ የሄደበትን ጋብቻ በተመለከተ ነው፡፡ ቄሱ የባልየውን ቤተሰብ በማሳተፍ፣ እርሱን ለብቻው በማዋራትና የሠራው ሥራ ጥፋት መሆኑን በማሳየት የራሳቸውን ጥረት አድርገዋል፡፡ ቄሱ እንዳሉት በእንዲህ ዓይነት ጊዜ ሴቷ ተጠያቂ ልትደረግ አትችልም፣ ይሄንን ዓይነት አስቸጋሪ ጸባይም እንድትቋቋም አትጠየቅም፡፡ ሌሎች ምስክርነቶች እንዳሳዩት ደግሞ ቀሳውስት ትእግሥት እንዲኖራት ከመምከር ባለፈ የተጨነቁ ሴቶችንና ሕፃናትን ለመርዳት ቁሳዊ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ አንድ ሴት የሚከተለውን መስክራለች፡

> አዎ አንድ የንስሓ አባት ነበር የነበረን፡፡ ነገር ግን ባሌ ትቶኝ ሄደ፡፡ የንስሓ አባቴ እንዲመለስ ነገሩት ነገር ግን አልሰማቸውም፡፡ ካልፈለገ ማስገደድ አይቻልምና የንስሓ አባታችን ምንም ማድረግ አልቻሉም፡፡ ነገረ ግን፡ [‹አትጨነቂ እኔ አለሁልሽ ከኔ ጋር ትቆዩአለሽ]› አሉኝ፡፡ አሁን ከንስሓ አባቴና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ነው ያለሁት፡ ፡[119]

አብዛኞቹ ሴቶች ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ሕይወት ባሎቻቸው ላይ የተደገፉ ከመሆናቸው አንጻር ይሄ ድርጊት መወደስ ያለበት ነው፡፡ የባልየው መለየት እና ለልጅ ተቆራጭ ለማድረግ አለመስማማቱ ሚስትየውን እና ልጆቿን ችግር ላይ ጥሏቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ሴቷ በሕይወት ያሉ ሊያግዟት የሚችሉ ሰዎች ከሌሏት እና ሥራ ልትቀጠር የምትችልበት የትምህርት ዝግጁነት ከሌላት የባሰ ችግር ውስጥ ሊከታት ይችላል፡፡ ደሞዝ ከሌላት የቤት ኪራይ መክፈል ስለማትችል ከቤቱ ያስወጧታል፡፡ ምናልባት ከላይ ምስክርነት የሰጠችው ሴት ባሏ ትቷት በሄደ ጊዜ ራሷን ያገኘችው እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ልትንከባከባቸው የሚገቡ ስድስት ልጆች አሏት ግን ምንም ቋሚ ገቢ የላትም፡፡ ስለዚህም ቄሱ ከራሳቸው ቤተሰብ ጋር እንድትኖር ጋብዘዋታል፡፡

እኒህ ምስክርነቶች ጉዳዩ የሚታይበትን የእይታ አድማስ የሚያሰፉት ሲሆን ምንም ስንኳ አንዳንድ ቀሳውስት ጋብቻው ይጠበቅ ዘንድ ቢመክሩም እና በዚህም ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች ቢጎዱም ቀሳውስቱ ሁሌ ጋብቻን በማስጠበቅ ላይ ብቻ አያተኩሩም፤ በወንዶች አስቸጋሪ ጠባይ ምክንያት ሴቶች ረዳት አልባ እንደሚሆኑ በመረዳት መጀመርያ ለሴቶቹ ደኅና መሆን ቅድሚያ ይሰጣሉ።

ሴቶቹ ምንም ስንኳ ሃይማኖታዊ የሆነውን ምክር ዋጋ ቢሰጡትም የቀሳውስቱን ምክር ያለ ትችት የማይተገብሩበት አጋጣሚ አለ፡ ፡[120] ቀሳውስቱ ጋብቻ ሰላማዊና የዕድሜ ልክ መሆን እንዳለበት መሆኑ ላይ ማተኮራቸው ሴቷ ላይ ተጨማሪ ግፊት ሊያሳድር ይችላል፡፡ በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ ከባሏ ጋር አለመጨቃጨቅ እና በጋብቻ ውስጥ ሁል ጊዜ ጸብን ማራቅ ከሴቷ የሚጠበቅ ነው፡ ፡ በዚህ ጊዜ ፍጹም ባልሆነው ትዳሯ ውስጥ ትዕግሥት እንድታሳይ የተመከረች ሴት ያለችበትን ሁኔታ ለማስተካከል ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ላታደርግ ትችላለች፡፡ እንዲህ ዓይነት ምክር በትክክለኛው መሥፈርት ያም ጋብቻ በሁለቱም መፋቀርና መከባበር ላይ መመሥረት እንዳለበት ካልተነገረ በሴቶቹ ዘንድ የተሰሚነት ማጣት መጥፎ ዝንባሌን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እዚህ የተገለጹት አብዛኞቹ ሁኔታዎች ችግር ያለባቸው ግን የግድ ጥቃት ፈጻሚ ያልሆኑ ወንዶችን ያካተተ ነው ነገር ግን አካላዊ ጥቃት ለሚስተዋልባቸው ሁኔታዎችም ተመሳሳይ የሆነ መንገድ መጠቀም የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡

## በአስቸጋሪ ወይም ጥቃት በሚፈጸምባቸው ትዳሮች የቀሳውስት ተሳትፎ ውሱንነት

በምእመናንና በቀሳውስት እንደተመሰከረው በጋብቻ ውሰጥ ጥቃት በሚኖርበት ጊዜ ልክ እንዳልሆነ ለመምከር ቀሳውስት ጣልቃ ቢገቡም አንዳንድ ምክንያቶች ግን የቀሳውስቱን የማስታረቅ ተልእኮ ውጤታማነት የሚቀንሱ ሲሆን ልብ የማይባሉ አደጋዎችንም ይፈጥራሉ፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ ጥያቄ በሚቀርብላቸው ጊዜ ሁሉም ቀሳውስት የጋብቻ ጉዳዮችን ለማየት ፈቃደኛ ቢሆኑም ብዙ ጊዜ ግን ይሄ ጉዳይ ጥቃት በደረሰበት አካል በቀጥታ አይነገርምና ሁሉም ቀሳውስት ጥቃቱ መፈጸም አለመፈጸሙን ላይረዱ ይችላሉ፡፡ ጥናቱ እንዳመለከተው ችግሩን በመረዳትና ሴቶቹ ጉዳዩን ምሥጢር የማድረግ ጠባይ እንዳላቸው በመገንዘብ አንዳንድ ቀሳውስት ሴቶቹ

---

[118] ከቄስ እና ከቤተክርስቲያን መምህር ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፤መጋቢት 24፣ 2009፡፡

[119] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 3፣ 2009፡፡

[120] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 17፣ 2009፡፡

በባሎቻቸው አካላዊ ጥቃት ደርሶባቸው ከሆነ ለማጣራት አስቀድመው ራሳቸው ይጠይቃሉ፤ ነገር ግን በማኅበረሰባቸው ውስጥ የጋብቻ ውስጥ ጥቃት የለም ብለው የሚያምኑ ጥቂት ቀሳውስትም ነበሩ፡፡ በርካታ ጥናቶች እንደጠቆሙት ቀሳውስት የጋብቻ ውስጥ ጥቃት ምልክቶችን በማስተዋል የተካኑ አይደሉም[121]፤ በዛም ላይ ጥቃት አድራሹ ጉዳዩን ለማቅለል ወይም በተወሰነ ጥፋቱ ጥቃት የተፈጸመበት አካል እንደሆነ ለማሳየት በሚያደርገው ነገር ወይም ይቅርታን ለማግኘት ብሎ በሚያሳየው የጸጸት ስሜት ሊታለሉ ይችላሉ፡፡[122]

በተጨማሪም በቀሳውስትም በምእመናንም የተገለጸው እንደሚጠቁመው ቀሳውስት የጥቃት ሰለባዎችን እና ጥቃት ፈጻሚዎችን በአግባቡ እና በልዩ ትኩረት የመረዳት የክህሎት ችግር ሳይኖርባቸው አይቀርም፤ ይሄም የጥቃት ሰለባዎችን ወይም ከጥቃት የተረፉትን በአስቸጋሪና ደኅንነት በማይሰማቸው ሁኔታ ውስጥ ሊከታቸው ይችላል፡፡ ምንም ስንኳ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አብዛኞቹ የገጠር ቀሳውስት ባል አካላዊ ጥቃት ማድረሱ ለሴቶች ያለውን አደጋ ከግምት በማስገባት ሴቶቹ ለፖሊስ ወይም ለፍርድ ቤት እንዲያመለክቱ ቢመክሩም በጠቅላላው ግን ቀሳውስት በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ጥቃት ፈጻሚውን ለመቀየር ይጥራሉ፡፡ ይሄኛው ጉዳዩን የመፍታት መንገድ የጥቃት ሰለባዎቹን ለለበለጠ የጥቃት አደጋ ሊያጋልጣቸው እንደሚችል ከግምት ገብቶ የማያውቅ ሲሆን ቀሳውስት ይሄ ዕድል ሊኖር እንደሚችል ስለማሰባቸው የሚጠቁም ነገር የለም፡፡ በሃይማኖታዊ ማኅበረሰብ የቤት ውስጥ ጥቃት ላይ የተሠሩ ጽሑፎች እንደሚጠቁሙት ቀሳውስት በጉዳዩ ዙሪያ የጥቃት ሰለባዎችን ወይም ጥቃት ፈጻሚዎችን ለብቻቸው ማናገር የለባቸውም፤ ነገር ግን ተጠቂው ላይ አዲስ የደኅንነት ስጋት ላለመፍጠር በጉዳዩ ላይ እውቀት ካላቸው አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመቀናጀት ወይም ለነሱ አሳልፎ በመስጠት መሆን አለበት፡፡[123] ቀሳውስት የጉዳዩን አስቸኳይነት በመገምገም፣ የጥቃት ሰለባውን መከራ ከግምት ውስጥ በማስገባት መንፈሳዊ ድጋፍ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ተጠቂውን ግን የቤት ውስጥ ጥቃትን ወደሚመለከቱ ባለሙያወች መላክ አለባቸው፡፡ ጥቃት ፈጻሚውን በተመለከተ ጥቃት ፈጻሚውን በሚያበሳጭ እና ወደ ባሰ አስቸጋሪ ጠባይ በሚወስድ መንገድ ጉዳዩ ላይ ያለማስተዋል ጣልቃ ባለመግባት መንፈሳዊ ምክር ብቻ ነው መስጠት ያለባቸው፡፡ በገጠሩ ማኅበረሰብ ውስጥ የቀሳውስቱ ዋነኛ ሚና እንዲህ ቢገለጽም ለቀሳውስት ግን ጣልቃ አለመግባት ከባድ ነው፤ በተለይም የቤት ውስጥ ጥቃትን የሚመለከት የተደራጀ አካልን ለማግኘት ዕድሉ በሌላቸው በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ የበለጠ ከባድ ነው፡፡ ይሄ ቀሳውስት ተጠቂዎችንና ጥቃት ፈጻሚዎችን የሚረዱበትን ሥነ ልቦና እና እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን ለመቅረፍ ሲሞክሩ ሊከተል የሚችለውን የደኅንነት አደጋ ለመቅረፍ በአግባቡ ሊመለከቱት የሚችሉበትን ዐቅም ማሻሻል አስቸኳይ እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡

በተመሳሳይም ቀሳውስት ብዙ ጊዜ የጋብቻ ችግሮችን የሚያስከትሉትን ምክንያቶች ለምሳሌ ድህነትን እና የገንዘብ ማጣት የሚያስከትለው ጭንቀትን ቢያውቋቸውም ብሎም አንዳንድ ችግሮች ሥነልቦናዊ መነሻ እንዳላቸው ቢያስተውሉም አሁንም ይሄንን ውስብስብ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ ነው ጥቃት ፈጻሚዎችን ለመለወጥ የሚጥሩት፡፡ አስቸጋሪ የሆኑ ወይም ነውጠኛ ግለሰቦች ለመለወጥ እንቢ ቢሉ ብዙ ጊዜ ይሄ ሁኔታ ከመጥፎ ጠባያቸው ወይም አመለካከታቸው የመነጨ እንደሆነ ነው የሚወሰደው፡፡ ለምሳሌ አንድ ቄስ እንዲህ ብሏል፡ ‹‹ቅጣት ትሰጣቸዋለህ፡፡ በእግዚአብሔር ቤት ቅጣት አለ፡፡ ይቀጣሉ ነገር ግን መልሰው ያደርጉታል፡፡ ከዛም ልማድ ይሆንባቸዋል፡፡››[124] በብዙ አጋጣሚዎች ቀሳውስት ጥቃት በሚፈጽሙ ባሎች ላይ በጠባያቸው ምክንያት መንፈሳዊ ቅጣት ይጥላሉ፤ የዚህ ኃጢአታቸው ውጤት ምን እንደሚሆን በመንገርም ያስጠነቅቋቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ቅጣት ለረዥም ጊዜ መጾምን፣ ራስን መቅጣትን ወይም ምጽዋት መስጠትን ያካትታል፡፡ ሌላው ርምጃ ደግሞ በአንድ ቄስ መልስ እንዲህ ተብራርቷል፡

---

[121] A. J. Johnson, ed. *Religion and Men's Violence Against Women* (Springer: New York, 2015), 5.

[122] C. Kilmartin, "Men's Violence Against Women: An Overview," in *Religion and Men's Violence Against Women*, ed. A. J. Johnson (Springer: New York, 2015), 17; N. Nason-Clark, B. Fisher-Townsend, C. Holtmann and S. McMullin, *Religion and Intimate Partner Violence: Understanding the Challenges and Proposing Solutions* (New York: Oxford University Press, 2018), 67.

[123] Johnson, *Religion and Men's Violence Against Women*, 5; Nason-Clark et. al., *Religion and Intimate Partner Violence*, 17, 82.

[124] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009

ለምሳሌ አንድ ወንድ የሌላ ወንድን ሚስት ቢያገባ ንስሐ በሚገባ ጊዜ ያለ ፍራሽ ለአንድ ዓመት መሬት ላይ እዲተኛ ይደረጋል፤ ምግብን በተመለከተ ደግሞ ቀኖና ላይ ያለ ሰው ከፋሲካ እሑድ በቀር ዋና ዋና በሚባሉ በዓላትን ሳይቀር ረቡዕ እና ዓርብን ጨምሮ ይጾማል፡፡[125]

እነዚህ እርምጃዎች የጸባይ ለውጥ በማምጣት ረገድ ሁል ጊዜ ውጤታማ አይደሉም ይሄም በአንዳንድ ተሳታፊዎች ቀሳውስት በሚጠቀሙት የፍርጃ ቋንቋ ምክንያት መሆኑ ተወስቷል፡፡ አንድ ቄስ እንዳሉት፡ ‹‹የንስሐ አባት ሁል ጊዜ ይሄን ወይም ያን አድርግ ይላል፡፡ እንዲህ የሚለው ትዳሩ ውስጥ ረብሻ እንዳይፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ሰዎች ስትገሥጻቸው አይወዱም፡፡››[126] ቀሳውስት የሚወስዱት የቅጣት ርምጃ ሰዎችን ከማነቃቃት አንጻር ተቃራኒ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል እኚህ ቄስ ይገነዘባሉ ፤ በተለይ ወንዶችን ጸባያቸውን እንዲቀይሩ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ የቄሱ አስተያየት ቀሳውስት ፍርጃን በመቀነስ የጥቃት ፈጻሚ ሰዎችን ሐላፊነት የመሰማት ሁኔታ የሚያግዝ አማራጭ መንገድ መጠቀም እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው፡፡

ሌላው ቀሳውስቱ በአግባቡ ያልተረዱት የሚመስሉት ነገር ወንዶችና ሴቶች ከሃይማኖታቸው (እምነታቸው) ጋር ያላቸው ቁርኝት የተለያየ መሆኑን ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ልምምድ እንደ ግለሰቡ ጾታ የሚለያይ ነው፤ በዋነኝነትም በማኅበራዊ-ባሕላዊ ዐውድ እና ወንዶችና ሴቶች የንብረት ይዞታን በተመለከተ በማኅበረሰባቸው ውስጥ በሚገጥማቸው ነገር የሚበየን ሲሆን የጋብቻ ሕይወት ላይም የራሱ አንድምታ አለው፡፡ ስለዚህ በአስቸጋሪ ትዳር ውስጥ ላሉ ለአብዛኞቹ ሴቶች እምነት እርግጠኛ ያለመሆን እና የመከፋት ስሜትን የሚቀንስ ሆኖ ሲያገለግል ለአንዳንድ ወንዶች ግን ኢ-ሞራላዊ እንደሆኑ ከሚቆጠሩ ወይም ኃጢአት ከሆኑ ለምሳሌ ከዝሙት እና ሚስትን ከመተው ከመሳሰሉ ድርጊቶች ለመከልከል የሚያገለግል ነው፡፡ በጋብቻ ውስጥ ጻድቅ ሆኖ ስለመኖር የሚገለጽበት ቋንቋም ቀሳውስት ሲጠቀሙት ወንዶች ላይ የተለየ ተጽእኖ ያለው ይመስላል፡፡ ስለዚህ በጋብቻ ውስጥ ጥቃት መፈጸም ፍትሐዊ እንዳልሆነ እና ኃጢአት እንደሆነ መናገር እና ወንዶች ጻድቅ እና ለሌሎች ምሳሌ እንዲሆኑ ማበረታታት መልካም የሆነ የጸባይ ለውጥ ለማምጣት አግባብ ያለው አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡

በመጨረሻም ሰዎች ሁሉ ለቀሳውስቱ ትምህርት ዕኩል ምላሽ እንደማይሰጡ ወይም ትምህርቶቻቸውን በዕኩል ደረጃ በዕላት ተዕለት ሕይወታቸው እንደማይተገብሩት ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በርካታ ቀሳውስት እንደገለጹት ምእመናን የቀሳውስቱን ትምህርት ለመስማት እና ጎጂ የሆኑ ኢ-ክርስቲያናዊ ጠባዮቻቸውን ለመቀየር ከፍተኛ ዳተኝነት እያሳዩ ነው፡፡ የጋብቻ ጉዳዮችን ከመሸምገል አንጻር የቀሳውስቱን ተሳትፎ ውጤት ጉዳትና ጥቅሙን ለማመዛዘን እያንዳንዱ ምእመን ከቀሳውስቱ ለእነሱ የተላለፈውን መልእክት የመቀበል እና ትምህርቶቹን በጋብቻ ሕይወቱ ላይ የመተግበር ብቃት እና ፍላጎት ላይ የሚወሰን መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡

## የቀሳውስት መንፈሳዊ ሕይወት እና ከባሕል ጋር ያለው ቁርኝት

አንዳንድ ቄሶች ራሳቸው ከሚስቶቻቸው ጋር በሰላም የሚኖሩ አለመሆናቸው የኖላዊነት ሥራቸውን ውጤታማነት የቀነሰው ሲሆን ይሄም ወሳኝ ወደሆነውና የቀሳውስትን መንፈሳዊ ሕይወት እና ምእመናን ላይ ያለውን ተጽእኖ ወደሚመለከተው ርእስ ይመራናል።

የነገረ መለኮት መምህራን፣ መነኮሳትና ቀሳውስት ያለ ልዩነት እንዳመኑት ቀሳውስቱ ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ቃል ቢያስተምሩም እነርሱ ግን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው አይተገብሩትም፡፡ አንድ የቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ መምህር እንዳስተዋሉት ቀሳውስት በማኅበረሰቡ ውስጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ናቸው ግን ሁሌ ሃይማኖቱ በሚያዘው መልኩ በትክክለኛው መንገድ አይኖሩም፡፡[127] እርሳቸው እንደሚያስቡት አንዳንድ ቄሶች ሙሰኛና ገንዘብ ወዳድ ሲሆኑ ይሄንን ጸባያቸውን በቀላሉ በምክንያት ይከላከሉታል፡፡ በሌላ በኩል በገጠሩ ማኅበረሰብ በመስክ ሥራው ወቅት ያጋጠሙን አንድ መነኩሴ እንደተናገሩት ቀሳውስት ጥቂት የሆነ የትርጓሜ ትምህርት ነው ያላቸው እናም ሕዝቡን በበቂ ሁኔታ አያስተምሩትም፡፡ እርሳቸው እንደተናገሩት አንዳንድ ቀሳውስት በኃጢአት ሥራ ይሳተፋሉ ለዚህም በቅርቡ በጎበኙት አንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተወሰኑ ቄሶች ጠላ (ስዋ) ሲጠጡ

---

[125] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009.
[126] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣2009.
[127] በቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ጥር 9፣ 2009፡፡

መመልከታቸውን እንደምሳሌ አንሥተዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ቄሶች ለሌላው የማኅበረሰቡ ክፍል መጥፎ ምሳሌ እንደሚሆኑ ተናግረዋል፡፡[128] ሌላም ቄስ እንዳሉት አብዛኞቹ ቄሶች ሕጉን ያውቁታል ሆኖም ግን መጥፎ ነገር ያደርጋሉ፡-

> ሕሊና ያለው ማንኛውም ቄስ ከቤተክርስቲያን ሕግ አይጻረርም፡፡ ነገር ግን ከቄስ ቄስ ልዩነቶች አሉ፡፡ አንዳንድ ቄሶች ገንዘብ ይቀበላሉ፤ ሁሉም ቄሶች መልካም ሰዎች አይደሉም፡፡ ሁሉንም ማለት አይደለም ነገር ግን አንዳንድ መጥፎ የሆኑ ቄሶች መኖራቸው እውነት ነው፡፡ ‹‹እኔ ዐዋቂ ነኝ፣ እኔ ጠንቋይ ነኝ፣ ይሄ መድኃኒት ነው›› ይላሉ፡፡ ማስተማር አይፈልጉም ነገር ግን የቤተክርስቲያን መሪዎች ሆነው እግዚአብሔር የማይወደውን ነገር ያደርጋሉ፡፡ ይሄን የመሰለ ነገር የለም ማለት አይቻልም፡፡[129]

የቤተክርስቲያን ሰዎች እና ጥንቆላ ያላቸው ግንኙነትም ምእመናን ከተናገሩት ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ በተለይ ደብተራዎች ያለ ልዩነት ሊባል በሚችል መልኩ ለገንዘብ ሲሉ ምትሐት የሚሠሩ ‹መጥፎ ሰዎች› ሲባሉ በወንዶችም በሴቶችም እጅጉን ይፈራሉ፡፡ አንዳንድ ቄሶችም መጥፎ ነገሮችን የሚያደርጉ ደብተራዎችን እንደሚያውቁ አምነዋል፡፡[130] አንድ የቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት መምህር የሚያውቀውን የአንድ ደብተራን ፈገግ የሚያሰኝ አጋጣሚ ይጠቅሳል፡፡ አንዴ ይሄ መምህር ደብተራውን እርሱ ለቤተክርስቲያንና ለተቸገሩ በማይሰጥበት ሁኔታ ከማኅበረሰቡ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ለምን እንሚያተኩር የጠየቀው ሲሆን የደብተራው መልስም ‹‹መጀመርያ እኔ ላግኝ ከዛ በኋላ እሰጣለሁ›› የሚል ነበር፡፡ ከዛም መምህሩ እንዲህ አሉኝ ‹‹ኢትዮጵያ እንዲህ ነው የምናደርገው፡፡ በቃል ትክክለኛውን ትምህርት እናስተምራለን በተግባር ግን ተቃራኒውን እናደርጋለን፡፡ ለምን ይሆን እንዲህ የምናደርገው?››[131] ሌላም ቄስ የሚከተለውን ብለዋል፡

> አዎ በቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ ነገር ግን ውጪ ሲወጡ ደግሞ ሌላ መጥፎ ነገር የሚያደርጉ ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ግን በከንቱ የሚደክሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ወደ በረሃ ወርጄ ደረቅ እንጨት ብለቅም ነገር ግን የተለቀመውን እንጨት የማስርበት ጠንካራ ገመድ ባይኖረኝ ከቆይታ በኋላ ላዬ ላይ ተበትኖ ይገድለኛል፡፡ ጠንካራው ገመድ ምንድነው? ጠንካራው ገመድ እውነት ነው፤ እውነተኛ ጸሎትና ቅዱስ ቁርባንነው፡፡ እነዚህ በምንሰደብ ጊዜ ራሳችንን ዝቅ እንድናደርግ፣ ገንዘብን እንድንጠላ እና እውነትን እንድንናገር አጥብቀው የሚይዙን ጠንካራ ገመዶች ናቸው፡፡ ያለ እነዚህ አንድ ሰው ጥሩ ቅኔ አዋቂ ቢሆን ወይም የቅዱስ ያሬድን ዜማ ማዜም ቢችል ከንቱ ነው፡፡ ሕይወቱን መለስ እያለ በመገምገም የማይመራ፣ ሚስትና ልጆቹን በሰላም የማያስተዳድር ሰው መምህር መሆን አይችልም፡፡ እምነታችንና መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያለውን ሰው በቤተክርስቲያን መምህር ማድረግን ይከለክሉናል፡፡ የግል ሕይወቴን፣ ሚስቴንና ልጆቼን በአግባቡ የምመራ ከሆነ ለማስተማር ልመረጥ እችላሉ፡፡ ነገር ግን እኔ ራሴ እንዴት እንደሚደረግ የማላውቀውንና የማላደርገውን ሌሎች እንዲፋቀሩና እርስ በእርሳቸው እንዲኖሩ እንዴት ላስተምር እችላለሁ? እንደዛ ዓይነት ሰው ከሆንኩ የማውቀው ብቸኛው ነገር ከሰዎች ጋር እንዴት መጨቃጨቅና መጣላት እንደምችል ብቻ ነው ማለት ነው፡፡[132]

በመጥፎ ጸባይ ምክንያት በራሳቸው ሕይወት እና ትዳር ላይ ችግር ያጋጠማቸው የቀሳውስት ጉዳዮችም በጥቂቱ ተነሥተዋል፡፡ አንዲት የገጠር ነዋሪ ሴት የሚከተለውን ታሪክ አካፍላለች፡

> ከሚስታቸው ጋር የተጣሉ አንድ ቄስ ነበሩ፡፡ በቤተክርስቲያን ያገለግላሉ ምሥጢራትም ይፈጽማሉ፡፡ በኋላ ላይ በሽማግሌ ተመክረው ወደ ትዳራቸው ተመልሰዋል፡፡ ነገር ግን እኚህ ቄስ ከባለቤታቸው ጋር ችግር ስለነበረባቸው መፋታትን ትክክለኛ አማራጭ አድርገው ወስደውት ነበር፡፡ ይሄን ያደረጉት ካህናት መፋታት የሚፈቀድላቸው

---

[128] በጣቢያ 1 ከሚገኙ መነኩሴ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤የካቲት 28፣ 2009፡፡
[129] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ ሰኔ 3፣ 2009፡፡
[130] ለምሳሌ በጣቢያ 1 ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[131] በቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ጥር 9፣ 2009፡፡
[132] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 28፣ 2009

ሆኖ አይደለም፡፡ አሁን እኒህ ቄስ ትዳርን መፍታት የሚገባ እንዳልሆነ ላስተምር ቢሉ ሕዝቡ በተመሳሳይ ነገር ይጠይቃቸዋል፡፡ ሕዝቡ ‹‹እርሶ ትክክል አላደረጉም፡፡ ትዳሮን መጠበቅ አልቻሉም፡፡ ተፋተዋል፡፡ ስለዚህ እርሶ ይሄን ማድረግ ሳይችሉ እንዴት እኔን አትፋታ ይሉኛል!›› ይሏቸዋል፡፡ እንዲህ በማለት ትምህርቱን ያልሰሙት ሰዎች አሉ፡፡[133]

ይሄ ታሪክ በንግግር ስለሆነ የሚተላለፈው ምናልባት ተጋኖ ወይም ተዛብቶ ሊሆን ይችላል ነገር ግን በምእመናን ዘንድ ቀሳውስት ሁሉ በጋብቻ ሕወታቸው ምሳሌ እንዳልሆኑ ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡ የቤተክርስቲያኗን ትምህርት በሕይወት የማይኖሩ ቀሳውስትም ተአማኒነታቸውን እንዳያጡ እንደሚሰጉም ያጠይቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህች ሴት ቀሳውስት በቀኖናው መሠረት መፍታት እንደማይፈቀድላቸው ከፈቱ ግን ከቤተክርስቲያን አገልግሎት እንደሚባረሩ ነገር ግን በኒህ ቄስ ጊዜ  ይሄ እንዳልተደረገ ቄሱም በዛው ቤተክርስቲያን እየሠሩ እንደሆነ ታውቃለች፡፡

ሴቷ የገለጸችው በአብዛኛው ያለውን እውነታ ከሆነ ከቤተክርስቲያኗ አስተምህሮ ጋር የማይስማማ ሲሆን ምእመናን የቄሶችን አስተምህሮ ወይም መንገድ ላለመቀበል እርግጠኝነት እንደሚሰማቸው የተናገረችው ገጠመኝ ያስረዳል ይሄም በአንድ ወንድ ምእመን አስተያየት እንዲህ ተገልጽዋል ‹‹አንዳንድ መጥፎ ቄሶች አሉ፡፡ ራሳቸው እንዲህ ሆነው ሳለ ሕዝቡን መርዳት እንዴት ይቻላቸዋል ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን፡፡ ነገር ግን አንዳንድ እጅግ መልካም ቄሶች አሉ፡፡››[134] እንዲህም ሆኖ ግን ምእመናን በቀሳውስቱ የግል ጉድለቶች ምክንያት ምንም ያክል ሊቀበሏቸው ባይፈቅዱም ስንኳ እንደተብራራው ከሆነ ቀሳውስቱ የሚያስተምሩት ግን የቤተክርስቲያኗን ትምህርት የሚያንጸባርቅ መሆኑ በጥብቅ ይታመናል፡፡ ይሄም የሚከተለውን በተናገረች ሴት አስተያየት ተንጸባርቋል ‹‹በጋብቻቸው ውስጥ ምን እንዳለ ማን ያውቃል፡፡ ነገር ግን የሚያስተምሩት የእግዚአብሔርን ቃል ስለሆነ ልክ ነው፤ ማስተማርም አለባቸው፡፡››[135]

ከነዚህ መጥፎ ምሳሌዎች ባሻገር ደግሞ አንዳንድ ቀሳውስት ወሳኝ የሆነውን ነገር በመተው በዓለማዊ ጉዳይ ተወጥረዋል በሚል ይተቻሉ፡፡ በቅዱስ ያሬድ የአብነት ትምህርት ቤት መምህር የሆኑ አንድ ሰው ይሄንን በምሳሌ እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡ አንድ ሴት የአለባበስ ሥርዓትን ሳታከብር ስትቀር ቀሳውስት ወይም ሌሎች የቤተክርስቲያን ሰዎች ያነጋግሯታል ይመክሯታልም ብለዋል፡፡ መምህሩ ምንም ስንኳ ከቅዱስ ጳውሎስ አስተምህሮ አንጻር ይሄንን ቢደግፉትም በገጠሩ ባሕል ሰዎችና ቄሶች ‹‹ከዋናው ነገር ይልቅ ለሥርዓት ይጨነቃሉ፡፡›› ብለዋል፡፡[136]

ቀሳውስት ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎችንና መንፈሳዊነትን በሕይወታቸው መተግበራቸውን ከፍ ባለ ደረጃ ልንረዳ የምንችለው መንፈሳዊ ማኅበራት ላይ በቋሚነት በመገኘት ነው፡፡ በገጠራማው የአክሱም አካባቢ በነዚህ ማኅበራት ጊዜ በምእመናን ዘንድ የተለመደው ጠላና (ስዋ) ዳቦ አዘጋጅቶ ለቡራኬ ማቅረብ ነው፡፡ ወደ ሃያ የሚጠጉ እንዲህ ያሉ ማኅበራትን በመታደም ደ/ር ኢስትራቲ በቀሳውስቱ ዘንድ ግልጽ የሆነ የመጠጥ ልማድ እንዳለ አስተውላለች፡፡ ይሄንንም በተለያዩ አጋጣሚዎች አጣርታለች፡፡ በአንድ አጋጣሚ በሕዝብ ማመላለሻ ከከተማ ወደ ገጠር ስትመለስ በተወሰነ የስካር ስሜት ከሚስተዋልባቸው አንድ ቄስ ጎን ተቀምጣ ነበር፡፡[137] ቄሱ የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው እንደሆነ በተጠየቁ ጊዜም  ከማኅበር እየተመለሱ እንደሆነ እና ጽዋ እንደጠጡ ተናገረዋል፡፡ በመቀጠልም ይሄ የኖላዊነት አገልግሎታቸው ላይ ጉዳት ያስከትላል ብለው ያስቡ እንደሆነ ተጠይቀው ነበር፡፡ በመጀመርያ ትንሽ ምግብ ብቻ እንደበሉና እና ቁመታቸው አጭር እንደሆነ ስለዚህም ጥቂት መጠጥ እንዳሰከራቸው እንጂ ብዙ እንዳልጠጡ በመናገር መጠጣታቸውን ለማስተባበል ሞከሩ፡፡ ነገር ግን ጥቂት ቆይተው ማኅበራት እና በቤተክርስቲያን

[133] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 7፣ 2009፡፡
[134] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 7፣ 2009፡፡
[135] ከሴት ምእመን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 19፣ 2009፡፡
[136] በቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከሚገኙ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ አክሱም፣ ሐምሌ 16፣ 2009፡፡
[137] ወደ ጣቢያ 1 በተደረገ ጉዞ ወቅት ከአንድ ቄስ ጋር በመኪና ውስጥ የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ግንቦት 6፣2009፡፡.

መጠጥ የሚቀርብባቸው በዓላት ሁሌ መኖራቸውን በጸጸት ስሜት የተናገሩ ሲሆን ይሄንን ልማድ ማስቀረት ለእርሳቸው የሚቻል አለመሆኑን በማዘን ተናግረዋል፡፡

በሌላ ቀን ከከተማ ወደ መንደር በታክሲ ስትመለስ ሁለት የሰከሩ ቄሶች አጋጥመዋት ነበር፡፡[138] በመንገድ ላይ በጣም ይጮሁና ይጫወቱ ነበር፡፡ መውረጃቸው ጋር ሲደርሱ ግን አንደኛው ቄስ አልወርድም በማለት እንደ ሕፃን አስቸገሩ፡፡ ሹፌሩን ስትጠይቀው የሰከሩ ቄሶች መሆናቸውን ያረጋገጠላት ሲሆን በሁኔታው እጅግ ማፈሩ ያስታውቅ ነበር፡፡ ዶ/ር ኢስትራቲ ይሄንን የመጠጥ ችግር መኖር በአክሱም ቤተክህነት ውስጥ ለሚሠሩ ሰዎች በተደጋጋሚ አንሥታላቸው የነበረ ሲሆን እነርሱም ምንም ማድረግ ባለመቻል በፈገግታ አሳልፈውታል፡፡ በአክሱም ከተማ ከሚገኙ ምእመናን ጋር በነበራት ውይይትም ቄሶች እንደሚጠጡ አብዛኞቹ መስክረዋል፡፡ አብዛኞቹ ሰዎች ቄሶቹን አይታዘቧቸውም፤ ይልቅስ ችግሩ እንዳለና እንደሚፈታ በማመን ያልፉታል፡፡ ብዙዎቹ ሰዎች በቄስ ፊት ምንም ነገር አይናገሩም ይሄም ቄሶቹን ከማክበር ነው፡፡

በሌላ ጊዜ ከ15 በላይ ቄሶች በተገኙበትና ከቅዳሴ መልስ ከቤተክርስቲያን ጀርባ ባለ ክፍል ውስጥ በተደረገ ማኅበር ላይ ተገኝታ ነበር፡፡[139] በልማዱ መሠረት ጽዋና እንጀራ ከቀረበ በኋላ ዶ/ር ኢስትራቲ እንዲቀላቀሉ ተጋበዙ፡፡ ዶ/ር ኢስትራቲ አልጠጣም በማለታቸው ግን ጥያቄ ያስነሣ ሲሆን ይሄም ቀሳውስቱ የመጠጣት ልማዳቸው ከኖላዊነት ተግባራቸው ጋር ስላለው ነገር በግልጽ የመጠየቅ ዕድሉን ፈጥሮ ነበር፡፡ ሁሉም ጠላ (ስዋ) እንደሚጠጡ የተናገሩ ሲሆን ይሄም በአብዛኛው ልምድ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ [140] ይሄ ድርጊት ከሃይማኖት አስተምህሮ ጋር እንደማይስማማ ቢሰማቸውም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ግን ማብራራት አልቻሉም ስለዚህም ዶ/ር ኢስትራቲ ዐሳባቸውን እንዲያጋሩ ተጋብዘው ነበር፡፡ እርሳቸውም ካህናት እንደመሆናቸው በመንፈሳዊው ሁኔታ መኖርን ማስቀደም እንዳለባቸውና የሥጋን ፍላጎትና ፍትወትን ተጽእኖ መቀነስ እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡ በዚህ መንገድ በክርስቶስ መኖርን ማሳካት እንደሚችሉ እና ለቤተክርስቲያን አባላት እጅጉን ጠቃሚ በሆነ መንገድ ምሥጢራትን መከወን እንደሚችሉ ተነሥቷል፡፡ ከዚህም በላይ የንስሐ ልጆቻቸው ምክር ፍለጋ ሊጎበኟቸው ቢመጡ ነገር ግን እነርሱ እየጠጡ ከሆነ በአግባቡ ሊመክሯቸው አይችሉም፡፡ ቀሳውስቱ በዚህ አመክንዮ ያመኑ መሰሉ፣ በዝምታና በማሰላሰል ተዋጡ፡፡ ይሄን ነገር እንዲህ በግልጽ የተወያዩበት ለመጀመርያ ጊዜ መሆኑ ግልጽ ነበር፡፡ ሲሰሙም በማስተዋልና መጸጸት በተመላበት ሁኔታ ይመስል ነበር ወዲያው ግን ወደ መጠጣቱ ተመለሱ፡፡ ይሄ የልማድን ተጽእኖ እና ከዚህ በምእመናንም በቀሳውስቱም በሰፋት ተቀባይነት ካገኘና ከሚተገበር ልማድ ራስን ማላቀቅ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ያለጥርጥር የሚያሳይ ነው፡፡

በከተማ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የነገረ መለኮት ሊቃውንት አብዛኞቹን የቀሳውስቱን ድክመቶች ያገናኙት ትክክለኛውን ትምህርት ካለመማር ጋር ወይም ሃይማኖቱን በአግባቡ ካለመረዳት ጋር ነው፡፡ ይሄን ዐሳብ አንድ መንደር ውስጥ ባለ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚሠራ የትምህርት ቤት መምህርም ይጋራዋል፡፡ እርሱ እንዳለው ምክንያቱ በካህናት ዘንድ የትክክለኛ ትምህርት እጥረት ሲሆን በአንዳንዶቹ ዘንድ ደግሞ የሃይማኖታዊ ንቃተ ሕሊና ድክመት ነው፡፡[141] ቀጥሎም እንዳብራራው አብዛኞቹ የትርጓሜ ትምህርት የላቸውም ስለዚህ ሌላውን ማኅበረሰብ ምሳሌ በመሆን ሊያስተምሩት አይችሉም፡፡ አንድ የነገረ መለኮት ሊቅ አንዳንድ ቀሳውስት ባሕልና ሃይማኖት መለየት የሚቸገሩ መሆኑን በተመለከተ የሚከተለውን ብሏል፡

> በአግባቡ ስላላስተማርናቸውና ባሕል ከእምነት አስተምህሮ በታች መሆን ስለነበረበት ነው፡፡ እንደ የሴት ልጅ ግርዛት ያሉ መጥፎ የሆኑ ባሕሎችን ማስወገድ የሚቻለው በትምህርት ብቻ ነው፡፡ ለዚህም የመጀመርያ እርምጃ የሚሆነው ስለ ትዳር እና መሰል ጉዳዮች ቀሳውስቱን ማስተማር ነው፡፡ በእርግጥ አሁን ላይ ቀድሞ ከነበረው የተወሰኑ መሻሻሎች አሉ፡፡[142]

[138] የመስክ ማስታወሻ፤ ግንቦት 6፣ 2009፡፡
[139] የመስክ ማስታወሻ፤ ሐምሌ 2፣ 2009፡፡
[140] በጣቢያ 2 ከሚገኙ ቄስ ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ ሐምሌ 2፣ 2009፡፡
[141] በጣቢያ 1 ከሚገኙ የቤተክርስቲያ መምህር ጋር የተደረገ ኢ-መደበኛ ውይይት፤ እሑድ ሰኔ 4፣ 2009፡፡
[142] ከቅዱስ ፍሬምናጦስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መቀሌ፣ ጥር 22፣ 2009

ሌሎች እንዳሉት ደግሞ እነዚህ ችግሮች የዓለማዊነት ተጽእኖ በከፍተኛ ደረጃ ባሕልን ከሃይማኖት እየለየ በመሆኑ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ አንድ የቤተክርስቲያን መምህር የሚከተለውን ብለዋል፡

> በማኅበረሰብ ውስጥ ሃይማኖት እና ባሕል ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ መጻሕፍትና እንደ መምህራን ግን አንድ ናቸው፡፡ ባሕላችን ሃይማኖታዊ ነው፤ ሃይማኖታችንም ባሕላችን ነው፡፡ አሁን ግን ባሕል የምንለው ሃይማኖት ከምንለው የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል በደንብ እንደተብራራው ሃይማኖት ከገዛ ሚስትህ ውጪ ወደ ሌላ ሴት እንዳትሄድ ይላል፡፡ ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ነገር ሁሉ ሃይማኖት አይደለም፡፡[143]

ምንም ስንኳ ይሄ ማብራሪያ በብዙዎች ተቀባይነት ቢኖረውም በአክሱም የተካሄደው ማጣራት ግን ውስብስ ገጽታን አመላክቷል፡ ፡ ልክ በጋብቻ ትምህርትና ተግባራዊነት ላይ እንደተጠቆመው የቀሳውስቱን ትምህርት ከማኅበራዊ ባሕላዊው ልማድ ጋር ጎን ለጎን ማስቀመጥ ችግሩ አንድ ብቻ ያም የባሕል ቅየጣ ወይም አብዛኞቹ በአዲስ አበባና በመቀሌ የሚገኙ የተማሩ የነገረ መለኮት ሊቃውንት እንደሚሉት የነገረ መለኮት ትምህርት ጉድለት ብቻ ላይሆን እንደሚችል ጥቆማ ይሰጣል፡፡ ቀሳውስቱ የሚያስተምሩት ከቤተክርስቲያኗ የአዋጅ አስተምህሮ የራቀ ባይሆንም ትምህርታቸው ሳይታወቅ ጎጂ የሆኑ ጎኖች ያሏቸው ባሕላዊ አስተሳሰቦችን አበረታትቶ መሆን አለመሆኑን ለመለየት ትክክለኛው ዐውድና ጥልቀት ግን የሚጎድለው ይመስላል፡፡ በተጨማሪም በተያያዥ ጉዳዮች ላይ በጣም ድርቅ ያለ አረዳድ ያላቸው አንዳንዶቹ ቀሳውስት በነገረ መለኮት ሰፊ ትምህርት ያላቸው ናቸው፡፡ ይሄ ትኩረትን በቤተክርስቲያኗ ወደሚሰጠው የትርጓሜ ትምህርት ጸባይ እና ልዩ ትኩረት በብሉይ ኪዳን ላይ ወደ ማድረጉ በዚህም ልማዳዊ ድርጊቶችን በማበረታታቱ ላይ  እና የሐዲስ ኪዳን የጋብቻ ነገረ መለኮት በአብዛኛው መዘንጋቱ ላይ እንድናተኩር ያደርገናል፡፡

ቀሳውስት ባሕል ተኮር በሆነ ልማድ ውስጥ ያደጉ ወንዶች ጭምር እንጂ ለሃይማኖታዊ ዓላማ ብቻ የሚታትሩ ተደርገው መታየት የለባቸውም፡፡ ምንም ስንኳ ‹የእግዚአብሔርን ቃል› ለመዋሐድ ራሳቸውን ከተራው ማኅበረሰብ የመለየትን አስፈላጊነት ቢገነዘቡትም በማኅበረሰቡ ውስጥ ለወንድ የሚሰጠውን ማኅበራዊ ቦታ ሙሉ በሙሉ ከራሳቸው አላስወገዱትም፡፡ እንደተገለጸው በጋብቻ ውስጥ ጥል በሚኖርበት ጊዜ የንስሓ አባቶች ጥፋተኛው ማን እንደሆነ ለመለየት ሁለቱንም ጥንዶች ያነጋግራሉ። የሚሰሙት ምክንያት እርስ በእርሱ የሚጣላ ወይም የተለያየ ሲሆን ግን ምን እንደሚሆን ወይም እንደሚደረግ ተነሥቶ አያውቅም። ጋብቻን በተመለከተ አብዛኞቹ ቀሳውስት ባሕል ተጽእኖ ያደረገበት አረዳድ እንዳላቸው በመመልከት እና ደግሞም እነርሱም ባል እንደመሆናቸው እና በራሳቸው ትዳር ውስጥ ፈተና ስለሚገጥማቸው አንዳንድ ቀሳውስት ለወንዱ የማድላት ነገር ሊያሳዩ ይችላሉ።

በተወሰኑ መመዘኛዎች ውስጥ በመኖር በምእመናን ዘንድ ተአማኒነትን የማግኘትን እና በአከባቢው ሃይማኖታዊ ትውፊት በመኖር የመታወቅን ግፊትም ሙሉ በሙሉ ሊገፉት አይችሉም፡፡ ይሄ ዐሳብ በደንብ የተብራራው ሴቷ ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ባሏን ለምን እንቢ ልትለው እንደምትችል ካልገባቸው ቄስ ጋር በነበረ ውይይት ነው፡፡ ቄሱ ባልና ሚስት አንድ አካል መሆናቸውን አጽንኦት መስጠታቸው ሚስት በገዛ ገላዋ ላይ ሙብት የላትም ባልም በገዛ ገላው ላይ ሙብት የለውም፤ አንዳቸው ለሌላቸው ሙብቱን በመስጠት አንዳቸው የአንዳቸው አገልጋይ ይሆናሉ እንጂ፡፡ በዚህም አንድ ይሆናሉ በሚለው ትምህርት የሚቃኝ ነው፡፡ ቄሱ ይሄ መስጣጣት የተመሠረተበት ኅቡእ የሆነው መልእክት ያም የጋራ ፍቅር፣ የራስን ፍላጎት አሳልፎ መስጠት እና ለራስ ጥቅም አለማሰብ አልታሰባቸውም፡፡ ልክ ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለው ራስ ወዳድነት በሌለበት መልኩ ባል ሚስቱን በእውነት የሚወዳት ከሆነ የሷን ደኅና መሆን እና ፍላጎት ከሱ የፍትወት ፍላጎት (ከራስ ወዳድነት) ያስበልጣል ምክንያቱም በሁሉ ነገር እርሷን ማስደሰት ስለሚፈልግ እና ደስተኛ ሆና ሊያያት ስለሚፈልግ ነው፡፡ ይሄ አስተሳሰብ በቄሱም ውስጥ ባለውና ወንድ በሚገንበት በሀገረኛው ባሕል ውስጥ የሚረዳው የሌለ ይመስላል፡፡

በገጠሩ ማኅበረሰብ ውስጥ ስላሉ ጾታዊ ጉዳዮች ስንወያይ አንድ የነገረ መለኮት ሊቅ ይሄንን እውነታ ጠንከር ያለ ቋንቋን በመጠቀም በግልጽ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡

> በቤተክርስቲያናችን የኖላዊነት መንገድ መበየን አለበት፡፡ የኛ ማኅበረሰብ ወንድ የሚገንበት ማኅበረሰብ ነው፡፡ ቀሳውስትም ይሄንን በትምህርት እያረጋገጡ አስቀጥለዋል፡፡ አብዛኞቹ ቀሳውስት በነገረ መለኮት ትምህርት

[143] በጣቢያ 1 ከሚገኙ ቄስና የቤተክርስቲያን መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡

ሥልጠና የሌላቸው ናቸው፡፡ ሥልጠናው ቢኖራቸውም ግን ልማዳዊ አሠራራቸውን አይቀይሩም ምክንያቱም መናፍቅ ስለሚያስመስላቸውና በተሐድሶ ስለሚያስጠረጥራቸው ነው፡፡ በጾታ እኩልነት የሚያምኑ ቀሳውስት ስንኳ በተሐድሶ ስለሚያስጠረጥራቸው ይሄንን ልማድ አይቃወሙትም፡፡ የበዛ አለመተማመን እና ጥርጣሬ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አለ፡፡ ይሄም የቤተክርስቲያኗን የኋላ ታሪክ ያጠይቃል፤ የሀገሪቷ የፖለቲካ ታሪክም እንዲሁ ነው፡፡[144]

እዚህ ላይ መታከል ያለበት ቄሶች በምእመናን (ለቅስና አገልግሎታቸው እንደማካካሻ የተወሰነ ገንዘብ ይሰጧቸዋልና) ላይ አላቸው የሚባለው የጥገኝነት ደረጃ ነው፡፡ ይሄ ምልከታ እንደሚጠቁመው ቀሳውስቱ በየትኛውም ጉዳይ ላይ እንዲሳተፉ ሲደረግ የኑሮ ሁኔታቸውን በተረዳ መልኩ መሆን ያለበት ሲሆን ለሚሠሩት ሥራ እንደ ማበረታቻ የሚሰጣቸው ጉርሻ መጠንም ከዚህ አንጻር መታየት አለበት፡፡ እነዚህ ስጦታዎች ከሀገረኛ የመጻሕፍት ትርጓሜ ዘዬ ጋር የሚናበቡ ትምህርቶችን በመስጠት፣ በማኅበረሰቡ የሚከበሩ ቅዱሳንን ትምህርት በማሰማት እና በተለይም ሐዲስ ኪዳን ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከትውፊት አፈንግጧል ተብሎ መጠርጠር የሚያመጣውን ፍራቻ መቋቋም የሚያስችሉ መሆንም አለባቸው፡፡

ስለ ጋብቻ ጥቂት መረዳት ብቻ ያላቸውና በትክክል በቤተክርስቲያኗ አስተምህሮ ላይ ተመሥርተው መምከር የማይችሉት ለምን እንደሆነ ለመጠየቅም ተሞክሮም ነበር፡፡ በቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት መምህር የሆኑ አንድ ሰው እንደሚያስቡት የዚህ ምክንያት በትውፊት እንደሚታወቀው አብዛኞቹ የእምነቱ መምህራን መነኮሳት ስለሆኑና መነኮሳት ደግሞ ስለ ጋብቻ ስለማይመክሩ ወይም መነኮሳት የባለትዳሮች የንስሓ አባት ከሆኑ ጋብቻን በተመለከተ እንዲመክሩና እንዲያስተምሩ ስለማይጠበቁ ነው፡፡[145] እርሳቸው እንደሚያስቡት የንስሓ አባት የሚሆነው ያገባ ቄስ ከሆነ ሁኔታው ሊለወጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪ እንደጠቀሱትም የቅዱስ ሲኖዶስ ተሰብሳቢዎች በዋነኝነት ጳጳሳት ስለሆኑ እና እነርሱም የማያገቡ በመሆናቸው ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በነዚህ ስበሰባዎች ላይ ለውይይት የመቅረባቸው እና ዋና አጀንዳ የመሆን ዕድላቸው አነስተኛ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንድ መርጌታ እንደተነገረው በአሁን ጊዜ የገጠር ቀሳውስቱ ቤተክርስቲያን ስለ ጋብቻ የምታስተምረውን ትምህርት ለማወቅ የሚያስችላቸው ግብአት እጥረት እንዳለም ማስተዋል ይገባል፡፡ መርጌታው የሚከተለውን ብለዋል፡ ‹‹ቀሳውስቱ ስለ ጋብቻ ሲያስተምሩ ከብሉይ ኪዳን ወይም ከሐዲስ ኪዳን ጥቅሶችን በመጥቀስ እነዛን ጥቅሶች ጥቂት ያብራሯቸዋል እንጂ ሌላ ነገር የለም፡፡››[146] ከቀሳውስቱ ጋር በነበረው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከመጽሐፈ ተክሊል ውጪ ቀሳውስቱ ሌሎች ግብአቶችን አይጠቀሙም፡፡[147] በፍትሐ ነገሥት ላይ የተወሰነ የተብራራ ነገር ቢኖርም ትምህርቱ ግን የሚሰጠው አብዛኞቹ ቀሳውስት በማይደርሱበት ከፍተኛ በሆነው የትምህርት ደረጃ (ወንበር) ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም በፍትሐ ነገሥት ላይ ስለ ጋብቻ የተወሳው በአብዛኛው መሠረታዊ የሆነው ነገር ሲሆን ለዘመኑ ፍላጎቶች የሚሆንም አይደለም፡፡

በአከባቢው ቋንቋ የተዘጋጀ ጠንከር ያለ ነገር ግን ግልጽ የሆነ እና በቀላሉ የሚረዳ አጋዥ ጽሑፍ ለቀሳውስቱ በማንኛውም ጊዜ ሊጠቀሙት የሚችሉት ቋሚ ማጣቀሻ ይሆናል፡፡ በነገረ መለኮት ጉዳይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ያለውን የማያከራክር ቦታ እና አንዳንድ የብሉይ ኪዳን የጋብቻ አረዳዶችን የቀየሩ የሐዋርያት ትምህርቶች ላይ የሠራቸው አንድምታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የእርሱ የጋብቻ ትምህርት ማብራሪያ ለእንዲህ ዓይነቱ ጽሑፍ መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ እየሰጠችው ካለው ሥልጠና (አሠልጣኙ ለሠልጣኞች አሳታፊ ባልሆነ መንገድ የሚያስተምርበት) በተቃራኒ ልክ በዚህ ጥናት እንደተተገበሩት የመስክ ሥራዎች በደንብ አሳታፊ የሆነ አቀራረብ ቀሳውስቱ ዐሳባቸውን እንዲያንጸባርቁ የሚያደርግ ትክክለኛ እና ውጤታማ የሆነ መንገድ ይፈጥርላቸዋል፤ ብሎም በሂደት ሐዋርያት ስለ ጋብቻ፣ የጋብቻ ግንኙነት እና መንፈሳዊ ዕድገት ያስተማሩትን በጥልቀት ለማደራጀት ያግዛቸዋል፡፡

[144] ከቅድስት ሥላሴ የነገረ መለኮት ኮሌጅ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ታኅሣሥ 8፣ 2009፡፡
[145] ከቅዱስ ጳውሎስ የነገረ መለኮት ኮሌጅ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ አዲስ አበባ፣ ጥር 9፣ 2009፡፡
[146] ከአንድ መርጌታ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 4፣ 2009፡፡
[147] ከቄስና የቤተክርስቲያን መምህር ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 24፣ 2009፡፡

dldl
ድልድል